ከከበደ ሚካኤል

# የትንቢት ቀጠሮ

ድራማ

፱ኛ ክፍል

ስለ ግርማዊ ጃንሆይ

የዘውድ በዓል መታሰቢያ

# የትንቢት ፡ ቀጠሮ ።

ከከበደ ፡ ሚካኤል ።

# የትንቢት ፡ ቀጠሮ ።

( ቴ ያ ት ር ) ።

ስለ ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡

የዘውድ ፡ በዓል ፡ መታሰቢያ ።

ኬሚ

ያለደራሲው ፡ ፈቃድ ፡ ማሳተም ፡ ወይም ፡ ቴያትሩን ፡ ማሳየት ፡ አይቻልም ።

Copyright

ተስተካክሎና ፡ ተለቅሞ ፡ በ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በድጋሚ ፡ ታተመ ፡
እንደገና ፡ በ፲፱፻፷፩ ፡ ዓ. ም. ታተመ ።

በብርሃንና ፡ ሰላም ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ፡
አዲስ ፡ አበባ ፡ ኢትዮጵያ ።



ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ።

## የትንቢት ፡ ቀጠሮ ።

እንዳይነጋ ፡ እንዳይመሽ ፡ ብልኀት ፡ ተገኝቶ ፡
ጊዜውን ፡ መከልከል ፡ እንዳይቻል ፡ ከቶ ፡
እንዲሁም ፡ ባለም ፡ ላይ ፡ አለ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡
በዚያም ፡ ቢሉት ፡ በዚህ ፡ መሆኑ ፡ የማይቀር ።

ይህ ፡ «የትንቢት ፡ ቀጠሮ» ፡ የተባለው ፡ ቴያትር ፡ መንፈሳዊና ፡ ሥጋዊ ፡ የሆኑ ፡ ሁለት ፡ ምስጢሮች ፡ ይገኙበታል ። በመንፈሳዊ ፡ በኩል ፡ የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ በመጣበት ፡ ዘመን ፡ ከአረመኔነት ፡ ጋራ ፡ ባደረገው ፡ ረዥም ፡ ትግል ፡ ወንጌል ፡ ድል ፡ እያደረገች ፡ አረመኔነት ፡ ግን ፡ እየተሸነፈ ፡ ሄዶ ፡ እውነተኛይቱ ፡ ሃይማኖት ፡ በመስፋፋት አሁን ፡ ካለችበት ፡ ሰዓት ፡ እንድትደርስ ፡ ለማድረግ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ረድኤት ፡ በመለኮታዊ ፡ ሁኔታ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ አድርጎ ፡ ይደግፋት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ የሚያስረዳ ፡ ምስጢር ፡ ያለበት ፡ ምሳሌ ፡ ነው ።

ሁለተኛውም ፡ በሥጋዊ ፡ በኩል ፡ ጥንቱን ፡ ሲፈጠሩ ፡ ላንዳንድ ፡ ከፍተኛ ፡ ዕድል ፡ የታጩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ተወስኖ ፡ ወደሚጠብቃቸው ፡ ደረጃ ፡ እንዳይደርሱ ፡ ሊያሰናክላቸው ፡ በዕንቅፋትነት ፡ የሚነሣባቸው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እየተሸነፈ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ የሠረጸው ፡ ውሳኔ ፡ በግድም ፡ ሆነ ፡ በውድ ፡ ተፈጻሚ ፡ ከመሆኑ ፡ ሊያግደው ፡ የሚችል ፡ ነገር ፡ እንደሌለ ፡ ያስረዳናል ።

## ማ ሳ ሰ ቢ ያ ።

በፈረንሳይ ፡ ቋንቋ ፡ ስለ ፡ ቴያትር ፡ አከፋፈል ፡ «አክት» ፡ ለሚለው ፡ ቃል ፡ ባማርኛችን ፡ ደራሲው ፡ «ጾታ» ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ ተክቶበታል ።

ጾታ ፡ ማለት ፡ ትርጕሙ ፡ ለዚህ ፡ የተሰጠ ፡ የተስማማ ፡ ነው ።

ካሊቃ ፡ ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ ፡ የተዘጋጀው ፡ የግእዝና ፡ ያማርኛ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ ለዚሁ ፡ ቃል ፡ የሚከተለውን ፡ ትርጕም ፡ ሰጥቶታል ።

ጾታ ፡ ተራ ፡ ረድፍ ፡ ክፍል ፡ ማዕርግ ፡ ዐይነት ፡ ስልት ፡ ወገን ፡ ነገድ ፡ የቅዳሴ ፡ ጸሎት ፡ ጓዝ ፡ . . . . . . . . . .

## ግርማዊ ፡ ሆይ ።

የቴያትር ፡ ሥራ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ሥልጣኔ ፡ ርምጃ ፡ የሰጠውን ፡ ትልቅ ፡ ጥቅም ፡ ከመገንዘብ ፡ የተነሣ ፡ አውሮፓውያን ፡ ያቀዱትን ፡ ስልት ፡ በመከተል ፡ ላገራችን ፡ በሚስማማው ፡ ረገድ ፡ አንድ፡ ቴያትር ፡ እንዳሰናዳ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ስለ ፡ አዘዙኝ ፡ ይህን ፡ «የትንቢት ፡ ቀጠሮ» ፡ የተባለውን ፡ ቴያትር ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ መታሰቢያ ፡ እንዲሆን ፡ በረከት ፡ አድርጌ ፡ አቀርባለሁ ።

ይህ ፡ ቴያትር ፡ ባለፈው ፡ ዓመት ፡ ለግርማዊነትዎ ፡ የልደት ፡ በዓል ፡ ክብር ፡ እንዲታይ ፡ አዘጋጅቼ ፡ ግርማዊነትዎም ፡ ወዶት ፡ እንዲሠራ ፡ ፈቅዶልኝ ፡ በመካከሉ ፡ ስለ ፡ ታመምሁ ፡ ሳይሠራና ፡ ሳይታተም ፡ ቀረ ። በእግዚአብሔር ፡ መሓሪነትና ፡ ግርማዊነትዎም ፡ ለኔ ፡ ለድኻዎ ፡ ባደረገው ፡ ሙሉ ፡ ርዳታ ፡ ከሕመሜ ፡ እንደ ፡ ዳንሁ ፡ ይህንኑ ፡ ከፍጻሜ ፡ ለማድረስ ፡ አስቤ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አንዳንድ ፡ ነገር ፡ ጨምሬ ፡ አሟላሁት ።

ምንም ፡ እንኳ ፡ ሩሶ ፡ ልማድን ፡ አጽድቆ ፡ ኒቼ ፡ ትዕቢትን ፡ አንግሦ ፡ ማኪያቬሊ ፡ ጥቅምን ፡ ብቻ ፡ አክብሮ ፡ ሌሎችም ፡ እነዚህን ፡ የመሰሉ ፡ ሊቃውንት ፡ ኈምዛዛ ፡ የሆነ ፡ ፍልስፍና ፡ እያመጡ ፡ እንደ ፡ ወይን ፡ ፍሬ ፡ ጣፋጭ ፡ የሆነውን ፡ የክርስቲ

ያንን ፡ መንፈስ ፡ ሊያበላሹት ፡ ቢጣጣሩ ፡ ብዙ
ዎች ፡ ፈላስፎች ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ መልካም ፡ አሳብ ፡
እየተመሩ ፡ ጠንክረው ፡ ከክርስቲያንነት ፡ የመነ
ጨው ፡ የእውነተኛው ፡ ሥልጣኔ ፡ ጣዕም ፡ እንዳይ
በላሽ ፡ ይታገላሉ ። የሰዎችን ፡ ሕይወት ፡ አድሶ ፡
ወደ ፡ ትልቅነት ፡ ለመምራት ፡ የክርስቲያንን ፡ ሃይ
ማኖት ፡ ያኽል ፡ የረዳ ፡ ነገር ፡ እንደሌለ ፡ ታሪክ ፡
ይመሰክራል ። ስለዚህ ፡ ባለቅኔዎችና ፡ ደራሲዎች ፡
የሆኑ ፡ ሁሉ ፡ የመልካም ፡ ምሳሌና ፡ የበጎ ፡ መንፈስ ፡
ባሕር ፡ ከሆነው ፡ ከክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ አርእስ
ታቸውን ፡ እየቀዱ ፡ በሊቴራቲር ፡ ዜና ፡ አስደናቂ ፡
የሆነና ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡
ሠሩ ፡ እናያለን ። ዳንቴ ፡ (Divina Commedia)
(መለኮታዊ ፡ ቧልታ) ፡ የተባለ ፡ መሰልና ፡ ተወዳዳሪ ፡
የሌለው ፡ የቅኔ ፡ ሐውልት ፡ የሆነውን ፡ መጽሐፍ ፡
የጻፈው ፡ ሚልተን ፡ (Paradise Lost) (ገነት ፡
ታጣች) ፡ በተባለ ፡ ስያሜ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ መንፈስ ፡
በማሰብ ፡ ብዛት ፡ ሊደርስበት ፡ የሚችለውን ፡ ከፍ ፡
ያለ ፡ የአእምሮ ፡ አስተያየት ፡ ለማስረዳት ፡ ትልቅ ፡
አብነትና ፡ አስደናቂ ፡ የሆነ ፡ ሥራ ፡ ተብሎ ፡ የተመ
ሰገነውን ፡ መጽሐፍ ፡ የጻፈው ፡ ለታስ ፡ (Geru-
salemme Liberata) (የኢየሩሳሌም ፡ ነጻ ፡ መው
ጣት) ፡ ብሎ ፡ የሰየመውን ፡ መላው ፡ ዓለም ፡ የተደነ
ቀበትን ፡ መጽሐፍ ፡ የጻፈው ፡ ራሲን ፡ የሚባለው ፡
ትልቁ ፡ ባለቅኔ ፡ ከዋና ፡ ሥራዎቹ ፡ አንደኛው ፡ ተብ
ሎ ፡ የሚቈጠረው ፡ (Athalie) (ኅታሊያ) ፡ ቴያት





ሩን ፡ የጻፈው ፡ ሻቶብርያን ፡ የሚባለው ፡ ትልቁ ፡
ደራሲ ፡ "Génie du christianisme" የተባለው ፡
ድርሰቱን ፡ የጻፈው ፡ ከዚሁ ፡ ከክርስቲያን ፡ ሃይማ
ኖት ፡ ምንጭ ፡ እየቀዱ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እኛ ፡ ደግሞ ፡
ኢትዮጵያውያን ፡ በክርስቲያንነት ፡ ጥንታዊነታችን ፡
የተመሰከረ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ይህንኑ ፡ መንገድ ፡ በተቻለ ፡
መጠን ፡ ልንከተለው ፡ የሚገባን ፡ መሆኑን ፡ ከመረ
ዳቴ ፡ የተነሣ ፡ ወደዚህ ፡ ምንጭ ፡ ተመርቼ ፡ ለቴያ
ትሩ ፡ ይህን ፡ አርእስት ፡ መረጥሁ ።

ይሁን ፡ እንጂ ፤ ደራሲ ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ሥራው ፡
ዋጋ ፡ የሚያገኝለት ፡ ላንባቢዎችና ፡ ለተመልካቾች ፡
በሚያቀርበው ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ በሚገልጠው ፡ ያሳብ ፡
አስተያየትና ፡ ባነጋገሩ ፡ ውበት ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ የአ
ርእስቱን ፡ አመራረጥ ፡ በማሳመር ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።

ይህን ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ በተቻለኝ ፡
መጠን ፡ ደክሜበት ፡ ያቀረብሁት ፡ ይህ ፡ ቴያትር ፡
ለዚሁ ፡ ለቴያትር ፡ ሙያ ፡ ስጦታ ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡
ተመርተውበት ፡ የበለጠ ፡ አድርገው ፡ እንዲሠሩ ፡
ምሳሌ ፡ ይሆናቸዋል ፡ ስል ፡ በሙሉ ፡ እየተመኘሁ ፡
ይህንኑ ፡ ሳቀርብ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ላገራችን ፡ ሥል
ጣኔ ፡ እርምጃ ፡ የሚጥሩላትና ፡ የሚያስቡላት ፡ አሳብ ፡
በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ እንዲፈጸም ፡ ጸሎቴን ፡ ከመላው ፡
የሕዝብዎ ፡ ጸሎት ፡ ጋራ ፡ እያስተባበርኩ ፡ ነው ።

በጠቅላላውም ፡ ይህን ፡ ቴያትር ፡ ያዘጋጀሁበት ፡
መሠረታዊው ፡ አሳብ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ትምህርትን ፡

ለማስፋፋት ፡ ያቀደው ፡ አሳብ ፡ በሰፊው ፡ ከመከናወኑ ፡ የተነሣ ፡ እንሆ ፡ ዛሬ ፡ ባመት ፡ ባመቱ ፡ የትምህርት ፡ ቤቶች ፡ በጣም ፡ እየተጨመሩ ፡ ከነሱም ፡ ጋራ ፡ የተማሪዎቹ ፡ ቊጥር ፡ እየበረከተ ፡ ስለ ፡ ሄደ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ወጣቶች ፡ ከትምህርታቸው ፡ ውጭ ፡ ባላቸው ፡ ሰዓት ፡ ዕውቀትና ፡ ጥበብ ፡ እንዲስፋፉ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ በግል ፡ ሊረዱ ፡ ስለሚችሉበት ፡ መንገድ ፡ መልካም ፡ አብነት ፡ እንዲያገኙ ፡ ከመሪ ፡ ምሳሌዎች ፡ አንደኛው ፡ ሊሆናቸው ፡ ይችላል ፡ በማለት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለሥራዬ ፡ ትምክሕተኛ ፡ ግምት ፡ ለመስጠት ፡ አይደለም ።



## ቴያትር ።

ቴያትር ፡ ማለት ፡ ሰው ፡ ጠባዩን ፡ ከክፋት ፡ ወደ ፡ ደግነት ፡ አእምሮውን ፡ ከስሕተት ፡ ወደ ፡ ዕውቀት ፡ እየመለሰ ፡ ወደ ፡ ጥበብ ፡ የሚመራበት ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ የሞላበት ፡ ጨዋታ ፡ ነው ።

ቴያትር ፡ ማለት ፡ ሰው ፡ ያለፈውን ፡ ታሪክ ፡ ጠቅሶና ፡ አስታውሶ ፡ የተረሳውን ፡ ነገር ፡ ከጨለማ ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ እየመለሰ ፡ አዲስ ፡ ሕይወት ፡ በመስጠት ፡ ያባቶቹን ፡ መታሰቢያ ፡ መጣሪያ ፡ አድርጎ ፡ በወጣቶቹ ፡ ልብ ፡ ውስጥ ፡ ያንቀላፋውን ፡ ያገር ፡ ፍቅር ፡ የሚቀሰቅስበት ፡ ነው ።

ቴያትር ፡ ማለት ፡ ሲያዩትና ፡ ሲሰሙት ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ሆኖ ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ደግሞ ፡ መጽሐፉ ፡ ታትሞ ፡ ሲወጣ ፡ ያማርኛው ፡ መጣራትና ፡ የታሪኩ ፡ ምስጢራዊነት ፡ የተስማማና ፡ የተዋሐደ ፡ ሆኖ ፡ በምሳሌውም ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ የሰውን ፡ አሳብ ፡ ወደ ፡ ከፍተኛ ፡ አስተያየት ፡ እየመራ ፡ ጠባይን ፡ እያረቀ ፡ ጕድለትን ፡ እየገለጠ ፡ ስሜትን ፡ እያራቀቀ ፡ ይልቁንም ፡ ለሕፃናት ፡ ጠቃሚ ፡ ትምህርት ፡ በመሆን ፡ በድርሰት ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ የማይሻርና ፡ የማይደመሰስ ፡ የቋንቋ ፡ ሐውልት ፡ ሆኖ ፡ የሚኖር ፡ መታሰቢያ ፡ ነው ።

ቴያትር ፡ ማለት ፡ ከምድራዊ ፡ ወደ ፡ ሰማያዊ ፡ አስተያየት ፡ እየተሳበ ፡ ከግዙፍ ፡ ወደ ፡ ረቂቅ ፡ እም

ነት ፡ ከደካማነት ፡ ወደ ፡ ፍጹምነት ፡ ባሕሪ ፡ ሰው ፡ የሚነሣበት ፡ የምኞት ፡ ክንፍ ፡ ነው ።

የቴያትር ፡ ሥራ ፡ በሦስት ፡ ዋና ፡ ክፍሎች ፡ ይለያል ።

እነዚህም ፡ ትራዤዲ ፡ ድራማ ፡ ኮሜዲ ፡ ናቸው።

ትራዤዲ ፡ ማለት ፡ ትልቅ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ የሚገኝበትን ፡ ታሪክና ፡ አሳብ ፡ ባማረ ፡ ንግግር ፡ ፍርሀትንና ፡ ሽብርን ፡ በሰው ፡ ልብ ፡ ውስጥ ፡ እየዘራ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ የርኅራኄንና ፡ የሐዘንን ፡ ስሜት ፡ እየቀሰቀሰ ፡ በግጥም ፡ የሚጻፍ ፡ ቴያትር ፡ ነው ።

ድራማ ፡ ማለት ፡ የሚያሳዝነውንና ፡ የሚያሥቀውን ፡ ነገር ፡ እየቀላቀለ ፡ ብዙ ፡ ጊዜም ፡ አደጋ ፡ የሚታይበት ፡ ብጥብጥና ፡ ሁከት ፡ የሞላበት ፡ ቴያትር ፡ ነው ።

ኮሜዲ ፡ ማለት ፡ በሰዎች ፡ ዘንድ ፡ ያለውን ፡ መጥፎ ፡ ፀመልና ፡ መጥፎ ፡ ልማድ ፡ የሞኝነትንም ፡ ባሕሪ ፡ በሚያሥቅ ፡ አኳኋን ፡ አድርጎ ፡ ስሕተትን ፡ በቧልታ ፡ ብቻ ፡ የሚዘልፍ ፡ ቴያትር ፡ ነው ።





የዚህ ፡ ቴያትር ፡ ፍሬ ፡ ነገሩ ፡ የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ሲመሠረት ፡ ካረመኔነት ፡ ጋራ ፡ ብርቱ ፡ ትግል ፡ ስለ ፡ ነበረበት ፡ ሐዋርያትና ፡ ሰማዕታት ፡ በመሥዋዕትነት ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ኑሮ ፡ ከገንዘባቸውና ፡ ከሕይወታቸው ፡ ጋራ ፡ ለሃይማኖታቸው ፡ ክብር ፡ ሲሉ ፡ አሳልፈው ፡ እየሰጡ ፡ በልበ ፡ ቈራጥነታቸው ፡ ላይ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ እየተጨመረ ፡ ከሠሩት ፡ ቅድስና ፡ ከሞላበት ፡ ገድል ፡ በቀር ፡ እግዚአብሔር ፡ ደግሞ ፡ መለኮታዊ ፡ ኃይሉን ፡ በብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሁኔታ ፡ እየገለጸ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ አድርጎ ፡ የክርስቲያንን ፡ ሃይማኖት ፡ እውነተኛነት ፡ ለሰዎች ፡ እንዳስተማረና ፡ እንዳስረዳ ፡ የሚገልጽ ፡ ነው ።

የክርስቲያንን ፡ ሃይማኖት ፡ በመቀበልና ፡ እውነተኛ ፡ ሃይማኖትነቷንም ፡ በማወቅ ፡ ቀደምትነት ፡ ካገኙት ፡ አገሮች ፡ አንደኛይቱ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ይህንን ፡ ታላቁን ፡ የምሥራች ፡ እንድትሰማ ፡ ያደረገላት ፡ እሱው ፡ ባለቤቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በቅዱስ ፡ መጽሐፍ ፡ እናገኘዋለን ። ይህም ፡ እንዲህ ፡ ነው ። የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ፊልጶስን ፡ እንዲህ ፡ አለው ፤ ተነሣና ፡ ሂድ ፡ በደቡብ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ እስከ ፡ ጋዛ ፡ በምታወርደው ፡ መንገድ ፡ እርሷም ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ናት ። ፊልጶስም ፡ ተነሥቶ ፡ ሄደ ።

እንሆም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ንግሥት ፡ በህንደኬ ፡
ዘንድ ፡ ሀብቱና ፡ ከብቱ ፡ ከሹማምቶቿ ፡ ሁሉ ፡ የሚ
በልጥ ፡ ጃንደረባ ፡ የሆነ ፡ አንድ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡
ነበር ። እሱም ፡ ሊሰግድ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጥቶ፡
በሠረገላው ፡ ተቀምጦ ፡ ወዳገሩ ፡ ሲመለስ ፡ የነቢ
ዩን ፡ የኢሳይያስን ፡ መጽሐፍ ፡ ያነብ ፡ ነበር ። መን
ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፊልጶስን ፡ አለው ፤ ሂድ ፡ ወደዚህ ፡
ሠረገላም ፡ ቅረብ ። ፊልጶስም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ኢትዮ
ጵያዊው ፡ ኢሳይያስን ፡ ሲያነብ ፡ ሰማው ። አለውም ፤
ይህን ፡ የምታነበውን ፡ ቃል ፡ ታስተውላለኽን ፤ እር
ሱም ፡ መለሰ ። ይህ ፡ እንዴት ፡ ይቻለኛል ፡ የሚያስ
ተምረኝ ፡ ሰው ፡ ባይኖር ። ፊልጶስም ፡ ወደ ፡ ሠረገ
ላኽ ፡ ወጥቼ ፡ አብሬኽ ፡ እቀመጥ ፡ ዘንድ ፡ ፍቀድ
ልኝ ፡ ሲል ፡ ለመነው ።

የመጽሐፉም ፡ ስፍራ ፡ ያነበው ፡ የነበረው ፡ እን
ዲህ ፡ የሚል ፡ ነበር ፤ እንደ ፡ በግ ፡ ሊታረድ ፡ ተነዳ ።
በጉም ፡ በሚያርደው ፡ ሰው ፡ ፊት ፡ ዝም ፡ እንዲል ፡
እሱም ፡ እንዲሁ ፡ አፉን ፡ አልከፈተም ፤ በትሕትናው ፡
ፍርዱ ፡ ወገደ ። ትውልዱን ፡ ይናገር ፡ ዘንድ ፡ ከቶ ፡
ማን ፡ ይችላል ፤ ሕይወት ፡ በምድር ፡ ወጥታለችና ።
ጃንደረባውም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ፊልጶስን ፡ ጠየቀው ፤
እለምንኻለሁ ፡ ትነግረኝ ፡ ዘንድ ፡ ይህንን ፡ የሚናገ
ረው ፡ ስለ ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ሆነ ። ነቢዩ ፡ የሚናገረው ፡
ስለ ፡ ራሱ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ ስለ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ነው ።
ፊልጶስም ፡ አፉን ፡ ከፈተ ፤ ከዚህም ፡ መጽሐፍ ፡





ዝምሮ ፡ ስለ ፡ ኢየሱስ ፡ ያስተምረው ፡ ነበር ። መንገዳ
ቸውንም ፡ ሲጓዙ ፡ ውሃ ፡ ካለበት ፡ ቦታ ፡ ደረሱ ።
ጃንደረባውም ፡ ከልቡ ፡ ስላመነ ፡ እንሆ ፡ ውሃ ፡ እንግ
ዴህ ፡ እጠመቅ ፡ ዘንድ ፡ የሚከለክለኝ ፡ ምን ፡ ነገር ፡
አለ? ፊልጶስም ፡ መለሰ ፡ በፍጹም ፡ ልብኽ ፡ እውነት ፡
ካመንኽ ፡ ይገባሃል ። ኢትዮጵያዊውም ፡ መለሰ ፤ እኔ ፡
አምናለሁ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የእግዚአብሔር ፡
ልጅ ፡ እንደ ፡ ሆነ ። ፊልጶስም ፡ ወደ ፡ ውሃው ፡ አብ
ሮት ፡ ሄደ ፡ አጠመቀው ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የእግዚ
አብሔር ፡ መንፈስ ፡ ፊልጶስን ፡ ነጥቆ ፡ ወሰደው ።

ይህ ፡ ዕድለኛው ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ወዳገሩ ፡ በገባ ፡
ጊዜ ፡ ስለ ፡ ጌታ ፡ መወለድና ፡ ለሕዝቦች ፡ ብርሃን ፡
ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ወንጌል ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ መሰ
በኩ ፡ የምሥራቹን ፡ ላገራችን ፡ ሰዎች ፡ መዠመሪያ ፡
የነገራቸው ፡ እሱ ፡ መሆኑ ፡ አይጠረጠርም ። በዚህ ፡
አኳኋን ፡ በሌሎችም ፡ አገሮች ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡
ነገር ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ ባጭሩ ፡ እንመልከተው ።

አሁን ፡ ፈረንሳዊ ፡ የምትባለው ፡ ጥንት ፡ ግን ፡
ጎል ፡ ተብላ ፡ ትጠራ ፡ የነበረችው ፡ አገር ፡ ንጉሥዋ ፡
ክሎቪስ ፡ አረመኔ ፡ ነበር ። ሚስቱ ፡ ክሎቲልድ ፡ ግን ፡
ክርስቲያን ፡ ስለ ፡ ነበረች ፡ ጣዖታትን ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡
እውነተኛው ፡ አምላክ ፡ ሃይማኖት ፡ እንዲገባ ፡ ሁል ፡
ጊዜ ፡ ትመክረውና ፡ ታስተምረው ፡ ስለ ፡ ነበረች ፡
ክሎቪስ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የሚስቱ ፡ ትምህርት ፡
ከልቡ ፡ ቢደርስ ፡ ከጥንት ፡ ልማድ ፡ የመጣለትን ፡

እምነት ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ ክርስቲያንነት ፡ እንዳይመለስ ፡ ያረመኔነቱ ፡ ትዕቢት ፡ ስላሸነፈው ፡ እንቢ ፡ ብሎ ፡ ይኖር ፡ ነበር ።

ባ፬፻፺ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ የጀርመን ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ የጎልን ፡ አገር ፡ ሊያስገብሩ ፡ አስበው ፡ ስለ ፡ ዘመቱባት ፡ ክሎቪስ ፡ ሰራዊቱን ፡ አስከትሎ ፡ ጦር ነት ፡ ገጠማቸው ። ሞትን ፡ የማይፈሩ ፡ ጦርነትንም ፡ ደስ ፡ እንደሚያሰኝ ፡ ጨዋታ ፡ አድርገው ፡ የሚቈጥሩ ፡ የጀርመን ፡ ኀይለኞች ፡ ጀግንነት ፡ እየተሜነው፡ ስለ ፡ ሄደ ፡ የክሎቪስ ፡ ሰራዊት ፡ የጦር ፡ ግንባሩ ፡ መሰበር ፡ ሲዠምር ፡ ክሎቪስ ፡ የመንግሥቱ ፡ ፍጻሜ ፡ መቃረቡን ፡ ተረድቶ ፡ በልቡ ፡ ሐዘንና ፡ ሽብር ፡ አደረበት ። በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ሚስቱ ፡ ክሎቲልድ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኀያል ፡ አምላክ ፡ የሰማይና ፡ የመሬት ፡ ጌታ ፡ ስለ ፡ መሆኑና ፡ ስለ ፡ ታላቅነቱም ፡ ታስተምረው ፡ የነበረው ፡ ሁሉ ፡ ትዝ ፡ ስላለው ፡ «ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፡ ድልን ፡ ብትሰጠኝ ፡ ባንተ ፡ አምናለሁ ፤ በስምኽም ፡ እጠመቃለሁ» ፡ ብሎ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ገባ ። እግዚአብሔርም ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ይህንን ፡ ከልብ ፡ የመነጨ ፡ ጸሎት ፡ ሰምቶ ፡ በሚያስደንቅ ፡ ሁኔታ ፡ ወዲያው ፡ ለተሰበረው ፡ ጦር ፡ ግንባር ፡ ግርማና ፡ ኀይልን ፡ ሰጥቶ ፡ ክሎቪስ ፡ በነገሩ ፡ እስኪደነቅበት ፡ ድረስ ፡ ድል ፡ አድራጊነትን ፡ ሰጠው ። ክሎቪስ ፡ በሐዘንና ፡ በውርደት ፡ ፈንታ ፡





ክብርንና ፡ ደስታን ፡ ተጐናጽፎ ፡ ወደ ፡ ዙፋኑ ፡ ሲመለስ ፡ ያለምስክር ፡ ልብ ፡ ለልብ ፡ የገባውን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ሳይዘነጋ ፡ ወይም ፡ ሳይሸፍጥ ፡ ስለቱን ፡ ሊፈጽም ፡ ጥምቀትን ፡ ራሱ ፡ ጠይቆ ፡ ወደ ፡ መቅደስ ፡ ቀርቧል ። ያጠመቀውም ፡ አቡን ፡ ክሎቪስ ፡ ኵሩ ፡ አረመኔ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ስለሚያውቅ ፡ በታሪክ ፡ ተጽፎ ፡ የሚገኘውን ፡ ቀጥሎ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ሥርዐተ ፡ ጥምቀቱን ፡ ሲፈጽምለት ፡ ተናግሮታል ። ቃሉም ፡ ይህ ፡ ነው ፤ «አንተ ፡ ትዕቢተኛ ፡ ሲካምብር፡ ሆይ ፡ ግንባርኽን ፡ አጐንብስኽ ፡ ታቃጥለው ፡ የነበረውን ፡ ስገድለት ፤ ትሰግድለት ፡ የነበረውንም ፡ አቃጥለው» ፡ ጣዖትን ፡ ሲል ፡ ነው ። በዚህ ፡ ቀን ፡ ከሹማምቶቹና ፡ ከወታደሮቹ ፡ መካከል ፡ ከክሎቪስ ፡ ጋራ ፡ ስድስት ፡ ሺ ፡ የሚሆኑ ፡ ሰዎች ፡ አብረው ፡ ተጠምቀዋል ። በክርስቲያኖች ፡ ላይ ፡ የበለጠ ፡ ግፍና ፡ ከሁሉ ፡ የባሰ ፡ ደም ፡ የፈሰሰባት ፡ አገር ፡ ሮማ ፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ ታሪክ ፡ ይናገራል ። ይልቁንም ፡ በጨካኙ ፡ በኔሮን ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በሰማዕታት ፡ ላይ ፡ የደረሰባቸው ፡ የጭካኔ ፡ ሥራ ፡ ከልማድ፡ የወጣ ፡ ነው ።

ታሲት ፡ የሚባለው ፡ ታሪክ ፡ ጸሓፊ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ጽፏል ፤ «ብዙዎቹን ፡ (ክርስቲያኖች) ፡ ያውሬ፡ ደበሎ ፡ አልብሰው ፡ ውሾች ፡ እየለቀቁባቸው ፡ እየገነጣጠሉና ፡ እየቦጫጨቁ ፡ በልተዋቸዋል ። ብዙዎ

ችንም ፡ አካላታቸውን ፡ ሙጫና ፡ ድኝ ፡ ቀብተው ፡ በግንድ ፡ ላይ ፡ አስረው ፡ እያቃጠሉ ፡ እንደ ፡ ጧፍ ፡ ሆነው ፡ ብርሃን ፡ እንዲሰጡ ፡ አድርገዋቸዋል ፡፡ ክር ስቲያኖች ፡ ከነሕይወታቸው ፡ እንዲህ ፡ እንደ ፡ ችቦ ፡ ሆነው ፡ እየነደዱ ፡ በሚሰጡት ፡ የእሳት ፡ ውጋጋን ፡ ውስጥ ፡ ኔሮን ፡ ራሱ ፡ በሠረገላ ፡ ተቀምጦ ፡ ይጫ ወት ፡ ነበር» ፡፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ በመስቀል ፡ ቍል ቍል ፡ ተዘቅዝቆ ፡ ተሰቅሎ ፡ የሞተው ፡ ጳውሎስም ፡ በሰይፍ ፡ የታረደው ፡ በኔሮን ፡ ዘመን ፡ ነው ፡፡

እግዚአብሔር ፡ ለዚህ ፡ ሁሉ ፡ ግፍ ፡ ፍጻሜ ፡ ለማድረግ ፡ ሲያስብ ፡ ቈስጠንጢኖስን ፡ አስነሥቶ ፡ ለክርስቲያኖች ፡ ዕረፍት ፡ ሰጥቷቸዋል ፡፡ ቈስጠን ጢኖስም ፡ እንደ ፡ ክሎቪስ ፡ ከመሠረቱ ፡ አረመኔ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፤ ወደ ፡ ጦርነት ፡ ሲሄድ ፡ በሰማይ ፡ ላይ ፡ የብርሃን ፡ መስቀል ፡ አየ ፡፡ በመስቀሉም ፡ ዙሪያ ፡ «በዚህ ፡ ምልክት ፡ ድል ፡ ታደርጋለኽ» ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ተጽፎ ፡ ይነበብ ፡ ነበር ፡፡ ቈስጠንጢኖስ ፡ በሰንደቅ ፡ ዐላማው ፡ ላይ ፡ የመስቀል ፡ ምልክት ፡ ያለበት ፡ የወርቅ ፡ አክሊል ፡ አስጠልፎ ፡ ለጦር ፡ ሰራዊቱ ፡ ሰጠ ፡፡ በዚሁ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ መሠረት ፡ ቈስጠንጢኖስ ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ በሮማ ፡ መንበረ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ የቄሳሮችን ፡ ዘውድ ፡ ደፍቶ ፡ ከነገሠ ፡ በኋላ ፡ በ፫፻፲፫ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ክርስቲያኖች ፡ የሃይማኖት ፡ ሙሉ ፡ ነጻነት ፡ እንዲ ያገኙ ፡ ዐዋጅ ፡ አስነገረ ፡፡





ተመልካች ፡ ይህን ፡ ቴያትር ፡ ካየ ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ ከሆን ፡ ኮከብ ፡ ቈጣሪዎች ፡ የሚናገሩት ፡ ትንቢት ፡ ሁሉ ፡ መሠረት ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ መሆኑ ፡ ነዋ? ብሎ ፡ የመጠራጠሪያ ፡ ወይም ፡ የመከራከሪያ ፡ አሳብ ፡ በመንፈሱ ፡ ሊመጣበት ፡ ይችላል ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ዓለም ፡ ያረመኔነት ፡ ጨለማ ፡ ውጧት ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ አምልኮት ፡ እምነት ፡ ሥልጥኖባት ፡ በነበረ በት ፡ ዘመን ፡ ከከለዳውያን ፡ የተገኘ ፡ ጥበብ ፡ ነው ፡ የሚባለው ፡ ይህ ፡ ኮከብ ፡ በመቍጠር ፡ ትንቢት ፡ የመናገር ፡ ሥራ ፡ ከትልቅ ፡ ጥበብ ፡ ተቈጥሮ ፡ ይታመ ንበትና ፡ ይሠራበት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ኋላ ፡ ግን ፡ የክር ስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ዕውቀትን ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ዘርግቶ ፡ ሰዎችን ፡ በሥጋዊም ፡ ሆነ ፡ በመንፈሳዊ ፡ በኩል ፡ ጥበብን ፡ እየገለጠላቸው ፡ በሥልጣኔ ፡ መን ገድ ፡ እየተራቀቁ ፡ በጣም ፡ እንዲራመዱ ፡ ካደረጋ ቸው ፡ ወዲህ ፡ የኮከብ ፡ መቍጠር ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ አሮጌ ፡ ዕቃ ፡ የወደቀና ፡ የተናቀ ፡ ሆኖ ፡ መቅረቱን ፡ ዐይናማ ፡ የሆነ ፡ ታሪክ ፡ መርማሪ ፡ አይዘነጋውም ፡፡

ዳሩ ፡ ግን ፡ ማንኛውም ፡ ነገር ፡ የሚሆነው ፡ እንደ ፡ ዘመኑ ፡ ልማድና ፡ እንደ ፡ ሕዝቡ ፡ ጠባይ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሰብአ ፡ ሰገል ፡ ጌታ ፡ መወለዱን ፡ በኮ ከቡ ፡ አይተናልና ፡ ሄደን ፡ እንስገድለት ፡ ብለው ፡ ገጸ ፡ በረከታቸውን ፡ ይዘው ፡ ሊሹት ፡ እንደ ፡ ተነሡ ፡ አግኝተውትም ፡ እንደ ፡ ሰገዱለት ፡ በመጽሐፍ ፡ የም ናውቀው ፡ ነገር ፡ ነው ፡፡ በአሪት ፡ ዘኍልቍ ፡ ምዕ

ራፍ ፡ ፳፪ ፡ ቍጥር ፡ ፳፪ ፡ እስከ ፡ ፴፭ ፡ ቀጥሎ ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ ተጽፎ ፡ እናገኛለን ።

«ባላቅ ፡ እስራኤላውያንን ፡ እንዲረግምለት ፡ በለዓምን ፡ ባስጠራው ፡ ጊዜ ፡ በለዓም ፡ ባህያው ፡ ተቀምጦ ፡ ሲሄድ ፡ አህያይቱ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መልክተኛ ፡ አይታ ፡ ጌታዋን ፡ በለዓምን ፡ እንደ ፡ ተሸከመች ፡ ተኛች ። በለዓምም ፡ በዚሁ ፡ ሥራዋ ፡ ተቈጥቶ ፡ በዱላ ፡ ደበደባት ።

እግዚአብሔርም ፡ ያህያይቱን ፡ አፍ ፡ ከፈተ ፤ በለዓምንም ፡ አለችው ፡ ምን ፡ ባጠፋሁ ፡ እንደዚህ ፡ አድርገኽ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ በዱላ ፡ ትደበድበኛለኽ? እንደዚህ ፡ አድርገሽ ፡ ከማላገጥ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ ታደርጊብኝ ፡ ኖሯል ፡ ብሎ ፡ በለዓም ፡ መለሰላት ። አህያይቱም ፡ መለሰች ፤ በለዓምን ፡ አለችው ፤ እኔ ፡ አህያኽ ፡ አይደለሁምን ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ የምትቀመጥብኝ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ዐመል ፡ አይተኽብኝ ፡ ታውቃለኽን ፤ በለዓምም ፡ መሰከረ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ዐመል ፡ እንዳላየባት ።

እግዚአብሔር ፡ የበለዓምን ፡ ዐይን ፡ ከፈተ ፤ የተመዘዘ ፡ ሰይፍ ፡ በጁ ፡ ይዞ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልክተኛ ፡ ከመንገድ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ አየ ።

እግዚአብሔር ፡ እንኳንስ ፡ የሰውን ፡ የእንስሳን ፡ አፍ ፡ ከፍቶ ፡ እንደሚያናግር ፡ ይህ ፡ ጥቅስ ፡ ያስረዳናል ።





ኋላም ፡ በተገናኙ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ባፌ ፡ የሚያደርገውን ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የምናገረው ፡ ብሎ ፡ በለዓም ፡ ለባላቅ ፡ መልሶለታል ።

በጥንት ፡ ዘመን ፡ ይታመንባቸው ፡ ከነበሩት ፡ ከብዙዎቹ ፡ ያምልኮት ፡ ነገሮች ፡ አንደኛው ፡ በጣዖት ፡ መቅደስ ፡ ይነገር ፡ የነበረው ፡ ትንቢት ፡ ነው ። ከሁሉም ፡ የሚበልጠው ፡ በግሪክ ፡ አገር ፡ ዴልፍ ፡ በሚባለው ፡ ከተማ ፡ አጵሎን ፡ ለሚባለው ፡ ጣዖት ፡ በተሠራው ፡ መቅደስ ፡ ውስጥ ፡ የሚነገረው ፡ ትንቢት ፡ ነበር ። የዚህም ፡ የትንቢት ፡ ነገር ፡ እንዲህ ፡ ነው ፤ ፒቲ ፡ ፒቶኒስ ፡ ወይም ፡ ሲቢል ፡ (ሳቤላ) ፡ የምትባል ፡ በመቅደሱ ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ካህናት ፡ ኗሪና ፡ አገልጋይ ፡ በሆነች ፡ ሴት ፡ አፍ ፡ አምላኩ ፡ (ጣዖቱ) ፡ እያደረ ፡ ባለጕዳዮች ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ሊያውቁት ፡ ስለሚፈልጉት ፡ ስለ ፡ ማንኛውም ፡ ስለ ፡ ችግራቸው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ለሚያቀርቡት ፡ ጥያቄ ፡ መልሱ ፡ በትንቢት ፡ ይሰጣቸዋል ፡ ተብሎ ፡ ይታመንበት ፡ ነበር ። ትንቢቱ ፡ ከሚነገርበት ፡ ቀን ፡ አስቀድሞ ፡ ፒቶኒስ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ከጾመች ፡ በኋላ ፡ የ«ሎሪዬ» ፡ ዛፍ ፡ ቅጠል ፡ ትበላለች ። ይህም ፡ ቅጠል ፡ ሲያሰክራት ፡ በሦስት ፡ እግር ፡ ከቆመ ፡ ጠረጴዛ ፡ ላይ ፡ ወጥታ ፡ ከጠረጴዛው ፡ ሥር ፡ የሚቀረና ፡ ጢስ ፡ ይጢስባታል ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ሰውነቷን ፡ በሙሉ ፡ እንደ ፡ ወባ ፡ ይመታትና ፡ ጠጕሯ ፡ ቆሞ ፡ አፏም ፡ ይንቀጠቀጥና ፡ አረፋ ፡ ይደፍቃል ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ትንቢት ፡ መና

ገር ፡ ትዝምራለች ። በጥንት ፡ ዘመን ፡ የነበሩት ፡ ነገሥታት ፡ ስለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ችግር ፡ የሚሆነውን ፡ ነገር ፡ ለማወቅ ፡ ትንቢቷን ፡ መጠየቅና ፡ የምትሰጣቸውንም ፡ ምላሽ ፡ መስማት ፡ የሚጓጉለትና ፡ የሚጣጣሩለት ፡ ጕዳይ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ በታሪክ ፡ ተጽፎ ፡ እናገኘዋለን ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ አውግስጦስ ፡ ቄሳር ፡ ለዚሁ ፡ ጕዳይ ፡ ወደ ፡ ፒቶኒስ ፡ (ሳቤላ) ፡



የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ መምጣቱ ፡ ሳቤላ ፡ ለአውግስጦስ ፡ ቄሳር ፡ ትንቢት ፡ እንደ ፡ ነገረችው ።

ዘንድ ፡ ሄዶ ፡ ሳለ ፡ ከቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ በተገኘው ፡ ምስክርነት ፡ መሠረት ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ላይ ፡ እንደምታዩት ፡ ሩፋኤል ፡ የሚባለው ፡ ትልቁ ፡





ሥዕል ፡ ሠዓሊ ፡ እንደ ፡ ነደፈው ፡ ፒቶኒስ ፡ ለአውግስጦስ ፡ ቄሳር ፡ ስለ ፡ ክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ መምጣት ፡ ትንቢት ፡ ነግራዋለች ። ይህም ፡ አረመኔዎች ፡ ከስሕተት ፡ ወደ ፡ እውነት ፡ ከጨለማ ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ እንዲመለሱ ፡ ለማድረግ ፡ እግዚአብሔር ፡ ክብሩን ፡ ለእነሱ ፡ በሚስማማቸው ፡ መንገድ ፡ እንደ ፡ ገለጠላቸው ፡ ያስረዳናል ።

## ማሳሰቢያ ።

ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ አሁን ፡ በመጨረሻ ፡ ጊዜ ፡ ሲታተም ፡ ደራሲው ፡ ከብዙ ፡ ቦታ ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ እየጨመረበት ፡ እንዲስፋፋ ፡ አድርጎታል ።

## ተጫዋቾች ።

ንጉሥ ፡
አንድ ፡ ወጣት ፡
ኮከብ ፡ ቈጣሪ ፡
የንጉሥ ፡ ባለሟል ።
አንድ ፡ ካህን ፡
የንጉሥ ፡ እንደራሴ ፡
የንጉሥ ፡ ልጅ ፡ (ልዕልት) ፡
ኀደኛዋ ፡
አገረ ፡ ገዥ ፡
የወታደር ፡ አለቃ ፡
የንጉሥ ፡ አሽከር ፡
የንጉሥ ፡ ወታደር ፡
አንድ ፡ ሰርገኛ ፡
አንድ ፡ ወታደር ፡
ገረድ ፡

## አንደኛ ፡ ጾታ ።

### ትርኢት ፡ ፩ ።

ንጉሥ ፡ ወታደር ፡ ኮከብ ፡ ቈጣሪ ፡ ገረድ ።

(ጊዜው ፡ ጨለማ ፡ ነው ፤ ከዋክብት ፡ በሰማይ ፡ ላይ ፡ ይታያሉ) ።

ንጉሥ ።

ቀን ፡ ሲሠራ ፡ ውሎ ፡ ሕዝቡ ፡ ሰራዊቱ ፡
ሁሉም ፡ በጸጥታ ፡ ገብቶ ፡ በየቤቱ ፡
እንሆ ፡ ተቀምጧል ፡ በሰላም ፡ በጤና ፡
ከዋክብት ፡ በሰማይ ፡ የብርሃንን ፡ ፋና ፡
በውበት ፡ በጸዳል ፡ ለመሬት ፡ ሲያወርዱ ፡
ያዳም ፡ ልጅ ፡ በወገን ፡ በዘር ፡ በነገዱ ፡
ተከፍሎ ፡ ባለበት ፡ የፈጣሪን ፡ ግርማ ፡
ለማድነቅ ፡ ይችላል ፡ ሌሊት ፡ በጨለማ ።

ወታደር ።

እውነት ፡ ነው ፡ ከተማው ፡ ሰላምን ፡ አግኝቶ ፡
ሕዝብ ፡ እንዲህ ፡ ሲከተት ፡ በየቤቱ ፡ ገብቶ ፡
ለሚያየው ፡ ደስ ፡ ይላል ፡ ለሚመለከተው ።

ንጉሥ ።

ሁሉም ፡ በደግ ፡ አሳብ ፡ ክፉን ፡ ነገር ፡ ትቶው ፡
በሰላም ፡ ሲኖሩ ፡ እንዲህ ፡ በጸጥታ ፡
ለማንም ፡ ተመልካች ፡ ይሰጣል ፡ ደስታ ።

ሕዝቡን ፡ ከተማውን ፡ ማታ ፡ እንዲህ ፡ ሳስተውለው ፤
ባሁኑ ፡ ሰዓት ፡ ነው ፡ ልቤን ፡ ደስ ፡ የሚለው ።

ወታደር ።

አገር ፡ ሲደላደል ፡ መንግሥቱ ፡ ሲረጋ ፡
እያንዳንዱ ፡ ፍጡር ፡ ሳይፈራ ፡ ሳይሠጋ ፡
ጌታን ፡ አመስግኖ ፡ ንጉሡን ፡ አፍቅሮ ፡
በሰላም ፡ ይኖራል ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ኑሮ ።

ንጉሥ ።

ማንኛውም ፡ ንጉሥ ፡ ማንኛውም ፡ መሪ ፡
አገሩን ፡ ሲገዛ ፡ ሆኖ ፡ አስተዳዳሪ ፡
ከመልካም ፡ ነገሮች ፡ ሁሉ ፡ የሚበልጠው ፡
ዋና ፡ ሀብት ፡ ሰላም ፡ ነው ፡ ለሕዝብ ፡ የሚሰጠው ።

ወታደር ።

እውነት ፡ ነው ፡ የቀረው ፡ ሌላ ፡ ሁሉ ፡ ንዋይ ፡
ሠርቶ ፡ ማግኘት ፡ ሆነ ፡ ብልጽግና ፡ ሲሳይ ፡
ዐውቆ ፡ ይከተላል ፡ ሆኖ ፡ ተጨማሪ ።

ንጉሥ ።

በየመንደሮቹ ፡ ተደርጎ ፡ መርማሪ ፡
በከተማ ፡ እንዳይኖር ፡ ወንበዴና ፡ ሌባ ፡
ማስፈተሽ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ በጣም ፡ የሚገባ ።





ወታደር ።

የከተማ ፡ ገዥ ፡ የሚያስፈልገውን ፡
እንደምን ፡ ሳይፈጽም ፡ ይቀራል ፡ እስካሁን ።

ንጉሥ ።

ሥራውን ፡ ተግባሩን ፡ እያከናወነ ፡
ሁሉም ፡ ሠራተኛ ፡ ታታሪ ፡ እየሆነ ፡
የደከመበትን ፡ የሥራውን ፡ ዋጋ ፡
አግኝቶ ፡ የሚኖር ፡ ሳያስብ ፡ ሳይሠጋ ፡
እንዲሆን ፡ እሻለሁ ፡ ሕዝቤ ፡ ባለጸጋ ።

ወታደር ።

ሰላምን ፡ አግኝቶ ፡ ተግቶ ፡ እየሠራ ፡
ሁሉም ፡ የሚጥር ፡ ነው ፡ ደክሞ ፡ የሚሠራ ።

ትርኢት ፡ ፪ ።

ንጉሥ ፡ ኮከብ ፡ ቈጣሪ ፡ ወታደር ፡ ገረድ ።

ገ ረ ድ ።

(ጊዜው ፡ ሌሊት ፡ መሆኑን ፡ ለማስረዳት ፡ ከጣራው ፡ ላይ ፡ ከዋክብት ፡ የተሣሉበት ፡ ትልቅ ፡ ሰሌዳ ፡ ይታያል ። ከመጋረጃው ፡ ውስጥ ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ስትጨነቅ ፡ ድምፅዋ ፡ ይሰማል ። አንድ ፡ ሰው ፡ ከደጅ ፡ ተቀምጧል ፤ ከንዳ ፡ ገረድ ፡ ወደ ፡ እሱ ፡ ትመጣለች) ።

በምጥ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ያሉት ፡ እመየቴ ፡ ሊወልዱ ፤
ሕመም ፡ ጸንቶባቸው ፡ በጭንቅ ፡ ተጎዱ ።

ቶሎ ፡ ረድተዋቸው ፡ እንዲገላገሉ ፡
ፈጥነው ፡ ይነሡና ፡ ላምላኮች ፡ ይሳሉ ።

ኮከብ ፡ ቈጣሪ ።

እንሆ ፡ ፈጥኜ ፡ ተነሣሁኝ ፡ እሺ ፤
አንቺም ፡ አጠገቧ ፡ ሂጂ ፡ ተመለሺ ።

(ሰውዬው ፡ ዕጣን ፡ አጭሶ ፡ ይለምናል) ።

የወንዝ ፡ የተራራ ፡ የጥበብ ፡ የፀሓይ ፡
የእሳት ፡ የነጐድጓድ ፡ የመሬት ፡ የሰማይ ፡
እናንተ ፡ አምላኮች ፡ የዓለም ፡ ሁሉ ፡ ሥልጣን ፡
በእጃችሁ ፡ የሆነ ፡ ይህ ፡ የዛሬው ፡ ሕፃን ፡
ሲወለድ ፡ ዕድሉን ፡ በኮከቦች ፡ ስሻ ፡
እንድትገልጹልኝ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ።
በስለት ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ስማችሁ ፡ ሲጠራ ፡
ግለጹልኝና ፡ ገላግሏት ፡ አደራ ።

(በዕጣኑ ፡ አጠገብ ፡ ሆኖ ፡ ይህንን ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፡ ተቀ ምጦ ፡ ከዋክብትን ፡ ያስተውላል) ።

አንተ ፡ የምሕረት ፡ አምላክ ፡ ይድረስኸ ፡ ጸሎቴ ፡
ማራት ፡ ይቅር ፡ በላት ፡ ተጨነቀች ፡ ሚስቴ ፤
አብረው ፡ ተጠበቡ ፡ ነፍሴና ፡ ሕይወቴ ።

. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

አትማራት ፡ ይቅር ፡ ሚስቴ ፡ አትገላገል ፤
ይቅር ፡ አትማራት ፡ መከራ ፡ ትቀበል ።





. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

እባክኽ ፡ ማርልኝ ፡ ሚስቴ ፡ ተጨነቀች ፤
ምጥ ፡ እያንገላታት ፡ በብዙ ፡ ማቀቀች ።

. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

ይቅር ፡ አትማራት ፡ ምሕረትኽን ፡ መልሰው ፤
አንደዬ ፡ እንደሁ ፡ ተፈጥሯል ፡ ጭንቅና ፡ ሞት ፡ ለሰው ።

. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .

እባክኽ ፡ ማርልኝ ፡ ሚስቴ ፡ ትገላገል ፤
አይተኽ ፡ አትጨክን ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ በደል ።

(የሕፃን ፡ ድምፅ ፡ ተሰማ) ።

ጨክነኽ ፡ አትጨክን ፡ ሰሚ ፡ ነኽ ፡ በርጋታ ፤
ምስጋና ፡ ይድረስኽ ፡ የሰማዩ ፡ ጌታ ።

ትርኢት ፡ ፫ ።

(ንጉሥ ፡ ከኋላው ፡ ወታደሩን ፡ አስከትሎ ፡ መጣ) ።

ን ጉ ሥ ።

እብድ ፡ ነኽ ፡ መሰለኝ ፡ ወይም ፡ ወፈፍተኛ ፤
እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ አዲስ ፡ አማርኛ ፡
ከወዴት ፡ አመጣኽ? ሴቷ ፡ ስትጨነቅ ፡
ሞተች ፡ ዳነች ፡ ሲባል ፡ ታማ ፡ ስትጠበቅ ፡
ቅጥ ፡ በሌለው ፡ ቋንቋ ፡ በወጣ ፡ ከሥራት ፡
እያልኽ ፡ መለመንኽ ፡ ማራት ፡ አትማራት ፡

በምን ፡ ምክንያት ፡ ነው ፤ ምንድነው ፡ ነገሩ ?
አልገባኝም ፡ እኔ ፡ ይህ ፡ ፊሊጥ ፡ ምስጢሩ ።

ኮከብ ፡ ቈጣሪ ።

ቀድሞ ፡ እረ ፡ አንተ ፡ ማነኽ ፡ አላውቅኽ ፡ አታውቀኝ ፤
በምን ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ የምትጠይቀኝ ?

ን ጉ ሥ ።

መንገደኛ ፡ ሰው ፡ ነኝ ፡ ስሄድ ፡ በጕዳና ፡
ሥራኽን ፡ ላይ ፡ መጣሁ ፡ አስደነቀኝና ።
የሠራኸው ፡ ሥራ ፡ በብዙ ፡ ገርሞኛል ፤
አሁንስ ፡ እብድ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ምን ፡ ያሰኛል ።

ኮከብ ፡ ቈጣሪ ።

እኔን ፡ እብድ ፡ ብትል ፡ ለሰሚም ፡ አይበጅ ፤
ትልቅ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ባይገባኽ ፡ ነው ፡ እንጅ ።
ይቺ ፡ ሴት ፡ ሚስቴ ፡ ነች ፡ ምጥ ፡ ይዟት ፡ አይቼ ፡
የኮከብን ፡ ምስጢር ፡ ጥበቡን ፡ አጥርቼ ፡
ዐውቀዋለሁና ፡ እዚህ ፡ ደጅ ፡ ወጥቼ ፡
እመለከታለሁ ፡ በጣም ፡ አስተውዬ ፡
የልጁንም ፡ ዕጣ ፡ በዚህ ፡ ተከትዬ ፤
ሲታየኝ ፡ የኮከብ ፡ መልካም ፡ አካሄድ ፡
ማርልኝ ፡ እላለሁ ፡ ልጁ ፡ እንዲወለድ ፡
አካሄዳቸው ፡ ግን ፡ ሲበላሽ ፡ አይቼ ፡
አትማር ፡ እላለሁ ፡ ልመናዬን ፡ ትቼ ።





ዕድሉ ፡ አምሮለት ፡ ዕጣው ፡ ካልተቃና ፡
ልጁ ፡ ባይወለድ ፡ የሚሻል ፡ ነውና ።

ን ጉ ሥ ።

ማር ፡ አትማር ፡ ስትል ፡ ደንቆን ፡ ነበር ፡ እኛ ፤
ለካ ፡ ብልኅ ፡ ሰው ፡ ነኽ ፡ ተመልካች ፡ ዚቀኛ ፡
ልጁ ፡ ተወለደ ፡ ድምፁንም ፡ ሰማነው ፤
ታዲያስ ፡ መጨረሻ ፡ ዕድሉ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ነው ?

ኮከብ ፡ ቈጣሪ ።

የኮከብ ፡ አዟዟር ፡ ወይም ፡ አቀማመጥ ፡
ለተፀነሰው ፡ ልጅ ፡ ጥሩ ፡ ዕድል ፡ የሚሰጥ ፡
በሆነበት ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ተወለደ ፡
ዕድሉ ፡ ግሩም ፡ ነው ፡ ተቃንቶ ፡ የሄደ ።

ን ጉ ሥ ።

ኮከብ ፡ አቈጣጠር ፡ አለው ፡ ብዙ ፡ ጣጣ ፡
አንተም ፡ በዚህ ፡ በኩል ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ልጅ ፡ ዕጣ ፡
በውነት ፡ ትታያለኽ ፡ ሆነኽ ፡ ጥበበኛ ፤
እስቲ ፡ በል ፡ ንገረን ፡ ተርጕምልን ፡ ለኛ ፡
እንዲህ ፡ ያለ ፡ ጥበብ ፡ ሲሰሙት ፡ ይደንቃል ፤
ታሪኩን ፡ ለማወቅ ፡ ልቤ ፡ ይናፍቃል ።

ኮከብ ፡ ቈጣሪ ።

አንተም ፡ ትመስላለኽ ፡ ጥበቡን ፡ አድናቂ ፤
እኔስ ፡ አይደለሁም ፡ የላቀ ፡ ዐዋቂ ።

ዐውቃለሁ ፡ አልልም ፡ ከሌሎች ፡ አብልጬ ፤
ሆኖም ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፡ ብነግርኽ ፡ ገልጬ ፡
ዳሩ ፡ ግን ፡ ሐተታው ፡ ብዙ ፡ በመሆኑ ፡
ጊዜ ፡ ያልፍብኻል ፡ መሽቷልና ፡ ቀኑ ።

ን ጉ ሥ ።

ምንም ፡ ጊዜው ፡ ቢመሽ ፡ ቢሆንም ፡ ጨለማ ፡
ልቤ ፡ በጣም ፡ ጓጕቷል ፡ ወሬውን ፡ ሊሰማ ።

ኮከብ ፡ ቈጣሪ ።

እንዲህ ፡ የምትጓጓ ፡ ከሆንክ ፡ በውኑ ፡
እንግዲያው ፡ ልንገርኽ ፡ ካልመሸብኽ ፡ ቀኑ ።
ከዩፒቴር ፡ ይዞኽ ፡ ያጽሎ ፡ ያቴና ፡
ያማልክቶቻችን ፡ ገድልና ፡ ዜና ፡
የሥልጣናቸውም ፡ አስደናቂ ፡ ዝና ፡
ውብ ፡ ነው ፡ ትንግርት ፡ ነው ፡ በጣም ፡ ያስደንቃል ፤
ተጽፎ ፡ ተወርቶ ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ መች ፡ ያልቃል ።
በእጃቸው ፡ ነው ፡ ያለ ፡ ምሕረትና ፡ ቍጣ ፤
ሲሳይና ፡ ጥበብ ፡ ቢገኝም ፡ ቢታጣ ፡
ሁሉ ፡ በእነሱ ፡ ነው ፡ የሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ዕጣ ።
እንዳባቶቻችን ፡ እኛም ፡ በዚህ ፡ አምነን ፡
ለነሱ ፡ ተገዝተን ፡ እነሱን ፡ ለምነን ፡
እንኖር ፡ ነበረ ፡ ዛሬ ፡ ግን ፡ በሰማይ ፡
ምስጢር ፡ ልመረምር ፡ ወደ ፡ ኮከቦች ፡ ሳይ ፡





ከዚህ ፡ ከምናምነው ፡ ሁሉ ፡ የበለጠ ፡
እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡ ለኔ ፡ ተገለጠ ።
በቤተ ፡ ልሔም ፡ ውስጥ ፡ ተወልዶና ፡ ኖሮ ፡
በእስራኤል ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ወንጌልን ፡ አስተምሮ ፡
ተሰቅሎ ፡ የሞተው ፡ ክርስቶስ ፡ የሚባል ፡
ይበልጣል ፡ ከሁሉም ፡ ከዩፒቴር ፡ ከበዓል ።
ከነገደ ፡ ዳዊት ፡ የመጣው ፡ ከይሁዳ ፡
ከነዛራቱስትራ ፡ ይበልጣል ፡ ከቡዳ ።
ኮከቡን ፡ አየሁት ፡ ሁሉን ፡ እያጠፋ ፡
እያደገ ፡ ሲሄድ ፡ በጣም ፡ እየሰፋ ።
ሊያጠፋው ፡ የሚችል ፡ ከቶ ፡ እንደማይገኝ ፡
ወንጌል ፡ እንዲያሸንፍ ፡ ተረዳው ፡ እመነኝ ።
በኀይልም ፡ በጥበብ ፡ በሲሳይ ፡ በግርማ ፡
ሥልጣኔያቸው ፡ በልጦ ፡ ካቴና ፡ ከሮማ ፡
ወደ ፡ ፊት ፡ ባለም ፡ ላይ ፡ እያሌ ፡ ነገሥታት ፡
አየሁኝ ፡ ሲነሡ ፡ አንድነት ፡ በብዛት ፡
ሥልጣኔያቸው ፡ ታላቅ ፡ ጥበባቸው ፡ ብዙ ፡
ሆኖም ፡ አየኋቸው ፡ ለወንጌል ፡ ሲገዙ ።

ን ጉ ሥ ።

ምንድነው ፡ ብዬ ፡ ስል ፡ የዚህ ፡ ሕፃን ፡ ዕጣው ፡
ይህን ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ አሁን ፡ ምን ፡ አመጣው ?

ኮከብ ፡ ቈጣሪ ።

ነገሩን ፡ ልጨርስ ፡ አድምጠኝ ፡ ቈይ ፡ እኮ ፡
ይህ ፡ የኛ ፡ ሃይማኖት ፡ ሊሆን ፡ ነው ፡ አምልኮ ፡

የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ምንም ፡ ሳይቸገር ፡
አየሁት ፡ ሲገባ ፡ ወዲህ ፡ ወደኛ ፡ አገር ።
ሳታውቀው ፡ አትቀርም ፡ በዚህ ፡ ባገራችን ፡
ልጅ ፡ የለውም ፡ ነበር ፡ ደጉ ፡ ንጉሣችን ።
አሁን ፡ በቀደም ፡ ለት ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡
ሴት ፡ ልጅ ፡ ተወለደች ፡ ሌሊት ፡ በውድቅቱ ፤
በዚሁም ፡ በወሊድ ፡ ሞተች ፡ ንግሥቲቱ ።
ይህ ፡ የኔ ፡ ሕፃን ፡ ልጅ ፡ ከልዕልቷ ፡ ጋራ ፡
ተጋብቶ ፡ ይነግሣል ፡ በእግዜር ፡ ጥበብ ፡ ሥራ ፡
ከመንገሡም ፡ በፊት ፡ ይማረውና ፡ ዐውቆ ፡
ክርስቲያን ፡ ይሆናል ፡ በወንጌል ፡ ተጠምቆ ።
ከወዴት ፡ ተምሮ ፡ ነው ፡ ወንጌልን ፡ ማወቁ ?
መጋባቱ ፡ እንዴት ፡ ነው? ደግሞስ ፡ መጠመቁ ?
ይህን ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ለማወቅ ፡ ዘርዝሬ ፡
አልቻልሁም ፡ ልረዳው ፡ ሁሉንም ፡ መርምሬ ።
እግዜር ፡ ሁሉን ፡ ነገር ፡ አይገልጥም ፡ ጨርሶ ፡
ድርሻውን ፡ ያስቀራል ፡ ከምስጢር ፡ ቀንሶ ።
ግን ፡ ያየሁት ፡ ነገር ፡ ይደርሳል ፡ አይቀርም ፤
እመነኝ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ አይጠረጠርም ።

## ን ጉ ሥ ።

ካፍኽ ፡ ካንደበትኽ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ሲወጣ ፡
ትንቢት ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ስለዚህ ፡ ልጅ ፡ ዕጣ ፡
ይህን ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ይህንን ፡ ሐተታ ፡
ትርጉሙን ፡ አድርገኽ ፡ እንዲህ ፡ የተፍታታ ፡





ከኮከብ ፡ አዛምደኽ ፡ ስትዘረዝረው ፡
አስበኽ ፡ ነውን ፡ የምትናገረው ?

## ኮከብ ፡ ቈጣሪ ።

አስቤ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከልቤ ፡ እንዴታ !
የምቀልድ ፡ መስሎኽ ፡ አይግባኽ ፡ ቅርታ ።
በግብጽም ፡ በፊንቂ ፡ በአሶር ፡ በባቢሎን ፡
በግሪክ ፡ በሮማ ፡ በፋርስ ፡ በካርታጎን ፡
የነበሩት ፡ ሁሉ ፡ አምላኮች ፡ ተንቀው ፡
በፍጹም ፡ ተረስተው ፡ ይቀራሉ ፡ ወድቀው ።
ሰው ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ሲጽፈው ፡ ተርኮ ፡
ዜናቸውን ፡ ሁሉ ፡ ይለዋል ፡ አምልኮ ፡
ስምም ፡ ሲሰጣቸው ፡ አብሮ ፡ በጠቅላላ ፡
ጣዖት ፡ ይላቸዋል ፡ ሁሉንም ፡ በሞላ ።
የሰማይ ፡ የመሬት ፡ ሥልጣን ፡ ተጠቅልሎ ፡
ላንድ ፡ አምላክ ፡ ይሰጣል ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ ተብሎ ፡
የሚጠራውና ፡ በጣም ፡ የከበረው ፡
ያው ፡ ነው ፡ ሌላ ፡ አይደለም ፡ ወንጌል ፡ ያስተማረው ።
እንግዲህ ፡ ከሰማኽ ፡ ያየሁትን ፡ ሁሉ ፡
አድምጥ ፡ የልጁ ፡ ዕጣ ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ በሙሉ ፤
መልኩ ፡ የተዋበ ፡ ተወዳጅ ፡ ባመሉ ፡
ሁል ፡ ጊዜ ፡ ሆኖለት ፡ መከታ ፡ ጦር ፡ ጋሻ ፡
ዕድል ፡ ይረዳዋል ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡
ላቅመ ፡ አዳም ፡ ሲበቃ ፡ እንዳልኩኽ ፡ ተጋብቶ ፡
እመነኝ ፡ ይነግሣል ፡ ከዙፋን ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ።

ይህ ፡ ያሁኑ ፡ መንግሥት ፡ ለጣዖት ፡ ይሰግዳል ፤
ቦረንትቻ ፡ እያለ ፡ ከብቱን ፡ ለዛፍ ፡ ያርዳል ፡
ኋላ ፡ ግን ፡ የኔ ፡ ልጅ ፡ ባምላክ ፡ ኀይል ፡ ይነግሣል ፡
የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ይነሣል ፤
እስከነ ፡ ምዙራቡ ፡ ጣዖትም ፡ ይፈርሳል ።
አሁን ፡ ተበድሎ ፡ በመሬት ፡ ያዘነ ፡
ነጻነት ፡ ያገኛል ፡ ባንድ ፡ አምላክ ፡ ያመነ ።

ን ጉ ሥ ።

በዚህ ፡ በኛ ፡ መንግሥት ፡ በዚች ፡ በኛ ፡ ሰዓት ፡
እንዴት ፡ ይደረጋል ፡ ይኸ ፡ ሁሉ ፡ መዓት ?
መለፍለፍ ፡ ይባላል ፡ እንዲያው ፡ መቀባጠር ፤
እውነትስ ፡ አይደለም ፡ ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ነገር ።
መቼም ፡ አይፈጸም ፡ የተናገርኸው ፡ ቃል ፤
ክርስቲያን ፡ ባሪያ ፡ ነው ፡ ዘላለም ፡ ይጠቃል ።

ኮከብ ፡ ቈጣሪ ።

እውነት ፡ ነው ፡ ነገሩ ፡ ያሳዝናል ፡ በጣም ፡
ግን ፡ ሁን ፡ ያለው ፡ መጥቶ ፡ ያላለው ፡ አይመጣም ፤
ከታቀደው ፡ መሥመር ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አይወጣም ።
ሰዎች ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ስንኖር ፡ እኛማ ፡
ጥቃቅን ፡ ፍጥረት ፡ ነን ፡ ዐቅማችን ፡ ደካማ ፡
ወይ ፡ አንተ ፡ ወይ ፡ እኔ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ሌላ ፡
እንደ ፡ ምን ፡ ይችላል ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ሊጣላ ?
የእግዚአብሔርም ፡ ፈቃድ ፡ በነቢይ ፡ አንደበት ፡





ወይም ፡ ደግሞ ፡ እንደዚህ ፡ በኮከቦች ፡ ጽሕፈት ፡
ትልቅ ፡ ምስጢር ፡ ሳይቀር ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡
ለሚሻው ፡ ይገኛል ፡ እየተገለጠ ።
የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ለምን ፡ ባለም ፡ መጣ ?
ብለኽ ፡ በመናደድ ፡ በከንቱ ፡ አትቈጣ ።
ብትወድስ ፡ ባትወድስ ፡ ያንተ ፡ አሳብ ፡ ምንድነው ፡
ማን ፡ ሊያስጥል ፡ ይችላል ፡ አምላክ ፡ ሲወስነው ?
ንጉሡም ፡ አይችሉ ፡ እመነኝ ፡ በውነቱ ፤
ይህ ፡ ያየሁት ፡ ነገር ፡ አይምሰልኽ ፡ ከንቱ ።

ን ጉ ሥ ።

ታሪክ ፡ ሰምቻለሁ ፡ ትንቢት ፡ በያይነቱ ፤
እንዲሁም ፡ ይኖራል ፡ ንግር ፡ በየቤቱ ፡
ነገር ፡ ግን ፡ እንደዚህ ፡ በውነት ፡ የሚያስደንቅ ፡
እስተውለው ፡ ሲያስቡት ፡ እጅግ ፡ የሚያስቅቅ ፡
መጥፎ ፡ የተጠላ ፡ መዓተኛ ፡ ወሬ ፡
ከቶ ፡ አልሰማሁም ፡ እኔ ፡ ያለ ፡ ዛሬ ።

ኮከብ ፡ ቈጣሪ ።

ሐሰት ፡ ቃል ፡ አይደለም ፡ የከንቱ ፡ ውዳሴ ፤
ታዘበኝ ፡ ይነቀል ፡ ጠጕር ፡ ከምላሴ ፡
ይህ ፡ ያልሆነ ፡ እንደሆን ፡ እብድ ፡ ነኝ ፡ እውነትም ፤
ነገር ፡ ግን ፡ እመነኝ ፡ እኔ ፡ አልሳሳትም ።
በውነቱማ ፡ ነገር ፡ አሁን ፡ ራሴ ፡ እኔ ፡
እምነቴ ፡ እንዳንተ ፡ ነው ፡ ፍጹም ፡ አረመኔ ፡

የኔ ፡ ልጅ ፡ ቢጠመቅ ፡ በጭራሽ ፡ አልወድም ፤
ግን ፡ ማንም ፡ ኀይለኛ ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ አንድም ፡
ሊያግደው ፡ አይችልም ፡ ከቶ ፡ ምንም ፡ ቢሆን ፡
ይህ ፡ ሁሉ ፡ ይሆናል ፡ ይፈጸማል ፡ አዎን ።

ን ጉ ሥ ።

እንደ ፡ ታዛቢ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ዳኛም ፡ ሆኜ ፡
ሳጠናው ፡ ሳስተውለው ፡ ነገሩን ፡ መዝኜ ፡
እጠራጠራለሁ ፡ እውነት ፡ አይመስለኝም ፤
እንዲህ ፡ የሚያስረዳ ፡ ጥበብ ፡ አይገኝም ።
ቀልድ ፡ ነው ፡ እንዳልል ፡ ነገሩ ፡ በረታ ፤
እውነት ፡ ነው ፡ እንዳልል ፡ ልቤ ፡ አመነታ ።

ኮከብ ፡ ቈጣሪ ።

እንዳይመጣ ፡ ብሎ ፡ የነገር ፡ እንግዳ ፡
ፍጡር ፡ ተደጋግፎ ፡ ባቅሙ ፡ ቢረዳዳ ፡
ምንም ፡ ቢፍጨረጨር ፡ እያጕረመረመ ፡
መጪውን ፡ ቢያግደው ፡ ቀን ፡ እያስቀደመ ፡
እጅግ ፡ ቢጠነቀቅ ፡ ብልኀቱን ፡ ቢያበዛ ፡
አስማተኛን ፡ ሁሉ ፡ በገንዘብ ፡ ቢገዛ ፡
ሕዝብ ፡ ቢተባበር ፡ ነገሥታት ፡ ቢቈጡ ፡
ጠቢባን ፡ ተስማምተው ፡ ሺ ፡ ዘዴ ፡ ቢያመጡ ፡
ወራትና ፡ ዓመታት ፡ ሕጋቸው ፡ ቢናጋ ፡
ዐውደ ፡ ሥርዐታቸው ፡ በውሉ ፡ ባይረጋ ፡
ቀኑም ፡ አልመሽ ፡ ብሎ ፡ ሌሊቱ ፡ ባይነጋ ፡





ጨረቃና ፡ ፀሐይ ፡ ብርሃንን ፡ ቢነሡ ፡
ሰማይና ፡ መሬት ፡ ተጋጭተው ፡ ቢፈርሱ ፡
የተጻፈ ፡ ነገር ፡ አይቀርም ፡ መድረሱ ።
እመነኝ ፡ አይደለም ፡ ከንቱ ፡ መለፍለፍ ፤
ይህ ፡ ሁሉ ፡ ተጽፏል ፡ በሰማይ ፡ መጽሐፍ ፡
ብራናው ፡ ጠፈር ፡ ነው ፡ ፊደሉም ፡ ኮከብ ፤
ቀና ፡ ብለኽ ፡ አንብብ ፡ ትልቁን ፡ መዝገብ ።
ደግሞም ፡ ሩቅ ፡ አይደል ፡ የዚህን ፡ ፍጻሜ ፡
እንደርስበታለን ፡ እኔና ፡ አንተ ፡ በዕድሜ ።

ን ጉ ሥ ።

ወይ ፡ አይፈጸምም ፡ ወይም ፡ ይፈጸማል ፤
በል ፡ ሂድሁኝ ፡ ደኅና ፡ ሁን ፤ ግን ፡ ሥራኽ ፡ ይገርማል ።

ኮከብ ፡ ቈጣሪ ።

እውነት ፡ ተገቢ ፡ ነው ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ቢገረም ፤
ነገር ፡ ግን ፡ ከንቱ ፡ ነው ፡ መቈጣት ፡ ማጕረምረም ።

ትርኢት ፡ ፬ ።

ን ጉ ሥ ።

(ንጉሥ ፡ ለተከተለው ፡ ወታደር) ።

ሰማኽ ፡ ወይ ፡ ይህ ፡ ድኻ ፡ እከካም ፡ ምስኪን ፡
ኮከብ ፡ አየሁ ፡ ብሎ ፡ ያሟረተውን ?

ይህ ፡ ትንቢት ፡ የሚባል ፡ ጉደኛ ፡ ሐተታ ፡
አስተውሎ ፡ ላላየው ፡ ይመስላል ፡ ጨዋታ ።
ይበልጥ ፡ የሚገርመው ፡ ይበልጥ ፡ የሚደንቀው ፡—
ተራ ፡ ሰው ፡ መደዴ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የናቀው ፡
ማንም ፡ ሳይጠረጥር ፡ ሳያስበው ፡ ከቶ ፡
እንዲህ ፡ እንደ ፡ ዋዛ ፡ ከመሬት ፡ ተነሥቶ ፡
የማይቻለውን ፡ በመንፈስ ፡ ሊበገር ፡
እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ የከበደ ፡ ነገር ፡
እየዘረዘረ ፡ አትቶ ፡ ተርጉሞ ፡
ሲናገር ፡ አይፈራም ፡ በጭራሽ ፡ ፈጽሞ ።
ይኸ ፡ ሰው ፡ ሲናገር ፡ በውነት ፡ እንዲህ ፡ ደፍሮ ፡
ልቤ ፡ ተደነቀ ፡ በሰው ፡ ልጅ ፡ ተፈጥሮ ።
ስንቱን ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡ ሽሮ ፡ አፈረሰው !
ስንቱን ፡ ቅዱስ ፡ ነገር ፡ ጥሎ ፡ አረከሰው !
እንደ ፡ ድፍረቱማ ፡ በሞት ፡ በተቀጣ ፡
ታዲያ ፡ ምን ፡ ይሆናል ፡ ይህ ፡ የትንቢት ፡ ጣጣ ፡
ብዙ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እኛ ፡ ብንከፋ ፡
ምናልባት ፡ ይሆናል ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ያላጠፋ ።
ከታየው ፡ ተገልጦ ፡ ያየውን ፡ ቢናገር ፡
እንደ ፡ ምን ፡ ይቀጣል ፡ እሱ ፡ በዚህ ፡ ነገር ?
መስሎ ፡ ቢታየንም ፡ ድፍረቱ ፡ የበዛ ፡
ነገሩን ፡ ሰማነው ፡ እኛም ፡ እንደ ፡ ዋዛ ።
እሱም ፡ የታየውን ፡ በሰፊው ፡ ተረከ ፤
እኔም ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ መንፈሴ ፡ ታወከ ።





ወታደር ።

ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ አይደንቅም ፡ ልማድ ፡ ነው ፡ ነገሩ ፤
እንደዚህ ፡ ይገኛል ፡ እብድ ፡ በያገሩ ፡
እንደዚህ ፡ አድርጎ ፡ በጣም ፡ በመድፈሩ ፡
አንገቱን ፡ አንቄ ፡ ጥዬ ፡ ሳንገላታው ፡
ጥቂት ፡ ቀርቶኝ ፡ ነበር ፡ በጥፊ ፡ ልመታው ።
ንጉሥ ፡ መሆንዎን ፡ እውነት ፡ ቢያውቅ ፡ ኖሮ ፡
ይህ ፡ ጅል ፡ ቀባጣሪ ፡ ቅዠታም ፡ ደንቈሮ ፡
አያወራም ፡ ነበር ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ደፍሮ ።

ን ጉ ሥ ።

ነገሩስ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ አይደለም ፡ የቅዠት ፤
ይህን ፡ የሚናገር ፡ ይዞ ፡ ነው ፡ መሠረት ።
የኮከብን ፡ ምስጢር ፡ ዐውቆ ፡ ለመመርመር ፡
ከኔ ፡ ወዲያ ፡ ብልኅ ፡ አይገኝም ፡ ነበር ፤
ግን ፡ እንዲህ ፡ ዘልቄ ፡ እስከዚህ ፡ ለመፍረድ ፡
አልደረስኩበትም ፡ የዚህን ፡ ሰው ፡ መንገድ ።
ይህ ፡ ነገር ፡ ያሠጋል ፡ በጣም ፡ ያሳስባል ፤
የሱ ፡ ልጅ ፡ የኔን ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ያገባል ?

ወታደር ።

አንደበቱ ፡ ይላል ፡ አሁንም ፡ ደጋግሞ ፡
የማይደረግ ፡ ነው ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ፈጽሞ ።

ን ጉ ሥ ።

አየኸ ፡ አይደለም ፡ ወይ ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ ድፍረት ?

ወታደር ።

አይቼ ፡ ደነቀኝ ፡ ይህን ፡ ከንቱ ፡ ፍጥረት ።

ን ጉ ሥ ።

ምን ፡ ያድርግ ፡ በራእይ ፡ ሲታየው ፡ ተገልጦ ።

ወታደር ።

ዕውቀቱ ፡ ጥበቡ ፡ እሱ ፡ ከማን ፡ በልጦ ።

ን ጉ ሥ ።

አሳብና ፡ ሥጋት ፡ በመንፈሴ ፡ መጣ ።

ወታደር ።

ይገባል ፡ ይኸ ፡ ሰው ፡ ሊታሰር ፡ ሊቀጣ ።

ን ጉ ሥ ።

እሱ ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ቢቀጣ ፡ ቢታሰር ፡
መች ፡ ይለውጠዋል ፡ የትንቢቱን ፡ ነገር ።

ወታደር ።

ሳይገረፍና ፡ ሳይቀጣ ፡ ታስሮ ፡
እንደ ፡ ምን ፡ ይቀራል ፡ ይህንን ፡ ተናግሮ ።

ን ጉ ሥ ።

ይሆናል ፡ አይሆንም ፡ ንግሩ ፡ ትንቢቱ ፡
ይህ ፡ ነው ፡ ዋናው ፡ ነገር ፡ ሌላው ፡ ሁሉ ፡ ከንቱ ።





ወታደር ።

ዐዋቂ ፡ ሰው ፡ መስሎ ፡ እሱ ፡ ቢናገርም ፡
ይፈጸማል ፡ ብዬ ፡ እኔ ፡ አልጠረጥርም ።

ን ጉ ሥ ።

ትንቢቱን ፡ ሲናገር ፡ አፉ ፡ አንደበቱ ፡
የገነነ ፡ ነበር ፡ ኀይለኛና ፡ ብርቱ ።

ወታደር ።

እንዲህ ፡ መለፍለፉ ፡ አፉን ፡ በጣም ፡ ከፍቶ ፡
ምናልባት ፡ እንዳይሆን ፡ ምናምን ፡ ጠጥቶ ።

ን ጉ ሥ ።

ስካርስ ፡ አይዶለም ፡ አፉ ፡ ያስታውቃል ፤
እያደር ፡ ሲያስቡት ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ይደንቃል ።

ወታደር ።

ከየት ፡ እንዳመጣው ፡ ይህንን ፡ ፈጠራ ፡
ሊጠየቅ ፡ ይገባል ፡ በሕግ ፡ ምርመራ ።

ን ጉ ሥ ።

ይህንን ፡ መመርመር ፡ ሞኝነት ፡ ነው ፡ ከንቱ ፡
በኮከብ ፡ ብራና ፡ ተጽፏል ፡ ማለቱ ፤
ለዚህ ፡ አይዶለም ፡ ወይ? ሐሰት ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ሰው ፡
ይገባል ፡ ጥበቡን ፡ ዐውቆ ፡ ሊመልሰው ።

ወታደር ።

የትንቢቱ ፡ ነገር ፡ ቢሆንም ፡ የከፋ ፡
ውሸት ፡ ነው ፡ እላለሁ ፡ የዚህ ፡ ሰው ፡ ልፍለፋ ።

ን ጉ ሥ ።

ውሸት ፡ ቢሆንማ ፡ ምን ፡ እፈልግ ፡ ነበር ፤
ይህ ፡ አልነበረም ፡ ወይ ፡ የምመኘው ፡ ነገር ፡
ብርቱ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የትንቢት ፡ ውሳኔ ፡
እውነት ፡ እንዳይሆን ፡ ነው ፡ የምፈራው ፡ እኔ ።

ወታደር ።

የንጉሥ ፡ አስተያየት ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ እውነት ፡ ነው ፤
ጊዜው ፡ ሲደርስ ፡ ነው ፡ ይህ ፡ የሚታወቀው ።

ን ጉ ሥ ።

መልካም ፡ ቃል ፡ ተናገርክ ፡ ይኸው ፡ አሁን ፡ ገና ፤
በማመዛዘንኽ ፡ ደረስክበት ፡ ደኅና ፡
እውነት ፡ ወይም ፡ ሐሰት ፡ መሆኑን ፡ ለማወቅ ፡
ይገባል ፡ ታግሦ ፡ ጊዜውን ፡ መጠበቅ ፡
እውነት ፡ ሆኖ ፡ ቢገኝ ፡ ይህ ፡ ትንቢት ፡ ምናልባት ፡
ዝም ፡ ብሎ ፡ መስጠት ፡ አይገባም ፡ ሰዓት ።
ጊዜው ፡ ከመድረሱ ፡ በፊት ፡ አስቀድሞ ፡
ዘዴውን ፡ መፈጸም ፡ ያሻል ፡ ተሽቀዳድሞ ።
ያም ፡ ሆነ ፡ ያም ፡ ሆነ ፡ እንኳን ፡ ሰማሁ ፡ ደኅና ፤
ይህን ፡ ሕፃን ፡ ፈጥነኽ ፡ አምጣው ፡ ስረቅና ።





ወታደር ።

እንደ ፡ ምንም ፡ ብዬ ፡ ጥሬ ፡ ተጣጥሬ ፡
ይገኘው ፡ እመጣለሁ ፡ ይህን ፡ ሕፃን ፡ ዛሬ ።

(ወታደር ፡ እያደባ ፡ ገብቶ ፡ ሕፃኑን ፡ ሰርቆ ፡ ሸፍኖ ፡ ያመጣል ፤ ንጉሡም ፡ ሕፃኑን ፡ ተቀብሎ ፡ ጩቤውን ፡ መዞ ፡ ይወጋዋል) ።

ሁለተኛ ፡ ጾታ ።

ትርኢት ፡ ፩ ።

ንጉሥ ፡ ባለሟል ።

ን ጉ ሥ ።

ሕዝቡ ፡ እየሠራ ፡ ሀብቱ ፡ እንዲደረጅ ፡
መንግሥቱ ፡ እንዲጠና ፡ ኍልበትም ፡ እንዲያበጅ ፡
አገሩ ፡ ጸጥታ ፡ ሰላምም ፡ እንዲያገኝ ፡
የማስብ ፡ የምጥር ፡ የምሻ ፡ ንጉሥ ፡ ነኝ ።

ባለሟል ።

እያንዳንዱ ፡ ዜጋ ፡ እያንዳንዱ ፡ አገልጋይ ፡
ይህንን ፡ ዐላማ ፡ ያስፈልጋል ፡ እንዲያይ ።

ን ጉ ሥ ።

ከውስጥም ፡ ከውጭ ፡ እንዳይኖር ፡ ምቀኛ ፡
ሊሆን ፡ ያስፈልጋል ፡ መንግሥቴ ፡ ኀይለኛ ።

ባለሟል ።

ሊፈጠር ፡ ከሚችል ፡ ከውጭ ፡ አደጋ ፡
የውስጥ ፡ ዕንቅፋት ፡ ነው ፡ በጣም ፡ የሚያሠጋ ።

ን ጉ ሥ ።

ለጦርነት ፡ ሆነ ፡ ለሰላምም ፡ ሰዓት ፡
ይገባል ፡ ጠንክረን ፡ በጣም ፡ መሰናዳት ፤
ፍጻሜው ፡ እንዲያምር ፡ ውጤቱ ፡ እንዲቃና ፡
ይህ ፡ ጉዳይ ፡ ይገባል ፡ በሰፊው ፡ ሊጠና ።

ባለሟል ።

ንጉሥ ፡ እንዳሰቡት ፡ ሆኖ ፡ እንዲከናወን ፡
የተዘጋጀን ፡ ነን ፡ ለመሥራት ፡ ሌት ፡ ተቀን ።

ን ጉ ሥ ።

በሁሉም ፡ ረገድ ፡ ለመሆን ፡ ጠንካራ ፡
ያሻል ፡ ሌትና ፡ ቀን ፡ ተግተን ፡ ልንሠራ ።

ባለሟል ።

ላሳብ ፡ ለድካምዎ ፡ ለመሆን ፡ ተካፋይ ፡
ሁሉም ፡ መሥራት ፡ ይሻል ፡ ከጐልበቱ ፡ በላይ ።





ን ጉ ሥ ።

ለሰላማዊ ፡ ሕዝብ ፡ ለጦር ፡ ሰራዊቱ ፡
ለከተማው ፡ ውበት ፡ ደግሞም ፡ ለጽዳቱ ፡

እድገትና ፡ ልማት ፡ ሁሉም ፡ በየክፍሉ ፡
የሚያስፈልገን ፡ ነው ፡ እንዲያገኝ ፡ በሙሉ ።

ባለሟል ።

እውነት ፡ ነው ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ በሙያው ፡ በባህሉ ፡
እድገት ፡ ሊያገኝ ፡ ያሻል ፡ ሁሉም ፡ በየክፍሉ ።

ን ጉ ሥ ።

አገራችን ፡ ስትኖር ፡ በጠላት ፡ ተከባ ፡
ይህንን ፡ ነው ፡ በጣም ፡ ማሰብ ፡ የሚገባ ።

ባለሟል ።

ማስተዋል ፡ መመልከት ፡ ማሰብ ፡ ያስፈልጋል ፤
ይኸ ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ እንዴት ፡ ይዘነጋል ።

ን ጉ ሥ ።

ለሕዝቡ ፡ ላገሩ ፡ ደግሞም ፡ ለመንግሥቱ ፡
የሚበጀው ፡ ነገር ፡ ተደርጎ ፡ ጥናቱ ፡
ቶሎ ፡ ያስፈልጋል ፡ ሊቀርብልን ፡ ለኛ ፤

ባለሟል ።

አገር ፡ ለም ፡ እንዲሆን ፡ መንግሥቱም ፡ ኀይለኛ ፡
ጕዳዩም ፡ ሲፈለግ ፡ እንዲህ ፡ እንዲጠና ፤
መለየት ፡ ይገባል ፡ ዝርዝሩን ፡ ከዋና ።

ን ጉ ሥ ።

ይህ ፡ ነገር ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ይገባል ፡ ማበጠር ፡
ፍሬውን ፡ ከጕድፍ ፡ ከገለባ ፡ ካፈር ።

ባለሟል ።

እንደዚህ ፡ አድርገው ፡ ትእዛዙን ፡ ሲሰጡ ፡
አሉ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ አሳብ ፡ የሚያመጡ ።

ን ጉ ሥ ።

ነጋዴ ፡ በንግዱ ፡ ገበሬውም ፡ በእርሻ ፡
አናጢ ፡ በመጋዝ ፡ ወታደር ፡ በጋሻ ፡
ቀጥቃጭ ፡ በመዶሻው ፡ ፀዋቂ ፡ በጽሕፈት ፡
ሁሉም ፡ እንደ ፡ ሙያው ፡ ይሥራ ፡ በነጻነት ፡
የጥበብ ፡ መጋኛ ፡ ተንኰል ፡ ካገር ፡ ይጥፋ ፡
ይህም ፡ ተፈጽሞ ፡ ሥልጣኔ ፡ እንዲስፋፋ ፡
አገር ፡ እንዲጠቀም ፡ ሕዝብ ፡ እንዳይጐዳ ፡
ምን ፡ ትመክረኛለኽ ፡ ለዚህ ፡ የሚረዳ ?

ባለሟል ።

በዚህ ፡ መልካም ፡ አሳብ ፡ ሕዝብ ፡ እየተመራ ፡
ደክሞም ፡ እንዲጠቀም ፡ ሠርቶም ፡ እንዲያፈራ ፡
ዕንቅፋት ፡ አግኝቶት ፡ ሰው ፡ እንዳይቸገር ፡
ማጥፋት ፡ ያስፈልጋል ፡ ጠንቀኛውን ፡ ነገር ።

ን ጉ ሥ ።

እውነት ፡ ነው ፡ ይህ ፡ ያልኸው ፡ ነገሩ ፡ ገብቶኛል ፤
ጠንቅ ፡ የሌለው ፡ ሥራ ፡ ባለም ፡ የት ፡ ይገኛል ?





የኛማ ፡ ጭቅጭቅ ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ ድካሙ ፤
እንታገላለን ፡ ከፍጥረት ፡ ዓለሙ ።
በስንት ፡ ዐይነት ፡ ልፋት ፡ አንዱን ፡ ስንወጣ ፡
ደግሞ ፡ ያልታሰበ ፡ ይወለዳል ፡ ጣጣ ፡
ርግጥ ፡ ችግር ፡ አለው ፡ ሥራ ፡ በየክፍሉ ፤
ብናመዛዝነው ፡ ሁሉን ፡ በበኩሉ ፡
ሕዝብ ፡ ማስተዳደር ፡ ይብሳል ፡ ከሁሉ ።

ባለሟል ።

ሕዝብን ፡ ማስተዳደር ፡ ያስቸግራል ፡ አዎን ፡
በጣም ፡ ያስፈልጋል ፡ ልበ ፡ ሰፊ ፡ መሆን ።
በሥራ ፡ በጥበብ ፡ ፍጥረት ፡ እንዲራመድ ፡
ሃይማኖት ፡ ነው ፡ እኮ ፡ ዋናው ፡ አውራ ፡ መንገድ ።
ዕንቅፋት ፡ ሲወገድ ፡ ሃይማኖት ፡ ሲቃና ፡
ሕዝቡ ፡ ይራመዳል ፡ በጥበብ ፡ ጐዳና ፡
እያስተሳሰረ ፡ ሕዝቡን ፡ ከመንግሥቱ ፡
አገርን ፡ የሚያደርግ ፡ ሀብታምና ፡ ብርቱ ፡
ሃይማኖት ፡ ነው ፡ እኮ ፡ ዋናው ፡ መሠረቱ ።
ካዲስ ፡ እምነት ፡ ጋራ ፡ እየተዳቀለ ፡
ሃይማኖት ፡ ከጠፋ ፡ ከተመሳቀለ ፡
ዐይነቱ ፡ እየበዛ ፡ ከተቀላቀለ ፡
ተከናውኖ ፡ ሊሄድ ፡ የጥበብ ፡ እርምጃ ፡
እንደ ፡ ምን ፡ ይሆናል ፡ አይመስለኝም ፡ እንጃ ።
የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ በሎቱ ፡ እየገፋ ፡
እንሆ ፡ ተነሣ ፡ አገሩን ፡ ሊያጠፋ ፡

እሱ ፡ ነው ፡ ከሁሉም ፡ በጣም ፡ የሚያሠጋ ፤
አይናቁት ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ይህን ፡ መጥፎ ፡ አደጋ ።
የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ እጅግ ፡ አስቸገረ ፡
ካህኑ ፡ በድብቅ ፡ ሕዝብ ፡ እያስተማረ ፡
በጣም ፡ ሥር ፡ ሰደደ ፡ ጠና ፡ ጠነከረ ።
ካባቶቻችንም ፡ ለያዝነው ፡ እምነት ፡
ይገባል ፡ አጥብቆ ፡ ሊደከምለት ።
የንጉሣችን ፡ ትዕግሥት ፡ ሆኖለት ፡ መከታ ፡
ክርስቲያን ፡ ተመቸው ፡ ሄደ ፡ እየበረታ ።
እንዳላየ ፡ አይተው ፡ ንጉሥ ፡ ሲታገሡ ፡
መውደቁ ፡ አይደለም ፡ ወይ ፡ ሃይማኖት ፡ መፍረሱ ?
እንዲህ ፡ ያለ ፡ አደጋ ፡ ባገር ፡ ላይ ፡ ሲመጣ ፡
መንግሥት ፡ የበረታ ፡ ዐዋጅ ፡ ካላወጣ ፡
ባስፈለገ ፡ ጊዜ ፡ አጥፊው ፡ ካልተቀጣ ፡
በኀይል ፡ አስገድዶ ፡ በጕልበት ፡ ካልሠራ ፡
ጕዳቱ ፡ ታላቅ ፡ ነው ፡ በጣም ፡ የሚያስፈራ ።
ይህን ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ ንጉሥ ፡ እያወቁ ፡
ለምን ፡ ነው ፡ ነገሩን ፡ እንዲህ ፡ የሚንቁ ?
የርስዎን ፡ ደግነት ፡ በማመዛዘኑ ፡
እቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ይመጣል ፡ ካህኑ ።
ከርስዎም ፡ አጠገብ ፡ እየገባ ፡ ደፍሮ ፡
ጕዳዩን ፡ ፈጽሞ ፡ ችግሩን ፡ ተናግሮ ፡
እንሆ ፡ ይኖራል ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ተከብሮ ።
እንዲህ ፡ ከዘለቀ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሁኔታ ፡
የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ በመጥፋቱ ፡ ፈንታ ፡





እያደር ፡ ይጸናል ፡ ሥሩ ፡ መሠረቱ ፡
ደግሞ ፡ ለወደ ፡ ፊት ፡ ያሠጋል ፡ በብርቱ ፡
እንኳንስ ፡ ለሌላ ፡ ለቤተ ፡ መንግሥቱ ።

## ን ጉ ሥ ።

የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ተነሥቶ ፡ እንደ ፡ ዋዛ ፡
ዐውቃለሁ ፡ መች ፡ አጣሁ ፡ ዛሬ ፡ እንደ ፡ ተባዛ ።
ካህኑ ፡ ቂል ፡ መሳይ ፡ አንገቱን ፡ የደፋ ፡
አይታወቅበት ፡ ሃይማኖት ፡ ሲያጠፋ ፡
የሱ ፡ ጦር ፡ ወንጌል ፡ ነው ፡ ልብን ፡ የሚወጋ ፤
ፍጻሜው ፡ ጥምቀት ፡ ነው ፡ ትልቁም ፡ አደጋ ።
ዝም ፡ ብዬ ፡ የማይ ፡ ቸግሮኝ ፡ ነው ፡ እኮ ፤
ሰው ፡ እንዳይጠመቅ ፡ መንፈሱ ፡ ተሰብኮ ፡
ይህን ፡ ተንኰለኛ ፡ የሃይማኖት ፡ መልቲ ፡
እንደ ፡ ምን ፡ እናጥፋው ? በል ፡ ምከረኝ ፡ እስቲ ።

## ባለሚል ።

ምንም ፡ አይሳነው ፡ ንጉሥ ፡ ከወደደ ፤
በብዙ ፡ ያተርፋል ፡ በሰይፍ ፡ የነገደ ።
እስቲ ፡ ተፈቅዶልን ፡ ጀግኖች ፡ ይሰለፉ ፤
ካህኑም ፡ ይታረድ ፡ እስከነ ፡ መጽሐፉ ፡
ኖሯል ፡ ወይ ? እስቲባል ፡ ካለም ፡ እንደምስሰው ፤
የክርስቲያንን ፡ ወገን ፡ በሰይፍ ፡ እንጨርሰው ።
የተጠመቁትም ፡ ይሙቱ ፡ ይቀጡ ፤
በወንጌል ፡ ያመኑ ፡ ይጥፉ ፡ ድምጥማጡ ።

ይቀደድ ፡ ወንጌሉ ፡ በጩቤ ፡ በካራ ፤
ቄሶቹን ፡ ይፍጃቸው ፡ ወታደር ፡ ሳይራራ ፤
ሥጋቸውን ፡ ይብላው ፡ የሰማይ ፡ አሞራ ።
ጭፍሮቼን ፡ ልምራቸው ፡ እኔው ፡ አሰልፌ ፡
የክርስቲያኑን ፡ ወገን ፡ ልግባበት ፡ በሰይፌ ፡
የክርስቲያን ፡ ምልክት ፡ ይሰበር ፡ መስቀሉ ፤
መሣለቂያ ፡ ሆኖ ፡ ይቃጠል ፡ ወንጌሉ ።
በክርስቲያን ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ እናድርግ ፡ ዘመቻ ፤
ታሪኩ ፡ በኛ ፡ አገር ፡ ይሁን ፡ መተረቻ ።
እኔ ፡ ራሴ ፡ ልሥራ ፡ አገር ፡ በማሳደም ፤
ልታጠበው ፡ እጄን ፡ በክርስቲያኖቹ ፡ ደም ።
ይህን ፡ አሳብ ፡ ወደው ፡ ንጉሥ ፡ ካልፈቀዱ ፡
በግድ ፡ ይሄዳሉ ፡ ሥር ፡ እየሰደዱ ።

## ን ጉ ሥ ።

ባገር ፡ ላይ ፡ ዐምፆ ፡ መንግሥት ፡ የበደለ ፡
ቋንቋ ፡ የቈረጠ ፡ ወይ ፡ ነፍስ ፡ የገደለ ፡
ርግጥ ፡ ነው ፡ ይቀጣል ፡ ይሞታል ፡ ተፈርዶ ፤
ይህ ፡ ያንተ ፡ አሳብ ፡ ግን ፡ አይደለም ፡ ተለምዶ ።
ምንም ፡ ንጉሥ ፡ ብሆን ፡ ማንንም ፡ ባልፈራ ፡
እንዴት ፡ ይቻለኛል ፡ ይህንን ፡ ልሠራ ፡
ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ እንዳልሆን ፡ ግፈኛ ፡
አለብኝ ፡ ኅሊና ፡ የሚባለው ፡ ዳኛ ።
ደፍሮ ፡ የሚወቅሠኝ ፡ ምንም ፡ ባይኖር ፡ ዛሬ ፡
ከሞትሁ ፡ በኋላ ፡ ባለም ፡ ላይ ፡ ባገሬ ፡
ታሪኬ ፡ ሲነበብ ፡ ይነቀፋል ፡ ግብሬ ።





ፈላጭ ፡ ቈራጭ ፡ ሆኖ ፡ ፍርድን ፡ የሚያጣራ ፡
ዳኛው ፡ ትውልድ ፡ ነው ፡ ኀይልን ፡ የማይፈራ ።
ያላፈነት ፡ ጭነት ፡ የክፉን ፡ የበጎ ፡
ተሸክሜ ፡ ስቀርብ ፡ ወደ ፡ ታሪክ ፡ ሸንጎ ፡
አንተ ፡ አትረዳኝም ፡ የኔ ፡ ስም ፡ ሲሰደብ ፤
ስለዚህ ፡ ግብራችን ፡ በሰይፍ ፡ አይመደብ ።
ወንጌልን ፡ ለማጥፋት ፡ ሰይፍ ፡ ይዞ ፡ መነሣት ፡
ማራገብ ፡ ያኽል ፡ ነው ፡ ነፋስን ፡ ወደ ፡ እሳት ፡
ኔሮን ፡ ተጨምሮ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቷ ፡
ሮማም ፡ አልቻለች ፡ በጦር ፡ ሰራዊቷ ።
የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ በሰይፍ ፡ አላለቀም ፤
ከጳውሎስ ፡ አናት ፡ ጋር ፡ ተቈርጦ ፡ አልወደቀም ።
እዚያው ፡ ይቀመጡ ፡ ሰይፍና ፡ ጐራዴ ፤
የምታገኝ ፡ ቢሆን ፡ ፈልግ ፡ ሌላ ፡ ዘዴ ።

## ባለሟል ።

ጕልበት ፡ የንጉሥ ፡ ነው ፡ ቅጣት ፡ ለሕግ ፡ አፍራሽ ፤
ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ብልኀት ፡ እኔ ፡ አላውቅም ፡ ጭራሽ ።

## ን ጉ ሥ ።

ይተላለቅ ፡ ብዬ ፡ ፍጥረት ፡ ይተራረድ ፡
እንዴት ፡ ይቻለኛል ፡ ይህንን ፡ ለመፍቀድ ።
ጸንቶ ፡ እንዲደላደል ፡ በልጅጎ ፡ መንግሥቱ ፡
ሊተዳደር ፡ ያሻል ፡ ሁሉም ፡ እንደ ፡ እምነቱ ።
ይህንን ፡ ማለቴ ፡ ወንጌልን ፡ ወድጄ ፡
ትምህርቱን ፡ ስብከቱን ፡ አይደለም ፡ ፈቅጄ ።

ብዙ ፡ ዓመት ፡ የሆነው ፡ አልፎ ፡ የተረሳ ፡
አንድ ፡ ወሬ ፡ ልንገርኽ ፡ በዚህ ፡ የተነሣ ።
በከተማ ፡ ስሄድ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ በማታ ፡
የሰማሁ ፡ መሰለኝ ፡ የሰዎች ፡ ጫጫታ ።
ጊዜው ፡ ወገግ ፡ ያለ ፡ ነበረች ፡ ጨረቃ ፡
አንዲት ፡ ሴት ፡ ስታለቅስ ፡ በወሊድ ፡ ተጨንቃ ፡
ተቀምጦ ፡ ነበረ ፡ ባሏ ፡ ደጅ ፡ አፋ ፡ ላይ ፡
ዐይኖቹን ፡ አቅንቶ ፡ ተክሎ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡
አምላክ ፡ ሚስቴን ፡ ማራት ፡ ይልና ፡ ቈይቶ ፡
መልሶ ፡ አትማራት ፡ ይላል ፡ ተመልክቶ ።
ይህን ፡ ነገር ፡ ቆሜ ፡ ካየሁኝ ፡ በኋላ ፡
ልጁ ፡ ተወለደ ፡ ሚስቱ ፡ ተገላግላ ።
እኔም ፡ ቀረብኩና ፡ ምንድነው ፡ ነገሩ ?
ማራት ፡ አትማራት ፡ ያልኽበት ፡ ምስጢሩ ፡
ብዬ ፡ ብጠይቀው ፡ መለሰ ፡ ሰውዬው ፤
የኮከቦችን ፡ ስልት ፡ አይቼ ፡ አስተውዬው ፡
የሚስማማ ፡ ሲሆን ፡ ከልጁ ፡ ዕድል ፡ ጋራ ፡
ገላግላት ፡ እላለሁ ፡ ሚስቴን ፡ ከመከራ ።
የኮከብ ፡ አካሄድ ፡ ሲሆን ፡ ያልተስማማ ፡
አትማር ፡ እላለሁ ፡ ጸሎቴን ፡ አትስማ ፡
የሚወለደው ፡ ልጅ ፡ ዕጣው ፡ ካልተቃና ፡
ጭራሽ ፡ ባይፈጠር ፡ የሚሻል ፡ ነውና ።
ይህንን ፡ ሲነግረኝ ፡ በጣም ፡ ተገርሜ ፡
አሁንም ፡ መልሼ ፡ ጠየቅሁት ፡ ደግሜ ፤
ሲያለቅስ ፡ ሰማነው ፡ ልጅኽ ፡ ተወለደ ፤
ታዲያ ፡ የጣው ፡ ነገር ፡ በምን ፡ መንገድ ፡ ሄደ ?





እሱም ፡ መለሰልኝ ፡ ዕድሉ ፡ ይቃናል ፤
ከንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ተጋብቶ ፡ ባላልጋ ፡ ይሆናል ፡
ሲነግሥም ፡ በወንጌል ፡ አምኖ ፡ ይጠመቃል ፡
የወጌልም ፡ እምነት ፡ በኛ ፡ አገር ፡ ይጸድቃል ፤
ያሁኑ ፡ ሃይማኖት ፡ ይቀራል ፡ ይረሳል ፤
የሠራነው ፡ መቅደስ ፡ ይዘጋል ፡ ይፈርሳል ።
ምንም ፡ ቢሆን ፡ ከቶ ፡ ይሆናል ፡ ይህ ፡ ነገር ፤
የማይቀር ፡ ነውና ፡ የማይጠረጠር ፡
አለና ፡ ቢነግረኝ ፡ በጣም ፡ ተናድጄ ፡
ደኅና ፡ ሁን ፡ አልኩና ፡ ካጠገቡ ፡ ሄጄ ፡
የተከተለኝን ፡ ወታደር ፡ ሂድና ፡
ይህን ፡ ሕፃን ፡ ሰርቀኽ ፡ ይዘኽ ፡ በቶሎ ፡ና ፡
ብዬ ፡ ስላዘዝሁት ፡ ገብቶ ፡ ተደብቆ ፡
ልጁን ፡ አመጣልኝ ፡ ከተኛበት ፡ ሰርቆ ።
ሆዱን ፡ ወጋሁና ፡ በጩቤ ፡ ቀድጄ ፡
በደም ፡ ተለውሶ ፡ ይታይ ፡ ነበር ፡ እጄ ፡
አውጥቼ ፡ ልጥለው ፡ ልቡን ፡ ልበጥሰው ፡
እጄን ፡ ጨመርሁና ፡ ሆዱን ፡ ስዳስሰው ፡
ይኽው ፡ ወታደሩ ፡ አብሮኝ ፡ የነበረ ፡
ይብቃ ፡ ገድለውታል ፡ በደም ፡ ተነከረ ፡
ይህስ ፡ የማይሆን ፡ ነው ፡ ከልማድ ፡ የወጣ ፤
ባባትዬው ፡ ዐመፅ ፡ ሕፃኑ ፡ ተቀጣ ፡
እንግዲህ ፡ አይድንም ፡ በቶሎ ፡ ይሞታል ፤
በደም ፡ ተነከረ ፡ ይብቃ ፡ ገድለውታል ።
እርስዎን ፡ የመሰለ ፡ መልካም ፡ ንጉሥ ፡ ከቶ ፡
ይህን ፡ የጭካኔ ፡ መጥፎ ፡ ሥራ ፡ ሠርቶ ፡

እንደ ፡ ምን ፡ ይገኛል ፡ ይልቅ ፡ ከዚህ ፡ ይብስ ፡
ወደ ፡ ወንዝ ፡ አውርጀ ፡ ሕፃኑን ፡ በፈረስ ፡
ባሕር ፡ ልወርውረው ፡ አለና ፡ ልጣለው ፡
ተቀበለኝና ፡ በሻሽ ፡ ጠቀለለው ፡
ሬሳውን ፡ ይዞ ፡ እየገሠገሠ ፡
በፈረሱ ፡ ጋልቦ ፡ ጥሎት ፡ ተመለሰ ፤
እኔም ፡ በመግደሌ ፡ የልቤ ፡ ደረሰ ።
ምንም ፡ ቅር ፡ አላለኝ ፡ ልቤም ፡ አላዘነ ፡
ኻያ ፡ ዓመት ፡ ሆኖታል ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ከሆነ ፡
በሃይማኖት ፡ ነገር ፡ ስጨክን ፡ ስቀና ፡
እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ነው ፡ ፍርዴ ፡ የሚጸና ።

ባለሟል ።

እስቲ ፡ በማን ፡ አገር ፡ ድኻ ፡ እንዲህ ፡ ያስባል?
ይህ ፡ የሠሩት ፡ ሥራ ፡ በጣሙን ፡ ይገባል ።
በጣም ፡ ደግ ፡ አረጉ ፡ ይገባል ፡ መጠርጠር ፤
መናቅ ፡ ሞኝነት ፡ ነው ፡ ይህን ፡ መሳይ ፡ ነገር ።

ን ጉ ሥ ።

ይህ ፡ ሰው ፡ የታየውን ፡ ስለ ፡ መናገሩ ፡
እኔ ፡ አልተቈጣሁም ፡ ስላደፋፈሩ ።
ዕውቀቱ ፡ በኮከብ ፡ በጣም ፡ የዘለቀ ፡
መስሎ ፡ ስለ ፡ ታየኝ ፡ አጥርቶ ፡ ያወቀ ፡
እኔም ፡ ስለማልንቅ ፡ ይህን ፡ ዐይነት ፡ ሥራ ፡
ይሆናል ፡ በማለት ፡ ልቤ ፡ በጣም ፡ ፈራ ፡
ስለዚህ ፡ ጨከኜ ፡ ሳላመነታታ ፡
ልጁን ፡ ቶሎ ፡ ማጥፋት ፡ ሆነብኝ ፡ ግዴታ ።





ባለሟል ።

እንዴት ፡ ዝም ፡ ይበሉ ፡ ይህን ፡ እየሰሙ ፡
የሚገባውን ፡ ነው ፡ ንጉሥ ፡ የፈጸሙ ።

ን ጉ ሥ ።

የነገረኝ ፡ ትንቢት ፡ እውነት ፡ ከሆነማ ፡
የሚቀፍ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ በጆሮ ፡ ሲሰማ ።

ባለሟል ።

ስንት ፡ ትንቢት ፡ አለ ፡ ባገር ፡ የሚወራ ፡
ነገር ፡ ግን ፡ ሐሰት ፡ ነው ፡ ሁሉም ፡ የፈጠራ ።

ን ጉ ሥ ።

ክፉ ፡ ባለ ፡ መንፈስ ፡ ሲናገር ፡ ጠንክሮ ፡
ይደንቅኽ ፡ ነበረ ፡ በሰማኽው ፡ ኖሮ ።

ባለሟል ።

መቼስ ፡ ምን ፡ ይደረግ ፡ ድኻም ፡ በበኩሉ ፡
እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ አለው ፡ እንዳመሉ ።

ን ጉ ሥ ።

የቃሉ ፡ ብርቱነት ፡ የድምፁ ፡ ሁናቴ ፡
ዛሬም ፡ ይደቀናል ፡ ይመጣል ፡ ከፊቴ ።

ባለሟል ።

እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ አሟራች ፡ ዚቀኛ ፡
አላገኙትም ፡ ወይ ፡ ቈይተው ፡ ዳግመኛ ?

ን ጉ ሥ ።

አይቼው ፡ አላውቅም ፡ ያንን ፡ ሰው ፡ ፈጽሞ ፡
ቤቱ ፡ የት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ቢጠይቁኝ ፡ ደግሞ ፡
አላስታውሰውም ፡ ጊዜው ፡ የዘገየ ፡
ታሪኩ ፡ ነውና ፡ ያረጀ ፡ የቈየ ።

ባለሟል ።

መልካም ፡ ነገር ፡ ሆነ ፡ ሕፃኑ ፡ መሞቱ ፡
ያሠጋ ፡ ነበረ ፡ እለዚያ ፡ በብርቱ ።

ን ጉ ሥ ።

ልረሳው ፡ ስፈልግ ፡ ነገሩ ፡ ከራሴ ፡
እሺ ፡ ብሎ ፡ አይጠፋም ፡ አለ ፡ በመንፈሴ ፤
ሁል ፡ ጊዜ ፡ ባንጐሌ ፡ ተቀርጾ ፡ ይኖራል ።

ባለሟል ።

እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ መንፈስን ፡ ያሠራል ፡
የማይረሳ ፡ ነው ፡ ካሳብ ፡ የማይጠፋ ።

ን ጉ ሥ ።

እያንዳንዱ ፡ ፍጡር ፡ እንዲኖር ፡ በተስፋ ፡
እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ካሳቡ ፡ ይፈልቃል ፤
ከየት ፡ እንዳገኘው ፡ ለማወቅ ፡ ይጨንቃል ።

ባለሟል ።

ሰው ፡ በሕልም ፡ በንግር ፡ ሲኖረው ፡ አምልኮ ፡
ምኞቱን ፡ ይገልጣል ፡ በትንቢት ፡ አስታኮ ።





ን ጉ ሥ ።

የሰውዬው ፡ ነገር ፡ ባሳቤ ፡ ሲመጣ ፡
አሁንም ፡ አይገባኝ ፡ የዚህ ፡ ትንቢት ፡ ጣጣ ።
ፈጠረው ፡ እንዳልል ፡ ብርቱ ፡ ነበር ፡ ቃሉ ፤
የሚያስደንቅ ፡ ነበር ፡ ሁኔታው ፡ በሙሉ ።

ባለሟል ።

ንጉሥ ፡ እንዲረዱት ፡ ተሸፍኖ ፡ እንዳይቀር ፡
አምላክ ፡ እንዲገለጥ ፡ ፈቀደ ፡ ይህ ፡ ነገር ።

ን ጉ ሥ ።

ታሪኩን ፡ ባልሰማ ፡ በድንገት ፡ ደርሼ ፡
አላውቀውም ፡ ነበር ፡ ነገሩን ፡ ጨርሼ ።

ባለሟል ።

እግዚአብሔር ፡ ነገሩን ፡ እንዲታይ ፡ አድርጎ ፡
የገለጠልዎት ፡ ለመልካም ፡ ለበጎ ፡
መሆኑ ፡ ግልጥ ፡ ነው ፤ እለዚያ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡
ጉዳት ፡ የሚያስከትል ፡ መሆን ፡ ይችል ፡ ነበር ።

ን ጉ ሥ ።

ምንም ፡ ሳልጠረጥር ፡ አጋጥሞኝ ፡ በድንገት ፡
እግዚአብሔር ፡ ገለጠው ፡ እንዲታሰብበት ።

## ትርኢት ፡ ፪ ።

### ንጉሥና ፡ አገረ ፡ ገዥ ።

ን ጉ ሥ ።

በመናገሻችን ፡ በዋናው ፡ ከተማ ፡
ሁል ፡ ጊዜ ፡ ብቀመጥ ፡ ዕውቀቴ ፡ ደካማ ፡
ጐደሎ ፡ ይሆናል ፡ በየዳር ፡ አገሩ ፡
ሥራቸውን ፡ መልካም ፡ ሹሞች ፡ የሚሠሩ ፡
መሆናቸው ፡ እንዴት ፡ ሊታወቅ ፡ ይቻላል ?
ያዩት ፡ ነገር ፡ ሲሆን ፡ ለመፍረድ ፡ ይቀላል ።
ስለዚህ ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ አገር ፡ መጐብኘቴ ፡
ይህንን ፡ አውራጃ ፡ ለማየት ፡ መምጣቴ ።

አገረ ፡ ገዥ ።

ንጉሥ ፡ ሲመጡልን ፡ ደስታና ፡ ክብሩ ፡
ለሁላችንም ፡ ነው ፡ ለሕዝቡም ፡ ላገሩ ፤
ጠቃሚ ፡ ይሆናል ፡ ባይን ፡ መታየቱ ፤
ሊሻሻል ፡ ይችላል ፡ ችግሩ ፡ ጉዳቱ ።
እያንዳንዱም ፡ ዜጋ ፡ ላለው ፡ አቤቱታ ፡
እያመለከተ ፡ ለንጉሥ ፡ በቀጥታ ፡
ውሳኔ ፡ ያገኛል ፡ ሳይውልም ፡ ሳያድር ፡
ይህም ፡ ይረዳዋል ፡ ሲኖርበት ፡ ችግር ።

ን ጉ ሥ ።

መልካም ፡ ነው ፡ እንግዲህ ፡ ሁሉም ፡ በየክፍሉ ፡
ጉዳቱን ፡ ችግሩን ፡ ዘርዝሮ ፡ በሙሉ ፡
እንዲያቀርብ ፡ ይታዘዝ ፤ ዕድልም ፡ ይሰጠው ።





አገረ ፡ ገዥ ።

ባለጉዳይ ፡ ሁሉ ፡ ይኸው ፡ የሚበልጠው ፡
በሰፈር ፡ አለቃው ፡ እየተነገረው ፡
በደል ፡ ቢሠራበት ፡ ደግሞም ፡ ቢቸግረው ፡
ያለበትን ፡ ችግር ፡ ተናግሮ ፡ እያስረዳ ፡
ፍርድ ፡ የጐደለበት ፡ ደግሞም ፡ የተጐዳ ፡
ሰው ፡ ቢኖር ፡ ሁሉንም ፡ ንጉሥ ፡ እያወቁ ፡
ጉዳዩን ፡ መርምረው ፡ መልሱን ፡ ሲያስታውቁ ፡
የሚሰጥ ፡ ይሆናል ፡ ለሕዝቡ ፡ ደስታ ፤
ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ምን ፡ አለ ፡ ውለታ ።

ን ጉ ሥ ።

መልካም ፡ ነው ፡ ያመልክት ፡ ባለጉዳይ ፡ ሁሉ ፡
ሕዝቡም ፡ እንዲረዳው ፡ ነገሩን ፡ በሙሉ ፡
ጉዳዩን ፡ ማመልከት ፡ የሚችል ፡ መሆኑ ፡
ገልጣችሁ ፡ ንገሩት ፡ ይወቅ ፡ ይህንኑ ።

## ሦስተኛ ፡ ጾታ ።

## ትርኢት ፡ ፩ ።

### ንጉሥ ፡ ካህን ፡ ወጣት ፡ ልጅ ፡ ሎሌ ።
### ሎሌ ፡ (ይገባል) ።

የክርስቲያኖች ፡ ካህን ፡ የገዳም ፡ አለቃ ፡
አሲዘው ፡ መጥተዋል ፡ የተሸፈነ ፡ ዕቃ ።
እንሆ ፡ ቆመዋል ፡ ቢችሉ ፡ ሊገቡ ፡
የንጉሥ ፡ ፈቃድ ፡ ቢሆን ፡ በቶሎ ፡ ሊቀርቡ ።

ን ጉ ሥ ።

ግባ ፡ በለው ፡ ይቅረብ ፡ አሁን ፡ በፍጥነት ፤
ለክርስቲያን ፡ ይተርፋል ፡ የኛ ፡ ቸርነት ።

ካህን ፡ (እጅ ፡ ይነሣል) ።

የቸሩ ፡ ጌታችን ፡ ሰፊው ፡ ደግነት ፡
ሲታደል ፡ ይኖራል ፡ ለመላው ፡ ፍጥረት ፤
ክብርም ፡ ስላገኘሁ ፡ ወዲህ ፡ ለመቅረብ ፡
ያመጣሁት ፡ ዕቃ ፡ አስቤ ፡ ከልብ ፡
ለታማኝነቴ ፡ ሆኖልኝ ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡
በጎ ፡ አሳቤን ፡ ይግለጥ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ።

ን ጉ ሥ ።

ተቀብዬኻለሁ ፡ በብዙ ፡ ምስጋና ፡
ምነው ፡ ምን ፡ አገኘኽ ፡ መጣኽ ፡ ወይ ፡ በደኅና ?

(መልኩ ፡ ያማረ ፡ አንድ ፡ ወጣት ፡ ልጅ ፡ ዕቃውን ፡ ያቀር
ባል ፤ ንጉሡም ፡ ትክ ፡ ብሎ ፡ ያየዋል) ።

ካህን ።

መቼም ፡ ላታክት ፡ ነው ፡ ወደዚህ ፡ ስመጣ ፡
አያልቅም ፡ ችግሬ ፡ የኑሮዬ ፡ ጣጣ ፡
ቤቱ ፡ ክርስቲያናችን ፡ በያለበት ፡ ስፍራ ፡
ጥቃትና ፡ በደል ፡ በዛብን ፡ መከራ ።
ሰዎች ፡ ይሰድቡናል ፡ ውሾች ፡ መጡ ፡ እያሉ ፤
ስድቡስ ፡ ምንም ፡ አይደል ፡ ባልጐዳን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡
ነገር ፡ ግን ፡ ሹሞቹም ፡ ያለአግባብ ፡ አጠቁን ፤
ሦስት ፡ እጅ ፡አብልጠው ፡ ነው ፡ ግብር ፡ ሲጠይቁን ፡





ጕዳይም ፡ አግኝቶን ፡ ስንሄድ ፡ ከነሱ ፡
ከፍ ፡ ዝቅ ፡ አድርገው ፡ ሕግ ፡ እያፈረሱ ፡
በሕዝብ ፡ መካከል ፡ ይሰድቡናል ፡ በግፍ ፤
እናንተን ፡ መፍጀት ፡ ነው ፡ በሳትና ፡ በሰይፍ ፡
ብለው ፡ ይዝታሉ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በይፋ ፡
እኛስ ፡ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ አለን ፡ ሙሉ ፡ ተስፋ ፡
ሕዝብዎ ፡ ነንና ፡ ይኸ ፡ ሁሉ ፡ በደል ፡
እንዲቀር ፡ ያርጉልን ፡ ግብሩም ፡ እንዲነቀል ፡
ከስድብ ፡ ኋላ ፡ ነው ፡ ከጥቃት ፡ ከዛቻ ፡
ቀጥሎ ፡ እሚመጣው ፡ ደም ፡ ማፍሰስ ፡ ዘመቻ ።

ን ጉ ሥ ።

ክርስቲያን ፡ ፈሪ ፡ ነው ፡ እሰማለሁ ፡ ሲባል ፡
መሞትን ፡ አትፍሩ ፡ ከገነት ፡ ያገባል ። (በማሾፍ) ።

ካህን ።

እኛ ፡ ለሞታችን ፡ አንፈራም ፡ ጨርሶ ፤
ግን ፡ ነፍስ ፡ የገደለ ፡ የሰው ፡ ደም ፡ አፍስሶ ፡
በመሬት ፡ ፍርድ ፡ እንኳን ፡ ካየነው ፡ ሲቀጣ ፡
እንደ ፡ ምን ፡ ያመልጣል ፡ ከፈጣሪ ፡ ቊጣ ?
ስለዚህ ፡ አንወድም ፡ በኛ ፡ የተነሣ ፡
ሰውን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ቢያገኘው ፡ አበሳ ።
በሐሰተኛ ፡ ፍርድ ፡ ይዘው ፡ እያጕላሉ ፡
እፊቱ ፡ ላይ ፡ ተፍተው ፡ መሬት ፡ እየጣሉ ፡
ገርፈው ፡ አንገላተው ፡ በመስቀል ፡ ሲሰቅሉት ፡
ካመፀኞች ፡ ጋራ ፡ ክርስቶስ ፡ ሲገድሉት ፡
አባቴ ፡ ይቅርታን ፡ ስጣቸው ፡ ይማሩ ፡

አያውቁትምና ፡ ምን ፡ እንደሚሠሩ ፡
ብሎ ፡ ተናገረ ፡ ለክፉ ፡ ሠሪዎቹ ።
ይህን ፡ ተከትለን ፡ እኛም ፡ ወገኖቹ ፡
ግፍ ፡ ለሚሠራ ፡ እንጂ ፡ አናስብም ፡ ለኛ ፡
ይልቅ ፡ በጨካኝ ፡ ሰው ፡ በክፉ ፡ ዐመፀኛ ፡
ተሰድበን ፡ ተንቀን ፡ ውሾችም ፡ ተብለን ፡
ስንሞት ፡ ጥሩ ፡ ነው ፡ ግፍን ፡ ተቀብለን ።
እርስዎ ፡ ካሽከሮችዎ ፡ እስቲ ፡ ለምሳሌ ፡
በጣም ፡ ቢያገለግል ፡ አንድ ፡ ታማኝ ፡ ሎሌ ፡
ይሰጡት ፡ የለም ፡ ወይ ፡ ክብርና ፡ ሽልማት ፡
ቃሉን ፡ በመፈጸም ፡ ትእዛዙን ፡ በመስማት ፡
መሪር ፡ የሆነውን ፡ የክፉን ፡ ሞት ፡ ጽዋ ፡
ደፍሮ ፡ ተቀብሎ ፡ ሕይወቱን ፡ የሠዋ ፡
ታላቅ ፡ እንደሚሆን ፡ የሰማይ ፡ ቤት ፡ ክብሩ ፡
ንጉሥ ፡ አይስቱትም ፡ ግልጽ ፡ ነው ፡ ነገሩ ።

ን ጉ ሥ ።

ይህንን ፡ ሃይማኖት ፡ ብትተዉት ፡ ምነው ፡
ከናንተ ፡ በስተቀር ፤ ማንም ፡ አላመነው ።

ካህን ።

ክፉ ፡ አለመሆኑን ፡ ምግባሩ ፡ ያስረዳል ፤
የፍጡር ፡ መድኀኒት ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ይካዳል ?
የኛ ፡ አምላክ ፡ ደግ ፡ ነው ፡ ከሁሉም ፡ ይበልጣል ፤
ምክሩና ፡ ትምህርቱ ፡ ከማር ፡ ይጣፍጣል ።
እስቲ ፡ ይመልከቱት ፡ ንጉሥ ፡ ያመዛዝኑ ፡
የቀሩት ፡ አምላኮች ፡ ጨካኞች ፡ የሆኑ ፡





መሥዋዕት ፡ ስታቀርቡ ፡ ጸሎት ፡ ስታደርሱ ፡
ሕፃን ፡ እረዱልን ፡ የሰው ፡ ደም ፡ አፍስሱ ፤
ሥሩልን ፡ ይላሉ ፡ የጭካኔ ፡ ሥራ ፤
የኛ ፡ ግን ፡ ደግ ፡ ነው ፡ ለሰው ፡ የሚራራ ።
ለበደላችሁ ፡ ሰው ፡ ይላል ፡ ደግ ፡ ሥሩ ፤
እርስ ፡ በራሳችሁ ፡ ይላል ፡ ተፋቀሩ ፡
ምክሩና ፡ ትእዛዙ ፡ አሳቡ ፡ ልማዱ ፡
ሁል ፡ ጊዜ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ በጣም ፡ ተዋደዱ ፡
የፍቅር ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ የፍጹም ፡ ትሕትና ፤
የሰው ፡ ደም ፡ አፍስሱ ፡ አይለንምና ።

ን ጉ ሥ ፡ (ወደ ፡ ልጁ ፡ እያየ) ።

ደግ ፡ ነው ፡ ሰማሁኸ ፡ ይወገዳል ፡ ጣጣኸ ፤
ይህን ፡ መሳይ ፡ ውብ ፡ ልጅ ፡ ከወዴት ፡ አመጣኸ ?
እንዲህ ፡ ያለ ፡ ወጣት ፡ የሚመስል ፡ አበባ ፡
ክርስቲያን ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ምንም ፡ አይገባ ።
እጅግ ፡ አርጎ ፡ በጣም ፡ መንፈሴ ፡ ወደደው ፤
እኔ ፡ ዘንድ ፡ ይቀመጥ ፡ እባክኸ ፡ ልውሰደው ።

ካህን ።

እውነት ፡ ነው ፡ ይደንቃል ፡ በጣም ፡ ውብ ፡ ነው ፡ መልኩ ፤
ይበልጡን ፡ ይደንቃል ፡ ቢሰሙት ፡ ታሪኩ ።

ን ጉ ሥ ።

አባቱ ፡ ማን ፡ ይሆን ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ አገሩ ?

ካህን ።

ታሪኩን ፡ ያድምጡኝ ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ ነገሩ ፡
እንደ ፡ ልማዳችን ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ሌሊት ፡
ስንጸልይ ፡ አድረን ፡ ማለዳ ፡ በጧት ፡
ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ድንገት ፡ ስንወጣ ፡
የሕፃን ፡ ልጅ ፡ ልቅሶ ፡ ከጕሯችን ፡ መጣ ፤
ኋላም ፡ ብቅ ፡ ብንል ፡ በጨርቅ ፡ ጠቅልለው ፡
ጥለውት ፡ ሄደዋል ፡ ሙዳይ ፡ አስመስለው ።
እኔም ፡ ጐንበስ ፡ ብል ፡ አየሁ ፡ ልብሱን ፡ ዘልቆ ፡
የተኛበት ፡ መሬት ፡ በደም ፡ ተጨማልቆ ፡
ከዚያም ፡ ገለጥኩና ፡ ብመለከት ፡ በጣም ፡
ደግነቱ ፡ ያ ፡ ቀን ፡ ተመልሶ ፡ አይመጣም ፡
ያየሁትን ፡ ነገር ፡ ሳስበው ፡ ያመኛል ፤
ዛሬም ፡ ሳስታውሰው ፡ ያንገፈግፈኛል ።
የሕፃን ፡ አካሉ ፡ በደም ፡ ተጥለቅልቆ ፡
ሆዱንም ፡ አየሁት ፡ ቈስሎ ፡ ተሠንጥቆ ።
ምን ፡ ዐይነት ፡ ጨካኝ ፡ ነው ፡ ይህን ፡ ጕድ ፡ የሠራ ፤
የሚያስለቅስ ፡ ነበር ፡ በጣም ፡ የሚያስፈራ ።
የቈሰለው ፡ ቦታ ፡ ሆዱን ፡ የተበሳው ፡
እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ይታያል ፡ ጠባሳው ።
ደሙን ፡ አጠብሁና ፡ ተጨነቀች ፡ ነፍሴ ፤
በቶሎ ፡ ጋልቤ ፡ ሄጄ ፡ በፈረሴ ፡
አፈናጠጥኩና ፡ አመጣሁ ፡ ወጌሻ ፤
ሕፃኑን ፡ አየና ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ሲሻ ፡
ሰፍቼ ፡ እንዳድነው ፡ ሰማኒያ ፡ ብር ፡ አምጣ ፡





አለዚያ ፡ እንቢ ፡ ብሎ ፡ ተነሣና ፡ ወጣ ።
እኔም ፡ ይዳን ፡ እንጂ ፡ እከፍላለሁ ፡ ብዬ ፡
ደርሶ ፡ የተረፈኝ ፡ ሀብታም ፡ ሰው ፡ መስዬ ፡
ገንዘቡን ፡ ሰጠሁት ፤ እሱም ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡
ወዲያው ፡ ቍስሉን ፡ ሰፍቶ ፡ አከመው ፡ በቶሎ ።
ከዚያም ፡ የእግዜር ፡ ጥበብ ፡ ይደንቃል ፡ በብዙ ፤
እየፋፋ ፡ ሄደ ፡ እያማረ ፡ ወዙ ።
ሞግዚት ፡ ቀጥሬለት ፡ ደሙ ፡ እየታደሰ ፡
ይኸው ፡ እንደሚያዩት ፡ ለዚህ ፡ ወግ ፡ ደረሰ ።
በእግዚአብሔር ፡ ታምር ፡ ነው ፡ ይኸ ፡ ልጅ ፡ የዳነ ፡
ኻያ ፡ ዓመት ፡ መልቶታል ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ከሆነ ።

ን ጉ ሥ ።

እንዲህ ፡ ያለ ፡ ታሪክ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ወሬ ፡
ጕሮዎቼም ፡ አልሰሙ ፡ እኔስ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ።
እውነትም ፡ በብዙ ፡ ይገርማል ፡ ታሪኩ ፤
እንዴት ፡ ያስደንቃል ፡ ቁመቱና ፡ መልኩ ፡
ለኔ ፡ ብትሰጠኝ ፡ እወዳለሁ ፡ በጣም ።

ካህን ።

ከኔ ፡ ጋር ፡ ካልሆነ ፡ ከገዳም ፡ አይወጣም ፡
ደግሞ ፡ ግን ፡ አጥብቀው ፡ ንጉሥ ፡ ከፈቀዱት ፡
እንቢ ፡ ልል ፡ አልችልም ፡ በውነት ፡ ከወደዱት ።
የገዳሙ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉም ፡ ያፈቅሩታል ፡
ልክ ፡ እንደ ፡ ልጃቸው ፡ ይመለከቱታል ፡

መቅረቱን ፡ ሲሰሙ ፡ በጣሙን ፡ ያዝናሉ ፡
ይህንን ፡ ማለቴ ፡ ጠባዩና ፡ ዐመሉ ፡
ተመስጋኝ ፡ መሆኑን ፡ ልናገር ፡ ነው ፡ እንጅ ፡
ጠልቼስ ፡ አይደለም ፡ መስጠት ፡ ይህን ፡ ልጅ ።

ን ጉ ሥ ።

ትእዛዝ ፡ እሰጣለሁ ፡ ጉዳይኽ ፡ እንዲያልቅ ፤
ልጁም ፡ ይቈይና ፡ ጥቂት ፡ ይጠብቅ ።
ሁሉን ፡ አደርጋለሁ ፡ ምንም ፡ አይቸገር ፤
ምንም ፡ አይጐድልበት ፡ አስፈላጊው ፡ ነገር ፡
እንደ ፡ ልጄ ፡ አድርጌ ፡ ይኖራል ፡ በደኅና ፤
በሰማሁት ፡ ታሪክ ፡ አዝኛለሁና ።
እስቲ ፡ ልጠይቅኽ ፡ መልሼ ፡ እንደ ፡ ገና ፡
ማነው ፡ ከናንተ ፡ ደጅ ፡ የጣለው ፡ አምጥቶ ?

ካህን ።

አምጭው ፡ መቼ ፡ ታየ ፡ ማን ፡ ዐወቀው ፡ ከቶ !

ን ጉ ሥ ።

ይህ ፡ የምትነግረኝ ፡ በውነት ፡ አስደናቂ ፤
የሚያስገርም ፡ ጕድ ፡ ነው ፡ እጅግ ፡ አሰቃቂ ።

ካህን ።

ማመን ፡ ያስቸግራል ፡ ሲያስቡት ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ።

ን ጉ ሥ ።

እንዲድን ፡ እንዲተርፍ ፡ እስካሁን ፡ እንዲቈይ ፡
በመፈለጉ ፡ ነው ፡ እግዜር ፡ በመፍቀዱ ።





ካህን ፡

ቍስሉን ፡ ንጉሥ ፡ ቢያዩት ፡ ያለውን ፡ በሆዱ ፡
የማይታመን ፡ ነው ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ዳነ ።

ን ጉ ሥ ፡ (ልጁን ፡ ይጠይቀዋል) ።

የተወለድክበት ፡ ወዴት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡
እስቲ ፡ ልጠይቅኽ ፡ አታውቅም ፡ ወይ ፡ አንተ ?

ወጣት ።

ዐይኔ ፡ ወላጆቼን ፡ ያልተመለከተ ፡
እናቴን ፡ አባቴን ፡ የማላውቅ ፡ ጨርሼ ፡
ፍጹም ፡ ምስኪን ፡ ልጅ ፡ ነኝ ።

ካህን ።

በታምር ፡ ደርሼ ፡

ባላድነው ፡ እኔ ፡ አሳክሜ ፡ ቶሎ ፡
ሞቶ ፡ ይቀር ፡ ነበር ፡ በደም ፡ ተበክሎ ።

ን ጉ ሥ ።

ዘመድኽን ፡ ወገንኽን ፡ ኋላ ፡ በመጠየቅ ፡
እንደ ፡ ምን ፡ አቃተኽ ፡ ለማግኘት ፡ ለማወቅ ?

ወጣት ።

በምን ፡ ዐይነት ፡ መንገድ ፡ እንዴትስ ፡ አድርጌ ፡
ማግኘት ፡ እችላለሁ ፡ እነሱን ፡ ፈልጌ ?
ከሳቸው ፡ በስተቀር ፡ ደግሞም ፡ ከፈጣሪ ፡
ለኔ ፡ አሳዳጊ ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ ሠሪ ።

ምንም ፡ ዘመድ ፡ የለኝ ፡ ጨርሶ ፡ ባለም ፡ ላይ ።

ን ጉ ሥ ።

ሲያስቡት ፡ ይገርማል ፡ በውነት ፡ ያንተ ፡ ጕዳይ ፡
አሁን ፡ ግን ፡ አታስብ ፡ ከልቢ ፡ በመውደድ ፡
እኔ ፡ እሆንኻለሁ ፡ አባትና ፡ ዘመድ ።

ወጣት ።

እግዜር ፡ አልጣለኝም ፡ በፊትም ፡ ካህኑ ፡
እኔን ፡ አሳከመው ፡ እንዲህ ፡ እንዲያድኑ ፡
ዛሬም ፡ ንጉሥ ፡ ለኔ ፡ ዘመድ ፡ እንዲሆኑ ፡
በታምር ፡ አዘዘ ፡ እንሆ ፡ ፈቀደ ።

ካህን ።

በፌቱቢ ፡ ተወግቶ ፡ ሆዱ ፡ ተቀደደ ፡
ከሞተ ፡ በኋላ ፡ በእግዜር ፡ ታምር ፡ ተርፎ ፡
ከዚያች ፡ መጥፎ ፡ ሰዓት ፡ ከዚያች ፡ ደቂቃ ፡ አልፎ ፡
ይኸው ፡ ዛሬ ፡ ደግሞ ፡ ለዚህ ፡ ማዕርግ ፡ በቃ ፡
በውነት ፡ ፈጣሪ ፡ ነው ፡ የዚህ ፡ ልጅ ፡ ጠበቃ ።
ታሪኩን ፡ ሳስበው ፡ በጣም ፡ ይገርመኛል ፡
ላምላክ ፡ የሚሳነው ፡ ምን ፡ ነገር ፡ ይገኛል ?

ን ጉ ሥ ።

በኛ ፡ በሰዎች ፡ ዘንድ ፡ እምነት ፡ ካልጐደለ ፡
ላምላክ ፡ የሚሳነው ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ የለ ።





ካህን ።

ልቤ ፡ እንዳይሠጋ ፡ መንፈሴ ፡ እንዳይፈራ ፡
ከዛሬ ፡ ዠምሮ ፡ ይህን ፡ ልጅ ፡ አደራ ፡
ለንጉሥ ፡ ሰጥቻለሁ ።

ን ጉ ሥ ።

አታስብ ፡ አትሥጋ ፡
ይኸው ፡ እኔን ፡ አምኖ ፡ ከኔ ፡ የተጠጋ ፡
መሆኑን ፡ ዐውቄ ፡ እንደ ፡ ልጄ ፡ አድርጌ ፡
እኔ ፡ አኖረዋለሁ ፡ በክብር ፡ አሳድጌ ።

ትርኢት ፡ ፫ ።

(ካህኑ ፡ ወጣ ፡ ልጁም ፡ አብሮ) ።

ን ጉ ሥ ፡ (ብቻውን) ።

እውነት ፡ ያ ፡ ሰው ፡ ኮከብ ፡ አሳምሮ ፡ ያውቃል ፡
አይደለም ፡ በከንቱ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ።
ይህ ፡ ልጅ ፡ ባለዕጣ ፡ ነው ፡ ላንድ ፡ ዕድል ፡ የታጨ ፡
ቢያመልጥማ ፡ ኖሮ ፡ ልቤ ፡ በተቈጨ ።
አሁን ፡ ግን ፡ ከሱ ፡ ዕጣ ፡ የኔ ፡ ዕጣ ፡ በለጠ ፡
እንዴት ፡ ቍስሉ ፡ ድኖ ፡ ከሞት ፡ አመለጠ ?
ይሁን ፡ እንጂ ፡ አሁንም ፡ ገብቷል ፡ በኔው ፡ እጅ ፡
አንድ ፡ ዘዴ ፡ አላጣም ፡ ለዚህ ፡ የሚበጅ ።
እንዴት ፡ ያቅተኛል ፡ እኔ ፡ እሱን ፡ ለማጥፋት ፡
መዘግየት ፡ መጥፎ ፡ ነው ፡ አሁን ፡ ማንቀላፋት ።
ዛሬ ፡ ነገ ፡ ሳልል ፡ ሳይዘገይ ፡ ሰዓቱ ፡

ትእዛዝ ፡ እሰጣለሁ ፡ እንዲፈጸም ፡ ሞቱ ።
እስቲ ፡ ይህን ፡ ጉዳይ ፡ በረጋ ፡ ኅሊና ፡
ልየው ፡ ላመዛዝነው ፡ በፊት ፡ በጽሙና ።
ሰው ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ቂል ፡ ነው ፡ ሞኝ ፡ ነው ፡ ደካማ ፡
ከስሜቱ ፡ በቀር ፡ ጥበብ ፡ የማይሰማ ።
ስለዚህ ፡ ወጣት ፡ ልጅ ፡ ካባቱ ፡ አንደበት ፡
በድንገት ፡ ደርሼ ፡ የሰማሁት ፡ ትንቢት ፡
እውነት ፡ ይሆን ፡ ብዬ ፡ አምኜ ፡ ባልፈራ ፡
ልገድለው ፡ አስቤ ፡ ያንን ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡
ባልሠራሁ ፡ ነበረ ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ በአእምሮ ፡
ነገሩን ፡ ሲያስተውለው ፡ አሳቤ ፡ መርምሮ ፡
ቂልነት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንዲያው ፡ ሞኝነቴ ፤
አይገባም ፡ ነበር ፡ ይህንን ፡ መፍራቴ ።
እውነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ንግሩ ፡ ትንቢቱ ፡
ልገድለው ፡ ማሰቤ ፡ ሞኝነት ፡ ነው ፡ ከንቱ ።
የእግዚአብሔር ፡ ውሳኔ ፡ ቃሉ ፡ እንዲጸና ፡
ትንቢቱ ፡ ሊፈጸም ፡ ያስፈልጋልና ፤
ብገድለው ፡ ኖሮማ ፡ አሳቤ ፡ ቢቃና ፡
ፈረሰ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ንግሩ ፡ ትንቢቱ ፤
ፈራሽ ፡ ካደረገው ፡ ሰው ፡ በግል ፡ ጉልበቱ ፡
ምኑን ፡ ትንቢት ፡ ሆነ ፡ መወሰኑም ፡ ከላይ ፡
ከፈጣሪ ፡ ጌታ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ከሰማይ ፡
የለውም ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ምንም ፡ ዐይነት ፡ ዋጋ ፡
ከንቱ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ፍጻሜው ፡ ያልረጋ ።
ከእግዚአብሔር ፡ ከሆነ ፡ ትንቢት ፡ የሚሰጠው ፡





አይችልም ፡ ፈጽሞ ፡ ማንም ፡ ሊለውጠው ።
መለወጥ ፡ ካልቻልኩኝ ፡ የጌታን ፡ ውሳኔ ፡
ልጁን ፡ ልግደል ፡ ብዬ ፡ ለምን ፡ ሞከርኩ ፡ እኔ ?
ደግሞስ ፡ ይኸ ፡ ትንቢት ፡ ሐሰት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡
ይህ ፡ ይፈጸም ፡ ብሎ ፡ ጌታ ፡ ካልወሰነ ፡
ውሸት ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ንግሩ ፡ ትንቢቱ ፤
ሥጋቴም ፡ ፍራቴም ፡ ሞኝነት ፡ ነው ፡ ከንቱ ።
ልጁንም ፡ ለመግደል ፡ ማሰብም ፡ መሞከር ፡
እንደዚህ ፡ ከሆነ ፡ ባልተገባኝ ፡ ነበር ።
ስለዚህ ፡ ሳስበው ፡ በመልካም ፡ ኅሊና ፡
በሁለቱም ፡ መንገድ ፡ መች ፡ ያስኬደኛና ።
እውነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብጣጣር ፡ በከንቱ ፡
ሊለወጥ ፡ አይችልም ፡ ንግሩ ፡ ትንቢቱ ።
ውሸት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የትንቢቱ ፡ ነገር ፡
ይህን ፡ ልጅ ፡ ለመግደል ፡ መጣጣር ፡ መሞከር ፡
ሆኖ ፡ ይቈጠራል ፡ ከንቱ ፡ ወንጀል ፡ መሥራት ፤
እኔም ፡ አይገባኝ ፡ ሐሰት ፡ ነገር ፡ መፍራት ።
በሞልካም ፡ ኅሊና ፡ ጉዳዩን ፡ ሳስተውለው ፡
እውነተኛ ፡ ነገር ፡ እንሆ ፡ ይኸ ፡ ነው ።
ዳሩ ፡ ግን ፡ ቢያስተውልም ፡ በመንፈሱ ፡ ፈርዶ ፡
በኅሊና ፡ መንገድ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ መች ፡ ሄዶ ፡
ግብዝ ፡ በመሆኑ ፡ ጠባዩ ፡ ደካማ ፡
የኅሊናን ፡ ብይን ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ አይሰማ ።
አስተዋይነትን ፡ መርጦ ፡ ሳይቀበል ፡
ዘላለም ፡ ይኖራል ፡ ስሜቱን ፡ ሲከተል ።

እኔም ፡ ማመዛዘን ፡ ያዘዘኝን ፡ ጥሼ ፡
ከንቱ ፡ ሞኝነቴን ፡ አሁንም ፡ አድሼ ፡
ስሕተት ፡ ልሠራ ፡ ነው ፡ እዚያው ፡ ተመልሼ ።

(ንጉሥ ፡ ያጨበጭባል ፤ አንድ ፡ አሽከር ፡ ይገባል) ።
(ደብዳቤ ፡ ይጽፋል) ።

ያንን ፡ እንግዳ ፡ ልጅ ፡ ትእዛዝ ፡ እንድሰጠው ፡
በፍጥነት ፡ አስገባው ፡ ወዲህ ፡ ቅረብ ፡ በለው ።

(ልጁ ፡ ይመጣል) ።

በድንገት ፡ አሰብሁኝ ፡ አሁን ፡ አንድ ፡ ነገር ፡
ሕዝብ ፡ ለመቃኘት ፡ ለመጐብኘት ፡ አገር ፡
እንሆ ፡ ከመጣሁ ፡ ወዲህ ፡ ወደ ፡ ገጠር ፡
ብዙ ፡ ወር ፡ ሆኖኛል ፤ አንተ ፡ ግን ፡ በከንቱ ፡
እዚህ ፡ አትጕላላ ፤ እቤተ ፡ መንግሥቱ ፡
ሂድና ፡ ጠብቀኝ ፤ ሁሉንም ፡ አስቤ ፡
እኔ ፡ ለእንደራሴው ፡ ጽፌያለሁ ፡ ደብዳቤ ።
ይህንን ፡ ደብዳቤ ፡ ይዘኽ ፡ በማለዳ ፡
ተነሥተኽ ፡ እንድትሄድ ፡ እዚህ ፡ አትጐዳ ።

## አራተኛ ፡ ጾታ ።

### ትርኢት ፡ ፩ ።

የንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ኀደኛዋ ፡ የወታደር ፡ አለቃ ፡ ወታደር ፡ ወጣት ፡ ልጅ ።

(ሁለት ፡ ልጅ ፡ አገረዶች ፡ ይጫወታሉ) ።





### የንጉሥ ፡ ልጅ ።

እስቲ ፡ ልለምንሽ ፤ ባማረው ፡ ድምፅሽ ፡
ልቤን ፡ ደስ ፡ ይበለው ፡ ዝፈኝ ፡ እባክሽ ፡
የስፍራው ፡ ውብነት ፡ ያበባውም ፡ ቃና ፡
በጣም ፡ የተሰጠ ፡ ስምም ፡ ነውና ።

(ኀደኛዋ ፡ ትዘፍናለች ፤ የንጉሥ ፡ ልጅ ፡ አንድ ፡ የተኛ ፡ ሰው ፡ አይታ ፡ ትመጣለች) ።

በጣም ፡ የተዋበ ፡ መልኩ ፡ ሰውነቱ ፡
እጅግ ፡ የሚያሳዝን ፡ በወጣትነቱ ፡
እጅግ ፡ አስደናቂ ፡ የውበቱ ፡ ነገር ፡
ምሳሌ ፡ የሌለው ፡ ጭራሽ ፡ በዚህ ፡ አገር ፡
አይተን ፡ የማናውቀው ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ከቶ ፡
እኅቴ ፡ አንድ ፡ ጕልማሳ ፡ አየሁኝ ፡ ተኝቶ ።
ደግሞ ፡ ከንጉሥ ፡ ዘንድ ፡ አምጥቷል ፡ ደብዳቤ ፤
ገልጬ ፡ ለማንበብ ፡ ፈልጓል ፡ አሳቤ ።
ምን ፡ አግኝቶት ፡ ይሆን ፤ አባቴ ፡ ከጻፈ ፡
ይኸው ፡ ስጠባበቅ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ አለፈ ።

### ኀ ደ ኛ ዋ ።

አትንኪ ፡ ይቅርብሽ ፡ አድምጪኝ ፡ እኅቴ ፡ ሆይ ፤
በንደራሴው ፡ በኩል ፡ ይደርሰን ፡ የለም ፡ ወይ ?
ሰርቀሽ ፡ ስታነቢ ፡ የደብዳቤውን ፡ ቃል ፡
ይኸ ፡ ሰው ፡ ምናልባት ፡ ከንቅልፉ ፡ ይነቃል ።

የንጉሥ ፡ ልጅ ።

ይቅር ፡ እውነትሽ ፡ ነው ፡ እንግባ ፡ እቤታችን ፤
የሽርሽሩም ፡ ጊዜ ፡ አልፏል ፡ ሰዓታችን ።

(ጥቂት ፡ ከሄዱ ፡ በኋላ) ።

የንጉሥ ፡ ልጅ ።

ይህንን ፡ ደብዳቤ ፡ ሳላይ ፡ ስለ ፡ ቀረ ፡
ልቤ ፡ ምነው ፡ በጣም ፡ ፈራ ፡ ተሸበረ ።
በዘዴ ፡ ቀስ ፡ ብዬ ፡ በብዙ ፡ ጥንቃቄ ፡
ምንም ፡ ቢሆን ፡ አይሆን ፡ ካላየሁ ፡ ሰርቄ ።

(ደብዳቤውን ፡ ከሰውዬው ፡ ደረት ፡ ላይ ፡ ከመያዣው ፡ ውስጥ ፡ አንሥታ ፡ ጥቂት ፡ ፈቀቅ ፡ ብላ ፡ የንጉሡ ፡ ልጅ ፡ ታነባለች) ።

የንጉሥ ፡ ልጅ ።

እኅቴ ፡ ሆይ ፡ ተመልከች ፡ በጣም ፡ ያሳዝናል ፤
የዚህ ፡ ደብዳቤ ፡ ቃል ፡ እንሆ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፤
ይድረስ ፡ ለእንደራሴ ፡ ይህንን ፡ ወረቀት ፡
ይዞልኽ ፡ የመጣ ፡ ይህ ፡ የሚያምር ፡ ወጣት ፡
ጥፋት ፡ ሠርቷልና ፡ በጣም ፡ የበረታ ፡
ቶሎ ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ በፊት ፡ እንደ ፡ ጌታ ፡
አስተናግደውና ፡ በጣም ፡ አቀማጥለው ፤
ኋላም ፡ በማግስቱ ፡ በቶሎ ፡ አስገድለው ።
ደግሞም ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ይኽ ፡ ጉዳይ ፡ ብርቱ ፡
ጻፍልኝ ፡ በፍጥነት ፡ ሲፈጸም ፡ መሞቱ ።





ገ ደ ኛ ዋ ።

ምን ፡ አጥፍቶ ፡ ይሆን ፡ ያሳዝናል ፡ በጣም ፤
የበረታ ፡ ወንጀል ፡ ፀመፅም ፡ አያጣም ።

የንጉሥ ፡ ልጅ ።

ተይ ፡ እንዲህ ፡ አትበይ ፡ ፍርዱ ፡ ሳይጣራ ፤
ምናልባት ፡ ጠላት ፡ ነው ፡ ይህንን ፡ የሥራ ፡
ለሞት ፡ የሚሰጠው ፡ ይህን ፡ መሳይ ፡ ወጣት ፡
ንጉሥ ፡ የሚያስጨክን ፡ የበረታ ፡ ኀጢአት ፡
አይችልም ፡ ሊሠራ ፤ አንድ ፡ ተንኰል ፡ አለ ፤
ንጉሥ ፡ ይሳሳታል ፡ እየተታለለ ።

ገ ደ ኛ ዋ ።

አንቺ ፡ እንደሚመስልሽ ፡ ቢሞኝም ፡ ቢታለል ፡
ይገባል ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ የንጉሥ ፡ ቃል ፡ መቀበል ።
ሰርቀሽ ፡ በማንበብሽ ፡ ጥፋት ፡ ስትሠሪ ፡
ደግሞ ፡ ማን ፡ አረገሽ ፡ ጉዳዩን ፡ መርማሪ ፡
ይልቅስ ፡ እንሂድ ፡ እቦታው ፡ መልሺ ፤
ሰዎች ፡ ያገኙናል ፡ በቶሎ ፡ ተነሺ ።

የንጉሥ ፡ ልጅ ።

ይህ ፡ ልጅ ፡ ቢያሳዝነኝ ፡ የለበትም ፡ ክፋት ፡
እባክሽ ፡ ላድነው ፡ ከታዘዘው ፡ ጥፋት ።

ገ ደ ኛ ዋ ።

ንጉሥ ፡ የላቸውም ፡ ሌላ ፡ ልጅ ፡ ያላንቺ ፤
ስለዚህ ፡ በፍቅር ፡ አባትሽን ፡ ልትረቺ ፡

ይቻልሽ ፡ ይሆናል ፡ ከተገኘ ፡ ዘዴ ፡
ምሕረትን ፡ ካገኘ ፡ የኔም ፡ ነው ፡ ፈቃዴ ።

### የንጉሥ ፡ ልጅ ።

አንቺስ ፡ መች ፡ አጣሽው ፡ ንጉሥ ፡ ይወዱኛል ፡
እጅግ ፡ አለመጠን ፡ በብዙ ፡ ያምኑኛል ፡
ነኝ ፡ ልል ፡ እችላለሁ ፡ የሥልጣን ፡ ተካፋይ ፡
አንድ ፡ ዐይነት ፡ አድርገው ፡ በጣም ፡ ተመሳሳይ ፡
ሁለት ፡ ማኅተም ፡ ነው ፡ ለመንግሥት ፡ ያሠሩ ፡
አንዱን ፡ ለኔ ፡ ሰጥተው ፡ እንዲህ ፡ ተናገሩ ፡
«እኔ ፡ በሕይወቴ ፡ በዚች ፡ ዓለም ፡ ውስጥ ፡
«ምንም ፡ ነገር ፡ የለኝ ፡ ካንቺ ፡ የሚበልጥ ፡
«ይህ ፡ አንደኛው ፡ ማኅተም ፡ በእጅሽ ፡ ይቀመጥ ፡
«የተቸገርሽበት ፡ ነገር ፡ ስታገኚ ፡
«እኔን ፡ በየጊዜው ፡ ከምትለምኚ ፡
«የምትፈልጊውን ፡ ለኔ ፡ ሳታሰሚ ፡
«ማዘዣውን ፡ ጽፈሽ ፡ ማኅተሜን ፡ አትሚ ፡
«ጉዳይ ፡ ሁሉ ፡ ይሁን ፡ በጅሽ ፡ ተፈጻሚ ።
ንጉሡ ፡ ከሰጡኝ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሥልጣን ፡
ይህን ፡ ሰው ፡ ለማዳን ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ዘዴ ፡ አጣን ?
ሌላ ፡ ልጻፍና ፡ በዚህኛው ፡ ፈንታ ፡
አትሜ ፡ ልለውጥ ፡ ቀስ ፡ ብዬ ፡ በርጋታ ፡
ይህን ፡ ግን ፡ አሁኑን ፡ እኔው ፡ በገዛ ፡ እጄ ፡
የፍርዱን ፡ ደብዳቤ ፡ ልጣለው ፡ ቀድጄ ፡
ጥፋትም ፡ ቢያጠፋ ፡ ከእግራቸው ፡ ወድቄ ፡
ባስምረው ፡ ምን ፡ አለ ፡ ይቅርታ ፡ ጠይቄ ።





### ጓ ደ ኛ ዋ ።

እንዲህ ፡ ያለ ፡ ማኅተም ፡ በጅሽ ፡ ከያዝሽማ ፡
ይህ ፡ ዘዴ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ በጣም ፡ የሚስማማ ።
(የንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ደብዳቤ ፡ ጽፋ ፡ ትተካና ፡ የቀድሞውን ፡ ትቀዳለች) ።

### የንጉሥ ፡ ልጅ ።

እንግዴህ ፡ እንሂድ ፡ እንግባ ፡ በቶሎ ፡
ማንም ፡ ሰው ፡ ሳያየን ፡ ድንገት ፡ ብቅ ፡ ብሎ ።

## ትርኢት ፡ ፪ ።

### የወታደር ፡ አለቃና ፡ ወታደር ።

### የወታደር ፡ አለቃ ።

ለቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ለግቢው ፡ ጥበቃ ፡
ሊሆን ፡ ያስፈልጋል ፡ መንፈስህ ፡ የነቃ ።

### ወታደር ።

በግራ ፡ በቀኝም ፡ ማስተዋሌን ፡ ሳልተው ፡
ይመለከታሉ ፡ ዐይኖቼ ፡ ተከፍተው ።

### የወታደር ፡ አለቃ ።

በዚህ ፡ ግቢ ፡ ገብተው ፡ የሚዘዋወሩ ፡
ከውጭ ፡ የመጡ ፡ ሰዎች ፡ እንዳይኖሩ ፡
ሊሆኑ ፡ ይገባል ፡ ዐይኖችኽ ፡ የበሩ ።

ወታደር ።

የጠበቀ ፡ እንዲሆን ፡ የግቢው ፡ ጸጥታ ፡
እመረምራለሁ ፡ እያንዳንዱን ፡ ቦታ ።

የወታደር ፡ አለቃ ።

ይልቁንም ፡ ንጉሥ ፡ በሌሉበት ፡ ጊዜ ፡
ለዘብ ፡ አጠባበቅ ፡ የወጣው ፡ ትእዛዝ ፡
መሆኑን ፡ አትርሳ ፡ ጠንካራና ፡ ብርቱ ።

ወታደር ።

የዘቡ ፡ ጥበቃ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡
ጠንካራ ፡ መሆኑ ፡ አይጠረጠርም ፤
እንኳን ፡ ሰው ፡ ይቅርና ፡ ወፍ ፡ በዚህ ፡ አይዞርም ።

የወታደር ፡ አለቃ ።

አንዳንድ ፡ ወታደሮች ፡ ይህንን ፡ ጥበቃ ፡
ሲሠሩ ፡ አልሆኑም ፡ ተመልካች ፡ ጠንቃቃ ፡
ባለማየታቸው ፡ ግቢውን ፡ ሲቃኙ ፡
ሰዎች ፡ ተይዘዋል ፡ ገብተው ፡ የተገኙ ።
አንተም ፡ ስትፈጽም ፡ ይህን ፡ ብርቱ ፡ ሥራ ፡
በላይም ፡ በታችም ፡ በቀኝም ፡ በግራ ፡
ደኅና ፡ አድርገኽ ፡ ፈትሽ ፤ አስተውለኽ ፡ ተመልከት ፤
ገብቶ ፡ የተገኘው ፡ አሁን ፡ በቀደምለት ፡
እብድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡ የሌለው ፡ አእምሮ ፡
መግባት ፡ የለበትም ፡ ማንም ፡ እዚህ ፡ ደፍሮ ።





ይልቁንም ፡ አሁን ፡ ጊዜና ፡ ሰዓቱ ፡
የሚመጡበት ፡ ነው ፡ ወዲህ ፡ ልዕልቲቱ ።
ስለዚህ ፡ ተመልከት ፡ እየዞርክ ፡ ቃኘው ፤
ንቁ ፡ ወታደር ፡ ነው ፡ አጥፊን ፡ የሚያገኘው ፡
መመልከት ፡ የማይችል ፡ ሰነፉ ፡ ፈዛዛ ፡
ጥበቃው ፡ ከንቱ ፡ ነው ፡ መቃኘቱም ፡ ዋዛ ።
ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ፡ ደንቡን ፡ ተከትዬ ፡
የገለጥኩልኽን ፡ ታስተውላለኽ ፡ ብዬ ።

ወታደር ።

የሰጡኝን ፡ ትእዛዝ ፡ ምንም ፡ ሳይዛባ ፡
እፈጽማለሁኝ ፡ ሁሉን ፡ በሚገባ ።

ትርኢት ፡ ፫ ።

(ወታደሩ ፡ እየተዘዋወረ ፡ ሲፈትሽ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ተኝቶ ፡ ያገኛል) ።

ወታደርና ፡ ወጣቱ ፡ ልጅ ።

ወታደር ።

እዚህ ፡ የተኛኽው ፡ ማነኽ ፡ አንተ ፡ ተነሥ ፤
(ይቀሰቅሰውና ፡ ያስነሣዋል) ።
ልዕልቷ ፡ ሁሉ ፡ ቀን ፡ ነፋስ ፡ ለመናፈስ ፡
በዚህ ፡ አታክልት ፡ ውስጥ ፡ እዚህ ፡ ቦታ ፡ ድረስ ፡
አታውቅም ፡ ወይ ፡ አንተ ፡ እንደምትመጣ ?
እዚህ ፡ የሚገኝ ፡ ሰው ፡ ደግሞ ፡ እንደሚቀጣ ፡
(ወጣቱ ፡ ልጅ ፡ ተነሥቶ ፡ ይቆማል) ።
ጕሮኽ ፡ አልሰማም ፡ ወይ ፡ ትእዛዝ ፡ እንደ ፡ ወጣ ?

ወጣቱ ፡ ልጅ ።

አላውቅም ፡ መኖሩን ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡
ፍጹም ፡ እንግዳ ፡ ነኝ ፡ እኔ ፡ ለዚህ ፡ አገር ።
የንጉሡን ፡ ደብዳቤ ፡ ይዤ ፡ ነው ፡ የመጣሁ ፤
ከንደራሴውም ፡ ዘንድ ፡ የሚያደርሰኝ ፡ አጣሁ ፡
በመንገዱ ፡ ርቀት ፡ ዛለና ፡ ጉልበቴ ፡
ድካም ፡ ተጭኖኝ ፡ ነው ፡ እዚህ ፡ መተኛቴ ።

ወታደር ።

በል ፡ ፍጠን ፡ ና ፡ ቶሎ ፡ አብረን ፡ እንሂድ ፤
እኔ ፡ አደርስኻለሁ ፡ እንደራሴው ፡ ዘንድ ።

(አብረው ፡ ይሄዳሉ ፡ መጋረጃ ፡ ይጣላል) ።

አምስተኛ ፡ ጾታ ።

ትርኢት ፡ ፩ ።

ንጉሥና ፡ ባለሟል ።

ን ጉ ሥ ።

ነፋስ ፡ እያመጣው ፡ ወዲህ ፡ በቀጥታ ፡
አይሰማኽም ፡ ወይ ፡ የዘፈን ፡ ጫጫታ ?

ባለሟል ።

(እጁን ፡ ጕሮው ፡ ላይ ፡ አድርጎ ፡ ያዳምጣል) ።

የጫጫታ ፡ ነገር ፡ ድምፅም ፡ የመሰለ ፡
ለኔ ፡ የሚሰማኝ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ የለ ።





ን ጉ ሥ ።

ጕሮኽ ፡ ቢደክም ፡ ነው ፡ ብታረጅ ፡ በውኑ ፡
እኔ ፡ ይሰማኛል ፡ ሰርገኞች ፡ ሲዘፍኑ ።

ባለሟል ።

ጕሮዬም ፡ ቢደክም ፡ ዕድሜዬም ፡ ቢያረጅ ፡
ምንም ፡ ዘፈን ፡ የለ ፡ መስሎዎት ፡ ነው ፡ እንጂ ።

ን ጉ ሥ ።

ከቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ አግጣጫና ፡ ወገን ፡
በውነት ፡ የሰርግ ፡ ነው ፡ የምሰማው ፡ ዘፈን ።

ባለሟል ።

ባዳምጥ ፡ ብሰማ ፡ በከንቱ ፡ ደከመኝ ፤
ነፋስ ፡ የሚያመጣው ፡ ምንም ፡ ድምፅ ፡ አላገኝ ።

ን ጉ ሥ ።

አሁንማ ፡ በጣም ፡ ዘፈኑ ፡ ተጣርቶ ፡
ድምፁ ፡ እየደመቀ ፡ ይሰማኛል ፡ ጕልቶ ።

ባለሟል ።

አላጣራ ፡ እያለ ፡ ነፋሱ ፡ ያሞኛል ፤
አሁን ፡ ግን ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ለኔም ፡ ይሰማኛል ፤
ግን ፡ ዘፈን ፡ አይደለም ፡ ሌላ ፡ ይመስለኛል ።

ን ጉ ሥ ።

ድምፁስ ፡ የዘፈን ፡ ነው ፡ ነገሩ ፡ ምን ፡ ይሆን ?

ባለሚል ።

ምናልባት ፡ ይኖራል ፡ ሰርግ ፡ በዚህ ፡ ሰሞን ፡
ማንኛውም ፡ ድግስ ፡ ሲኖር ፡ ባንድ ፡ ቦታ ፡
ምክንያት ፡ ያገኛል ፡ ሰዉ ፡ ለጨዋታ ።

ን ጉ ሥ ።

ከሌላ ፡ ዘንድ ፡ ቢሆን ፡ ምን ፡ ቸገረኝ ፡ ነበር ፤
ለኔ ፡ እንደሚመስለኝ ፡ ዳሩ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ነገር ፡
የመጣ ፡ ድምፅ ፡ ነው ፡ ከቤተ ፡ መንግሥቱ ።

ባለሚል ።

ንጉሥ ፡ አያስቡ ፡ ይህንን ፡ በከንቱ ፡
በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ማን ፡ ይዘፍናል ፡ ደፍሮ ፡
የመጣ ፡ ቢሆን ፡ ነው ፡ ስሕተቱ ፡ ከገጠሮ ።

ትርኢት ፡ ፪ ።

ንጉሥ ፡ የንጉሥ ፡ እንደራሴ ፡ አንድ ፡ ሰርገኛ ፡
ልዕልት ፡ ሙሽራ ፡ ኮከብ ፡ ቈጣሪ ፡ ባለሚል ፡ ካህን ፡
ሕዝብ ።

ን ጉ ሥ ።

(ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ሲቃረብ ፡ ሰርገኞች ፡ ሲዘፍኑ ፡
ይሰማል ። አንድ ፡ ሰርገኛም ፡ ይገኛል) ።

ምንድን ፡ ነው ፡ ሽብሩ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ጫጫታ ?

አንድ ፡ ሰርገኛ ።

እንዴት ፡ ንጉሥ ፡ አጡት ፡ ያሁኑን ፡ ደስታ ፤
ይኸው ፡ ዐሥር ፡ ቀን ፡ ነው ፡ ልዕልቲቱ ፡ አግብታ ፤
በሰርግ ፡ ነው ፡ ያለን ።





ን ጉ ሥ ።

ምን ፡ ይቀባጥራል ፤
ይኸ ፡ ጅል ፡ ሰካራም ፡ ምን ፡ ሐሰት ፡ ያወራል ።

ሰርገኛ ።

የስካሩ ፡ ነገር ፡ ምኑ ፡ ተጠይቆ ፤
በጠጅ ፡ በዘፈን ፡ ፍጥረቱ ፡ ተላልቆ ፡
ታላቅ ፡ ሰርግ ፡ ሆኖ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡
በክብር ፡ ተድራ ፡ ይኸው ፡ ልዕልቲቱ ፡
ይበላል ፡ ይጠጣል ፡ ገብቶ ፡ ሰራዊቱ ፡
ጨዋታና ፡ እልልታ ፡ ደስታና ፡ ዘፈን ፡
እጅግ ፡ አርጎ ፡ ሞቆ ፡ ቀልጧል ፡ አለመጠን ።
ስምንት ፡ ቀኑ ፡ ነው ፡ ሲበላ ፡ ሲጠጣ ፤
እኔ ፡ አይቼ ፡ አላውቅም ፡ ሰርግ ፡ እንዲህ ፡ ሲዋጣ ።
ዋሽንትና ፡ ክራር ፡ ማሲንቆ ፡ ከበሮ ፡
ጫጫታው ፡ ሲጨመር ፡ ፍጥረቱ ፡ ቱሳክሮ ፡
ቅልጥ ፡ ያለ ፡ ሆነ ፡ አለፈች ፡ መሬቷ ፤
እንዴት ፡ ዕድላም ፡ ነች ፡ በውነት ፡ ልዕልቲቷ !
ይደንቃል ፡ በብዙ ፡ ዘፈኑም ፡ መብሉም ፤
የሙሽራው ፡ ውበት ፡ ይበልጣል ፡ ከሁሉም ።

ን ጉ ሥ ።

ሰክሮ ፡ ሲለፈልፍ ፡ ይመስላል ፡ ካንገቱ ፤
ከመንገድ ፡ ሳልገባ ፡ እኔ ፡ ባለቤቱ ፡
ይህን ፡ ትልቅ ፡ ጉዳይ ፡ በድፍረት ፡ ወስኖ ፡
የኔን ፡ ልጅ ፡ ማ ፡ ሊድር ? አግቢውስ ፡ ማ ፡ ሆኖ ?

ሰርገኛ ።

ሰርግ ፡ ላይ ፡ ደርሼ ፡ በላሁኝ ፡ ሲበሉ ፡
ደስታ ፡ ልካፈል ፡ ዘለልሁኝ ፡ ሲዘሉ ፡
አብሬ ፡ ጠጣሁኝ ፡ ፍጥረቱ ፡ ሲጠጣ ፡
አልተመራመርሁም ፡ የቀረውን ፡ ጣጣ ።

ን ጉ ሥ ።

እንዴት ፡ ያለ ፡ ፍጡር ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ደፋር ፡
ይችላል ፡ ያለኔ ፡ የኔን ፡ ልጅ ፡ ለመዳር ?

ሰርገኛ ።

ሰርጋቸውን ፡ በላን ፡ ልዕልት ፡ ተዳሩ ፤
እንሆ ፡ ይኸ ፡ ነው ፡ የማውቀው ፡ ነገሩ ፡
ይህ ፡ ውሸት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ንጉሥ ፡ አይጠርጥሩ ።

ን ጉ ሥ ።

ድግስም ፡ ቢደገስ ፡ ሰርግም ፡ ብትበላ ፡
የልጄን ፡ አይደለም ፡ ይሆናል ፡ የሌላ ።

ሰርገኛ ።

ድግሱን ፡ የበላው ፡ ሕዝቡ ፡ ሰራዊቱ ፡
በንጉሥ ፡ አዳራሽ ፡ ነው ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ።

ን ጉ ሥ ።

እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ይሠራል ፡
ያንተን ፡ ነገር ፡ ማመን ፡ በውነት ፡ ይቸግራል ።





ሰርገኛ ።

ንጉሥ ፡ አሁን ፡ ሄዶ ፡ ቢመለከት ፡ ቀርቦ ፡
በግቢው ፡ ይገኛል ፡ ዓለም ፡ ተሰብስቦ ።

ን ጉ ሥ ።

እንዴት ፡ ሊሆን ፡ ቻለ ፡ ይኸ ፡ ነገር ፡ ከቶ ፡
ማነው ፡ የሚነግረኝ ፡ ይህን ፡ አስረድቶ ?
ይህንን ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ለማወቅ ፡ የምሻው ።

ሰርገኛ ።

ዛሬማ ፡ ሊሆነው ፡ ሰርጉ ፡ መጨረሻው ፡
ሲበላ ፡ ሲጠጣ ፡ ሲዘፍን ፡ ሰንብቶ ፡
ልዕልት ፡ ተድረው ፡ ሰርጋቸው ፡ ተበልቶ ፡
ይኸው ፡ ድግሱ ፡ አልቆ ፡ ሰራዊት ፡ ይወጣል ፤
ያሁኑ ፡ ጥያቄ ፡ ምን ፡ ጥቅም ፡ ይሰጣል ?

ን ጉ ሥ ።

ካሳቡ ፡ አፍልቆ ፡ በውሸት ፡ ፈጠራ ፡
ያልሆነውን ፡ ነገር ፡ ቃኝቶ ፡ የሚያወራ ፡
መስለኸ ፡ ትታያለኸ ፡ ሰክሮ ፡ ዘባራቂ ፤
አትመስልም ፡ ነገሩን ፡ አጥርተኸ ፡ ዐዋቂ ።

ሰርገኛ ።

ድግሱን ፡ አብሬ ፡ የበላሁ ፡ የጠጣሁ ፡
ከቤተ ፡ መንግሥትም ፡ አሁን ፡ ነው ፡ የመጣሁ ፡
የተናገርኩትም ፡ ርግጥ ፡ ነው ፡ ነገሩ ፤
ሰርገኛ ፡ መሆኔን ፡ ንጉሥ ፡ አይጠርጥሩ ።

ን ጉ ሥ ።

ሆኖብኛልና ፡ ንግግርኽ ፡ ግራ ፤
እንደራሴው ፡ መጥቶ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ይጣራ ።

ትርኢት ፡ ፪ ።

(እንደራሴው ፡ ተጠርቶ ፡ ይገባል) ።

ን ጉ ሥ ።

አልገባኝም ፡ እኔ ፡ ምንድነው ፡ ዘፈኑ ፤
በሰርግ ፡ አገባች ፡ ወይ ፡ የኔ ፡ ልጅ ፡ በውኑ ?

እንደራሴ ።

በጸፋት ፡ ደብዳቤ ፡ በላኩት ፡ ውሳኔ ፡
የንጉሡን ፡ ትእዛዝ ፡ ፈጽሚያለሁ ፡ እኔ ።

ን ጉ ሥ ።

ነገሩን ፡ ዘርዝረኽ ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡
እስቲ ፡ ግለጥልኝ ፡ አስረዳኝ ፡ በሙሉ ።

የንጉሥ ፡ እንደራሴ ።

እውነት ፡ ነው ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ መልክተኛ ፡
ከንጉሥ ፡ ተልኮ ፡ ሲመጣ ፡ ወደኛ ፡
ካታክልት ፡ ተኝቶ ፡ አገኘው ፡ ዘበኛ ።
ከተኛበት ፡ ቦታ ፡ ቀስቅሶ ፡ አስነሥቶ ፡
ስለ ፡ መገኘቱ ፡ በዚያ ፡ ቦታ ፡ ገብቶ ፡
ትቀጣለኽ ፡ ብሎ ፡ ቢይዘው ፡ በጥፋት ፡
እንግዳ ፡ መሆኑን ፡ ደግሞ ፡ በዚያ ፡ ሰዓት ፡





ልዕልት ፡ መውጣቷን ፡ ነፋስ ፡ ለመቀበል ፡
ደንብ ፡ መኖሩንም ፡ ሰው ፡ እንዲከለከል ፡
ከቶ ፡ አለማወቁን ፡ ደክሞት ፡ መተኛቱን ፡
ከንጉሥ ፡ ተልኮ ፡ ደብዳቤ ፡ ማምጣቱን ፡
ወደኔ ፡ እሚያደርሰው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ማጣቱን ፡
ተናግሮ ፡ ቢያስረዳ ፡ ዘበኛውም ፡ ደግሞ ፡
አይቶ ፡ እንደማያውቀው ፡ ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡
ሁኔታውም ፡ ደግሞ ፡ እውነተኛ ፡ እንግዳ ፡
አዲስ ፡ መልክተኛ ፡ መሆኑን ፡ ቢረዳ ፡
መልክቱን ፡ ለማድረስ ፡ ወደኔ ፡ ይዞት ፡ መጣ ፤
እኔም ፡ በጥፋቱ ፡ አልቻልሁም ፡ ልቄጣ ።
ጉዳዩን ፡ በቶሎ ፡ ለማወቅ ፡ ሠግቼ ፡
ከተቀመጥኩበት ፡ ቶሎ ፡ ተነሥቼ ፡
የንጉሡን ፡ ደብዳቤ ፡ ወዲያው ፡ ተመልክቼ ፡
የደብዳቤውን ፡ ቃል ፡ አድርጌ ፡ መሠረት ፡
ግዴታ ፡ ሆኑብኝ ፡ ፈጽሜ ፡ መገኘት ።
በሰርግ ፡ ነው ፡ ያለን ፡ ልዕልቲቱን ፡ ድሬ ፤
ጋብቻው ፡ ከሆነ ፡ ሳምንት ፡ ነው ፡ ዛሬ ።
እንሆ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ የንጉሡ ፡ ደብዳቤ ፤

(ወረቀቱን ፡ ከኪሱ ፡ ያወጣል) ።

ይህ ፡ ወጣት ፡ የኔን ፡ ልጅ ፡ እንዲያገባ ፡ አስቤ ፡
ልኬዋለሁና ፡ ሰርጉ ፡ ተደግሶ ፡
ድግሱም ፡ ተፋጥኖ ፡ በሦስት ፡ ቀን ፡ ደርሶ ፡
ይፈጸም ፡ ጋብቻው ፡ እኔን ፡ አትጠብቁ ፤
ይህ ፡ ጉዳይ ፡ አስቸኳይ ፡ መሆኑን ፡ ዕወቁ ።

እንሆ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ደጋግሜ ፡ አይቼ ፤
ነገሩ ፡ ከንክኖኝ ፡ እኔ ፡ እንኳ ፡ ፈርቼ ፡
ዋኖቹን ፡ መሳፍንት ፡ በቶሎ ፡ ሰብስቤ ፡
ገልጬ ፡ አሳየሁኝ ፡ ይህንን ፡ ደብዳቤ ፤
ሁሉም ፡ እንዲነግሩኝ ፡ እንደሚታያቸው ፡
ምን ፡ ይበጃል ፡ ብዬ ፡ ምክር ፡ ጠየቅኋቸው ፤
እነሱም ፡ አንብበው ፡ እንሆ ፡ ማኀተሙ ፤
አንተ ፡ ምን ፡ አስፈራኽ ፡ ትእዛዝ ፡ መፈጸሙ ?
ደብዳቤው ፡ ጕልሕ ፡ ነው ፡ ቃሉ ፡ የተጣራ ፤
ምን ፡ አገኘኽበት ፡ እስቲ ፡ የሚያስፈራ ፡
ብለው ፡ ቢናገሩ ፡ ምንም ፡ ባመነታ ፡
ትእዛዙን ፡ መፈጸም ፡ ሆነብኝ ፡ ግዴታ ።

(ንጉሡ ፡ ወረቀቱን ፡ ተቀብሎ ፡ ይመለከታል) ።

ን ጉ ሥ ።

መንገዱ ፡ ራቀና ፡ ጊዜው ፡ ግን ፡ አጠረ ፤
እደርሳለሁ ፡ ብዬ ፡ መጥቼ ፡ ነበረ ።
ቃሉን ፡ መፈጸምኽ ፡ አድርጊኻል ፡ ደኅና ፤
ይምጡ ፡ ሰርገኞቹ ፡ አስጠራቸውና ።

ትርኢት ፡ ፫ ።

(ልዕልቲቱ ፡ ገባች ፤ የቀሩት ፡ ወጡ) ።

የንጉሥ ፡ ልጅ ።

አባቴ ! አንድ ፡ ቀን ፡ ባታክልቱ ፡ ስፍራ ፡
ልናፈስ ፡ ወጥቼ ፡ ከወዳጄ ፡ ጋራ ፡





የርስዎን ፡ ደብዳቤ ፡ ከደረቱ ፡ ከትቶ ፡
አንድ ፡ ሰው ፡ አገኘሁ ፡ ከዛፍ ፡ ሥር ፡ ተኝቶ ።
ወሬዎን ፡ ልሰማ ፡ እርስዎን ፡ ናፍቄ ፡
አሰብሁ ፡ ደብዳቤውን ፡ ላነበው ፡ ሰርቄ ።
ጕዳዩን ፡ ስረዳ ፤ ኋላም ፡ ተመልክቼ ፡
በጥልቃዊ ፡ ስሜት ፡ በጣም ፡ ተመትቼ ፡
ከርኅራኄ ፡ ጋራ ፡ ፍቅር ፡ ተቀላቅሎ ፡
በጣም ፡ አስጨነቀኝ ፡ ልቤን ፡ አመሳቅሎ ።
ከመሞት ፡ ላድነው ፡ ፈልጌ ፡ አንድ ፡ ዘዴ ፡
መንፈሴ ፡ ተነሣ ፡ አልችል ፡ አለ ፡ ሆዴ ።
ትእዛዙን ፡ ለውጬ ፡ ደብዳቤ ፡ ስተካ ፡
የማይገባኝን ፡ ደፍሬ ፡ ስነካ ፡
ዐውቃለሁ ፡ አምናለሁ ፡ ባለመከራከር ፡
ጥፋቴ ፡ ብርቱ ፡ ነው ፡ በጋብቻው ፡ ነገር ።
እጇ ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ ቃሉን ፡ እንደ ፡ ጻፈ ፡
ምንም ፡ አልታወቀኝ ፡ ነገሩ ፡ ካለፈ ፡
ከሆነ ፡ ወዲያ ፡ ነው ፡ የታየኝ ፡ ጥፋቴ ፤
የተገለጠልኝ ፡ በሙሉ ፡ ስሕተቴ ።
የጸጸቴ ፡ ብዛት ፡ አሳጣኝ ፡ መድረሻ ፤
ዳሩ ፡ ምን ፡ ይሆናል ፡ ቢያዝኑ ፡ መጨረሻ ፤
ያከተመ ፡ ነገር ፡ የለውም ፡ ማደሻ ።
ለቃል ፡ ለማኅተሙ ፡ ለበደል ፡ ለሰርጉ ፡
ለጥፋቴ ፡ ሁሉ ፡ ምሕረትን ፡ ያድርጉ ፤
ለወንጀለኛውም ፡ ጥፋቱ ፡ ለጸና ፡
ምሕረትን ፡ ያድርጉ ፡ በሙሉ ፡ ልቡና ፤
ልጅዎ ፡ በድዬ ፡ አዝኛለሁና ።

ን ጉ ሥ ።

የማንም ፡ አይደለ ፡ ጥፋቱ ፡ ስሕተቱ ፤
በዚህ ፡ የተነሣ ፡ አትዘኝ ፡ በከንቱ ፡
ገና ፡ ሳትወለጅ ፡ በፊት ፡ አስቀድሞ ፡
በእግዚአብሔር ፡ ኀሊና ፡ ሁሉም ፡ ተፈጽሞ ፡
ዕጣችን ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ሲወሰን ፡ ሲቀባ ፡
ያርባ ፡ ቀን ፡ ዕድልሽ ፡ በመዝገብ ፡ ሲገባ ፤
በኮከብ ፡ ፊደሎች ፡ በጠፈር ፡ ብራና ፡
ተጽፎ ፡ ታትሞ ፡ ውሳኔው ፡ ሲጸና ፡
እንዲህ ፡ ይሁን ፡ ብሎ ፡ ባደላዳይ ፡ ግብሩ ፡
አምላክ ፡ ሲወስን ፡ ነው ፡ ያለቀው ፡ ነገሩ ።
ይምጡ ፡ ሰርገኞቹ ፡ እዚህ ፡ ይሰብሰቡ ፤
አንድ ፡ ሰው ፡ እንዳይቀር ፡ ሁሉም ፡ አብረው ፡ ይግቡ ።

ትርኢት ፡ ፩ ።

(ሁሉም ፡ ተሰበሰቡ) ።

ን ጉ ሥ ።

ከልብ ፡ ሆናችሁ ፡ አድምጡኝ ፡ ልጆቼ ፡
እንዲሁም ፡ ሁላችሁ ፡ እናንተ ፡ ሕዝቦቼ ፡
አንተ ፡ የታደልኸው ፡ መልካሙ ፡ሙሽራ ፡
ለዚህ ፡ አደረሰኸ ፡ ያምላክ ፡ ጥበብ ፡ ሥራ ።
እሱም ፡ አባትኸ ፡ ነው ፡ ወላጅኸ ፡ በሥጋ ፤
(አባቱን ፡ ያሳየዋል) ።
ከሌሊት ፡ ዝምሮ ፡ ውድቅቱ ፡ ሳይነጋ ፡
እኔ ፡ ገዳይኸ ፡ ነኝ ፡ አሳዳጅ ፡ ባላንጣኸ ፤





ከሞት ፡ ከመቃብር ፡ በታምር ፡ ያወጣኸ ፡
የመንፈስ ፡ አባትኸ ፡ ቄሱ ፡ ነው ፡ ካህኑ ፤
የእግዜር ፡ መሣሪያ ፡ ነኸ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ በውኑ ።
እዚህ ፡ ላለው ፡ ፍጥረት ፡ ለሕዝቡ ፡ በሞላ ፡
ልናገር ፡ ልመስክር ፡ አሁን ፡ በጠቅላላ ፡
ላንተ ፡ ግን ፡ በሰፊው ፡ ዘርዝሬ ፡ በኋላ ፡
ነገሩን ፡ ማስረዳት ፡ ይገባኛል ፡ ገና ፤
የራስኽን ፡ ታሪክ ፡ አታውቀውምና ።

ወጣት ፡ ልጅ ።

እጅግ ፡ አለመጠን ፡ በብዙ ፡ ይገርማል ፤
ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ነገር ፡ እንዴት ፡ ይፈጸማል ?
የንጉሥ ፡ ልጅ ፡ አግብቼ ፡ ይህን ፡ ክብር ፡ ላገኘው ፡
እንኳንስ ፡ በውኔ ፡ በልሜም ፡ አልመኘው ።
ወደው ፡ ሲድሩልኝ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ልጅዎን ፡
እንዴት ፡ ይችላሉ ፡ ደመኛዬ ፡ መሆን ?
እሱስ ፡ እንዴት ፡ አርጎ ፡ ይሆናል ፡ አባቴ ፡
እኔ ፡ ዘመድ ፡ አላውቅ ፡ በሙሉ ፡ ሕይወቴ ፤
ይህ ፡ ሁሉ ፡ በውኔ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ በቅዠቴ ?
የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ ፡ ከማየት ፡ በስተቀር ፡
ምንም ፡ አይገባኝም ፡ ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ነገር ።

ን ጉ ሥ ።

ምን ፡ ሊገባኸ ፡ ይቻል ፡ እግዚአብሔር ፡ ባበጀው ፡
አለማወቅኸ ፡ ነው ፡ ደግሞም ፡ የሚበጀው ።
ሕዝቡም ፡ መኳንንቱም ፡ እንዲያውቁት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡
እኔ ፡ ግን ፡ ልናገር ፡ የልቤን ፡ ኑዛዜ ።

ሐሰት ፡ በሌለበት ፡ በሙሉ ፡ ልቡና ፡
እግዚአብሔር ፡ ለሠራው ፡ ምስክር ፡ ነኝና ።
አገር ፡ እገዛለሁ ፡ ኀይለኛ ፡ ንጉሥ ፡ ነኝ ፤
ነገር ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ ለማጥፋት ፡ ተሳነኝ ።
ክርስቲያንን ፡ ሊደግፍ ፡ እግዚአብሔር ፡ አስቦ ፡
የጥበቡን ፡ ሥራ ፡ አጣምሮ ፡ ተብትቦ ፡
በዚያም ፡ በዚህ ፡ ብሎ ፡ ይህን ፡ ልጅ ፡ አዳነ ፤
ከልጄም ፡ ተጋብቶ ፡ ይኸው ፡ አማች ፡ ሆነ ።
ሊታገል ፡ አልልም ፡ እኔ ፡ ከዚህ ፡ ሌላ ፡
እንዴት ፡ ይቻለኛል ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ልጣላ ?
በላይኛው ፡ መዝገብ ፡ በውነት ፡ ከተጻፈ ፡
የምድሩ ፡ ቀሪ ፡ ነው ፡ እየተሸነፈ ።
እስቲ ፡ ተመልከቱ ፡ ይህንን ፡ ወጣት ፡ ልጅ ፡
ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ነበር ፡ የሞተው ፡ በኔ ፡ እጅ ፡
«ሁል ፡ ጊዜ ፡ ሆኖለት ፡ መከታ ፡ ጠር ፡ ጋሻ ፡
«ዕድል ፡ ይረዳዋል ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ።
ብሎኝ ፡ የነበረ ፡ ይህ ፡ ኮከብ ፡ ቈጣሪ ፡
ያምላክ ፡ ፈቃድ ፡ ኖሮ ፡ የእግዜር ፡ የፈጣሪ ፡
ለዚህ ፡ ታጭቶ ፡ ኖሮ ፡ ቀድሞውን ፡ ሲቀባ ፡
ይኸው ፡ ተፈጸመ ፤ የኔን ፡ ልጅ ፡ አገባ ።
በማናቸው ፡ ዐቅሜ ፡ በየትኛው ፡ ኀይሌ ፡
የምችል ፡ መስሎኝ ፡ ነው ፡ ካምላክ ፡ መታገሌ ።
ድኻ ፡ ብዬ ፡ አይደለም ፡ ይህን ፡ ልጅ ፡ መናቄ ፤
ለሃይማኖት ፡ ነበር ፡ እኔስ ፡ መጨነቄ ፡
ዳሩ ፡ ግን ፡ አልሆነም ፡ አሳቤ ፡ ተናደ ፤
እኔ ፡ ምን ፡ አገባኝ ፡ እግዜር ፡ ከፈቀደ ።





እኔ ፡ የጻፍሁትን ፡ ቃሉን ፡ የለወጠች ፡
ሌላ ፡ ሰው ፡ አይደለም ፡ ይችው ፡ የኔ ፡ ልጅ ፡ ነች ፡

(ወደ ፡ ልጁ ፡ እያየ) ።

ነችና ፡ እሷ ፡ ብቻ ፡ ማኅተሜን ፡ የያዘች ፤
ደግሞም ፡ በሷ ፡ አልፈርድም ፡ አሁን ፡ በዚህ ፡ ነገር ፤
የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ነው ፡ በፍቅር ፡ ማኅደር ፡
በጥበብ ፡ ተፀንሶ ፡ ያደረው ፡ በልቧ ፡
እንዲሳብ ፡ ያረገ ፡ ወደዚህ ፡ አሳቧ ።
እግዜርን ፡ ማን ፡ አየው ? መኖሩን ፡ ማን ፡ ያውቃል ?
ያላዩትን ፡ ነገር ፡ ለማመን ፡ ይጨንቃል ፡
ብለን ፡ በልባችን ፡ እንዳንጠራጠር ፡
ይህን ፡ በመሰለ ፡ ትንግርተኛ ፡ ነገር ፡
እግዚአብሔር ፡ ተገልጦ ፡ ሥራውን ፡ ሲሠራ ፡
ምን ፡ ዕውር ፡ ይገኛል ፡ ዐይኑ ፡ የማይበራ ?
ምን ፡ ጨካኝ ፡ ይገኛል ፡ ልቡ ፡ የማይፈራ ?
ለእምነቴ ፡ መጠጊያ ፡ ለነፍሴ ፡ መሸሻ ፡
እውነተኛን ፡ አምላክ ፡ ልቤ ፡ በጣም ፡ ሲሻ ፡
ጨለማ ፡ የዋጠኝ ፡ እኔ ፡ ቅብዝብዙ ፡
እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ተሟገትሁ ፡ በብዙ ።
ዛሬ ፡ ግን ፡ ተረታሁ ፡ ድል ፡ ሆነ ፡ መንፈሴ ፤
እውነተኛን ፡ አምላክ ፡ አገኘችው ፡ ነፍሴ ፡
አሁን ፡ ግን ፡ ታከተኝ ፡ ይብቃኝ ፡ መግደርደሩ ፤
አምላክ ፡ ቢፈቅድ ፡ ነው ፡ የሆነው ፡ ነገሩ ።
የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ይወደድ ፡ ይነግሥ ፤
ካምላክ ፡ የሚታገል ፡ አለበት ፡ አበሳ ፡

ተሰምቶኛልና ፡ ከእግዚአብሔር ፡ መሆኑ ፡
ይቀጥል ፡ ሰርጋቸው ፤ ይጠጡ ፡ ይዝፈኑ ፤
ይቅር ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ መንፈሴ ፡ ማዘኑ ።
ደግሞም ፡ ቢወደኝ ፡ ነው ፡ እሱ ፡ ባለቤቱ ፡
ይህን ፡ ያኽል ፡ ታምር ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ መሥራቱ ።
ለምን ፡ ይህን ፡ ሠራሽ ፡ በማለት ፡ ጠይቄ ፡
ልጄንም ፡ በከንቱ ፡ ይቅር ፡ ማስጨነቄ ፤
መንግሥቱን ፡ ለናንተ ፡ ሰጠሁኝ ፡ ለቅቄ ።
ሃይማኖት ፡ የሚያድስ ፡ እምነት ፡ የሚያጸና ፡
ዘመን ፡ የሚለውጥ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነውና ።
እውነት ፡ በልጄ ፡ አሳብ ፡ አልሆነም ፡ ይህ ፡ ሰርግ ፤
እኔ ፡ ያቃተኝን ፡ እሷ ፡ ምን ፡ ታድርግ ።
ኮከብ ፡ ፊደል ፡ ሆኖ ፡ ሰማዩ ፡ ብራና ፡
ጥንቱን ፡ ይኸ ፡ ሁሉ ፡ ተጽፎ ፡ አልቋልና ፡
አንተ ፡ ኀያል ፡ ጌታ ፡ ያለኸ ፡ ከሰው ፡ በላይ ፡
ፈቃድኸ ፡ ይፈጸም ፡ በመሬት ፡ በሰማይ ።
እረ ፡ እስቲ ፡ ላግባና ፡ ጣልቃ ፡ በነገሬ ፡
ከቶ ፡ ምን ፡ አመጣኸ ፡ አንተን ፡ እዚህ ፡ ዛሬ ?

## ኮከብ ፡ ቈጣሪ ።

ብዙ ፡ ታሪክ ፡ ያያል ፡ ከሞት ፡ የተረፈ ፤
ያ ፡ ነገር ፡ ከሆነ ፡ ኻያ ፡ ዓመት ፡ አለፈ ።
አስታውሰዋለሁ ፡ ምንም ፡ አልተረሳኝ ፤
የራእይ ፡ ኀይል ፡ ነው ፡ በመንፈስ ፡ ያነሣኝ ።
ጠፈሩ ፡ እንደ ፡ መጽሐፍ ፡ ገጹ ፡ ተለዋውጦ ፡
ኮከቡ ፡ እንደ ፡ ፊደል ፡ ትርጕሙ ፡ ተገልጦ ፡





ሐተታው ፡ ከምንጩ ፡ በደኅና ፡ ተጣርቶ ፡
ይታየኝ ፡ ነበረ ፡ ምስጢሩ ፡ ተከፍቶ ፡
ትንቢቱ ፡ ሲወጣ ፡ ካፌ ፡ ከምላሴ ፡
ይደነቅ ፡ ነበረ ፡ የገዛ ፡ መንፈሴ ።
አለሁ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ነገሩን ፡ ሳልረሳው ፤
እንደ ፡ ሰከረ ፡ ሰው ፡ ልቡን ፡ እንደ ፡ ነሣው ፡
ልክ ፡ እንዳልነበረ ፡ የዚያ ፡ ዕለት ፡ ራሴ ፡
በጣም ፡ ተሰምቶኛል ፡ እኔም ፡ ለመንፈሴ ።
ድምፄና ፡ አንደበቴ ፡ አልነበሩም ፡ የኔ ፤
ያናግረኝ ፡ ነበር ፡ እንደ ፡ ባለቅኔ ።
የበገና ፡ ኸርማት ፡ ቅኝቱ ፡ ሲዋጣ ፡
እንደ ፡ መቱት ፡ አርጎ ፡ ድምፅ ፡ እንደሚያመጣ ፡
ከፍጡር ፡ መካከል ፡ ባገኘው ፡ ብዙርና ፡
ሰውም ፡ መሣሪያ ፡ ነው ፡ የእግዚአብሔር ፡ በገና ።
በእግሩም ፡ ሆነ ፡ በእጁ ፡ ወይም ፡ ባንደበቱ ፡
ሊያዝበት ፡ ይችላል ፡ ሲሻ ፡ ባለቤቱ ፡
ከባለቤቱ ፡ ነው ፡ የመጣልኝ ፡ ቃሉ ፤
መች ፡ ከኔ ፡ ፈለቀ ፡ እውነትስ ፡ ያ ፡ ሁሉ ።
ሌሊት ፡ ተደብቆ ፡ ከቤቴ ፡ የገባ ፡
ልጄን ፡ ሰረቀብኝ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በደባ ።
ምንም ፡ ልጄ ፡ ጠፍቶ ፡ መኖሩን ፡ ባላውቀው ፡
በኮከብ ፡ ያየሁት ፡ ያ ፡ የምጠብቀው ፡
የትንቢቱ ፡ ነገር ፡ ፍጻሜው ፡ ናፈቀኝ ፤
የማደርገው ፡ ነገር ፡ አጥቼ ፡ ሲጨንቀኝ ፡
ልዕልት ፡ ማግባቷን ፡ ሰማሁ ፡ ይህን ፡ ሰሞን ፤
ለማወቅ ፡ ፈልጌ ፡ አግቢው ፡ ማን ፡ እንደሆን ፡

አሁን ፡ ገና ፡ ይኸው ፡ ወጥቼ ፡ ከቤቴ ፡
ለወሬ ፡ ነበረ ፡ ወደዚህ ፡ መምጣቴ ።
ነገሩ ፡ እንዲፈጸም ፡ ያምላክ ፡ ፈቃድ ፡ ኖሮ ፡
እዚህ ፡ አገናኘን ፡ የትንቢት ፡ ቀጠሮ ።

ን ጉ ሥ ።

የትንቢት ፡ ቀጠሮ ፡ እንበለው ፡ እውነት ፡ ነው ፤
አንተም ፡ የኔ ፡ ወዳጅ ፡ ያ ፡ የተጫወትነው ፡
በሃይማኖት ፡ ጉዳይ ፡ የተነጋገር፣ው ፡
ትዝ ፡ ይበልኽና ፡ ፈጣሪኽን ፡ ፍራ ፤
ልቡናኽ ፡ ይሰበር ፡ ከትዕቢትኽ ፡ ጋራ ።
ዛቻኽም ፡ ይወገድ ፡ ይቅርብኽ ፡ ንዴቱ ፤
ሰይፍኽን ፡ በሰላም ፡ ክተት ፡ ወዳፎቱ ፤
አዳምጠው ፡ ሲያስተምረን ፡ ከላይ ፡ ባለቤቱ ፤
ዐይኖችኽ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ አብረው ፡ ይከፈቱ ፡
እንየው ፡ እንስማው ፡ እግዜርን ፡ በአእምሮ ፤
የሚናገረውን ፡ በልባችን ፡ ጕሮ ።

ባለሟል ።

መርጦና ፡ ቀብቶ ፡ እግዜር ፡ ከፍጥረቱ ፡
ንጉሥ ፡ የሚያነግሠው ፡ አይደለም ፡ በከንቱ ፡
ዙፋን ፡ አይሰጠውም ፡ ለከንቱ ፡ ውዳሴ ፤
ሊመራ ፡ አይደለም ፡ ወይ ፡ ሕዝቡን ፡ እንደ ፡ ሙሴ ?
ዐይንዎ ፡ ዐይናችን ፡ ነው ፡ ጆሮዎ ፡ ጆሮቻችን ፤
አምላክ ፡ ይቅር ፡ ይበል ፡ ለየጥፋታችን ።





እንደ ፡ ሰማይ ፡ መልአክ ፡ በንግግር ፡ ቃና ፡
እንደዚህ ፡ ሲያስረዱን ፡ የፈጣሪን ፡ ዝና ፡
እውነተኛን ፡ አምላክ ፡ አግኝተው ፡ ሲሰጡን ፡
ምስክርነትዎ ፡ ከሁሉም ፡ መብለጡን ፡
እንቀበላለን ፡ አምነን ፡ ከልቡና ፤
ሕይወት ፡ አይደለም ፡ ወይ ፡ የነፍሳችን ፡ ጤና ፡
ድንቍርናችንን ፡ እሱ ፡ ተመልክቶ ፡
ላለፈው ፡ ሥራችን ፡ ይቅርታውን ፡ ሰጥቶ ፡
ልጆቹ ፡ ያድርገን ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጣሪ ፤
ርግማን ፡ ይምጣበት ፡ በተጠራጣሪ ።

ን ጉ ሥ ።

አንድ ፡ ሰው ፡ ተልኮ ፡ ይጠራ ፡ ካህኑ ፤
ሰርጉም ፡ አይቋረጥ ፡ እንግዲህ ፡ ዝፈኑ ።
መጠጥ ፡ ያቅርብልን ፡ አሳላፊው ፡ ታዞ ፤
አዝማሪውም ፡ ይምጣ ፤ ማሲንቆውን ፡ ይዞ ።

(ሰርገኞቹ ፡ ተቀመጡ ፤ መጠጥ ፡ ቀረበ ። ዘፈኑ ፡ ደመቀ ፤ ንጉሥ ፡ እንደዚህ ፡ እያለ ፡ ላዝማሪው ፡ ግጥም ፡ ይናገራል) ።

እግዚአብሔር ፡ ሲፈጥረው ፡ ጸጋ ፡ ካለበሰው ፡
እመኑኝ ፡ አይችልም ፡ ዕንቅፋት ፡ ሊሆን ፡ ሰው ።

.........................................................

እግዚአብሔር ፡ ጠፍቶብኝ ፡ ስሻ ፡ ተቸግሬ ፡
ሕፃን ፡ ልጅ ፡ ሲያሳድግ ፡ አገኘሁት ፡ ዛሬ ።

.........................................................

ሰይፍና ፡ ወረቀት ፡ ተጣልተው ፡ ቢማቱ ፡
ተቀዶ ፡ ወደቀ ፡ አሉኝ ፡ ወረቀቱ ፡

ምነው ፡ ታዲያ ፡ እንሆ ፡ የወንጌል ፡ ብራና ፡
ብዙ ፡ ሰይፍ ፡ ሰብሮ ፡ ይኖራል ፡ በደኅና ።

ትርኢት ፡ ፭ ።

(ካህን ፡ መጣ) ።

ን ጉ ሥ ።

የውነተኛው ፡ አምላክ ፡ አገልጋይ ፡ ካህኑ ፡
ይኸው ፡ ደርሷልና ፡ ጊዜውና ፡ ቀኑ ፤
የወንጌልን ፡ ዝና ፡ ተርጕመኽ ፡ አስታውቀን ፤
ደግሞም ፡ ሳትዘገይ ፡ በፍጥነት ፡ አጥምቀን ።
ፍቅር ፡ በጣም ፡ ያውቃል ፡ በውነት ፡ ያንተ ፡ ጌታ ፤
ምስጢሩ ፡ ረቂቅ ፡ ነው ፡ ሲመክር ፡ በርጋታ ።
የወንጌል ፡ ሃይማኖት ፡ ለውነተኛነቷ ፡
በቀሩትም ፡ አንጻር ፡ ለበላይነቷ ፡
አምጣልኝ ፡ አልልም ፡ ማስረጃ ፡ ምስክር ፤
ከፈጣሪ ፡ ጋራ ፡ ሳለሁ ፡ በክርክር ፡
ኻያ ፡ ዓመት ፡ ሆኖኛል ፡ ዛሬ ፡ ግን ፡ ተረታሁ ፤
ካረመኔነት ፡ ጋር ፡ እንሆ ፡ ተፋታሁ ።
መሳፍንት ፡ መኳንንት ፡ ሁላችሁ ፡ ሕዝቦቼ ፡
ስመለስ ፡ አይታችሁ ፡ እኔ ፡ ተረትቼ ፡
አብራችሁ ፡ ከኔ ፡ ጋር ፡ ዛሬ ፡ ተጠመቁ ፤
ከውነተኛው ፡ አምላክ ፡ በቶሎ ፡ ታረቁ ።

ካህን ።

አድምጡኝ ፡ ሁላችሁ ፡ ሳይበዛ ፡ ባጭሩ ፤
ላምጣው ፡ የኛን ፡ ታሪክ ፡ ከምንጩ ፡ ከሥሩ ።





አባታችን ፡ አዳም ፡ እግዚአብሔር ፡ ሲፈጥረው ፡
በፍጹም ፡ ደስታ ፡ በገነት ፡ አኖረው ።
እዚያም ፡ ደኅና ፡ ሲኖር ፡ በደስታ ፡ ስፍራ ፡
የለበትም ፡ ነበር ፡ ጭንቅና ፡ መከራ ፤
ሳይቈፍር ፡ ሳይደክም ፡ ሳያመው ፡ ሳይሠራ ፡
ይበላ ፡ ነበረ ፡ በያይነቱ ፡ ፍሬ ፤
የለበትም ፡ ነበር ፡ አሳብ ፡ እንደ ፡ ዛሬ ።
ካምላኩ ፡ ልተካከል ፡ የሚል ፡ የደንቈሮ ፡
በናታችን ፡ ሔዋን ፡ መጥፎ ፡ ምኞት ፡ አድሮ ፡
በሰይጣን ፡ ክፉ ፡ አሳብ ፡ መንፈሷን ፡ አስክራ ፡
የራሷ ፡ እንዳይበቃት ፡ አዳምንም ፡ መክራ ፡
ሰይጣን ፡ ጠላታችን ፡ እንዲህ ፡ አሳስቶ ፡
በፍቅራቸው ፡ መኻል ፡ በተንኰሉ ፡ ገብቶ ፡
አዳምን ፡ አጠፋው ፡ ተጌታው ፡ አጣልቶ ።
እንጀራውን ፡ ሊያገኝ ፡ እየሠራ ፡ ደክሞ ፡
በሰጠው ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ረግሞ ፡
ከገነት ፡ ተሰዶ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ሲመጣ ፡
ያረሰው ፡ በቅሎለት ፡ ፍሬም ፡ እስቲያወጣ ፡
አዳም ፡ ተቸገረ ፡ የሚበላው ፡ አጣ ።
ችግሩን ፡ አዋይቶ ፡ እያስተዛዘነ ፡
ካምላክ ፡ አማልደኝ ፡ ሲል ፡ መልአኩን ፡ ለመነ ፡
መልአኩም ፡ ያዳምን ፡ ችግር ፡ በማየቱ ፡
የገነትን ፡ ፍሬ ፡ ቈርጠው ፡ ከያይነቱ ፡
ወፎችን ፡ አዘዘ ፡ ላዳም ፡ እንዲወስዱ ፤
ወፎችም ፡ ፍሬውን ፡ ይዘውለት ፡ ሄዱ ።

አዳምን ፡ ሲያጽናኑት ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ቈይተው ፡
አብረው ፡ ሲጫወቱ ፡ አንድነት ፡ ሰንብተው ፡
ገነትን ፡ አስታውሶት ፡ ወፎች ፡ ውበታቸው ፡
በማስተዋል ፡ ብዛት ፡ አይቶ ፡ ሳይጠግባቸው ፡
ወደ ፡ ገነት ፡ ቦታ ፡ ፈጥነው ፡ ሊመለሱ ፡
ካዳም ፡ ተሰናብተው ፡ ወፎቹ ፡ ተነሡ ።
አዳም ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ሐዘኑ ፡ በረታ ፤
ወፎች ፡ አልበደሉም ፡ ዐምፀው ፡ በጌታ ፤
ስለዚህ ፡ አልወጡም ፡ ከደስታ ፡ ቦታ ።
አዳም ፡ ግን ፡ እንሆ ፡ ከወፎች ፡ አነሰ ፤
አመድ ፡ ላይ ፡ ወደቀ ፡ ቅጠልም ፡ ለበሰ ።
ወፎች ፡ መጸወቱት ፡ አጥቶ ፡ የሚጐርሠው ፤
እሱ ፡ አልነበረም ፡ ወይ ፡ ገነት ፡ የነገሠው ?
ብርሃንና ፡ አበባ ፡ ፍሬም ፡ በያይነቱ ፡
ወፎችም ፡ እንስሳት ፡ ደግሞም ፡ አራዊቱ ፡
አልተፈጠሩም ፡ ወይ ፡ እሱን ፡ ሊያጫውቱ ?
ዛሬ ፡ ግን ፡ እንሆ ፡ ሁሉንም ፡ ገፈፈው ፤
ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ ጸጋ ፡ ምንም ፡ አልተረፈው ።
እግዚአብሔር ፡ ሲፈጥረው ፡ ከሁሉም ፡ አክብሮ ፡
በልዩ ፡ ችሮታ ፡ ሠራለት ፡ አእምሮ ፡
በዚሁ ፡ መሣሪያ ፡ አዳም ፡ ግን ፡ መልሶ ፡
አምላኩን ፡ በደለ ፡ ከንስሶቹ ፡ ብሶ ።
እንደ ፡ እንስሳ ፡ ሆኖ ፡ ትክክል ፡ ተፈጥሮ ፡
ይሻለው ፡ ኖሯል ፡ ወይ ፡ ባይሰጠው ፡ አእምሮ ?
የሲሳይ ፡ የውበት ፡ የደስታ ፡ ገዳም ፡
ገነት ፡ ለወፍ ፡ እንጂ ፡ አልሆነችም ፡ ላዳም ።





ይህንን ፡ ባሳቡ ፡ ሲያወጣ ፡ ሲያወርደው ፡
በጣም ፡ አበሳጨው ፤ አዳምን ፡ ነደደው ፡
በጸጸቱ ፡ ብዛት ፡ እያነቀው ፡ እንባ ፡
አብሮ ፡ ወደ ፡ ገነት ፡ አሰበ ፡ ሊገባ ።
አዳም ፡ ከልብ ፡ አዝኖ ፡ ባገኘው ፡ አበሳ ፡
ወደ ፡ ገነት ፡ ሊሄድ ፡ በቶሎ ፡ ተነሣ ።
ወፎች ፡ በክንፋቸው ፡ በረው ፡ ገቡ ፡ ቀድመው ፡
እየሮጠ ፡ በእግሩ ፡ አዳምም ፡ ሳይደክመው ፡
በዱር ፡ በገደሉ ፡ በጕድባ ፡ ባቀበት ፡
ሲወድቅ ፡ ሲነሣ ፡ ሲዞር ፡ ሲንከራተት ፡
ከእግዚአብሔር ፡ ያጣላው ፡ አገኘው ፡ ሰይጣኑ ፤
እንዴት ፡ ልብ ፡ የለኽም ፡ እብድ ፡ ነኽ ፡ በውኑ ፡
ለካ ፡ አሁንም ፡ ልብኽ ፡ ገነትን ፡ ይመኛል ?
ካልሞትክልኝ ፡ ልቤ ፡ መች ፡ ዕረፍት ፡ ያገኛል ፡
ብሎ ፡ ትልቅ ፡ ድንጋይ ፡ ባዳም ፡ ላይ ፡ ጫነበት ፤
አዳምም ፡ ተቀብሮ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ሦስት ፡ ሌት ፡
እንደ ፡ ሞተ ፡ ሆኖ ፡ እተኛበት ፡ ቀረ ፤
ኋላም ፡ ነፍስ ፡ ዘርቶ ፡ ሊነሣ ፡ሞከረ ።
ቢያመው ፡ አስተዋለ ፡ ጐኑን ፡ አቀርቅሮ ፤
አገኘ ፡ ካጥንቱ ፡ ጐድኑን ፡ ተሰብሮ ።
ፍሬም ፡ አነሣና ፡ በቍስሉ ፡ አርሶ ፡
መሥዋዕት ፡ አቀረባት ፡ በደሙ ፡ ለውሶ ።
ደሜ ፡ እንደ ፡ ፈሰሰ ፡ በጨካኝ ፡ ጠላቴ ፡
እንዲህ ፡ ያለ ፡ በደል ፡ ደርሶብኝ ፡ ማየቴ ፡
ፍርዱ ፡ ይድረስ ፡ ላንተ ፡ አለና ፡ ለጌታ ፡
አልቅሶ ፡ ጸለየ ፡ ከተኛበት ፡ ቦታ ።

እግዜር ፡ በምሕረቱ ፡ ይህን ፡ ለቅሶ ፡ ሰምቶ ፡
«አዳም ፡ አዳም ፡ አለው ፡ በድምፁ ፡ ጐብኝቶ ፤
«ምሕረትን ፡ አግኝቶ ፡ የሚድን ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡
«በኔ ፡ ጌታኽ ፡ እንጂ ፡ ባንተ ፡ ደም ፡ አይደለም ።
«የምታገኝ ፡ መስሎኽ ፡ የገነትን ፡ ስፍራ ፡
«አንተም ፡ አይልመድኽ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሥራ ።
«ደምኽ ፡ እንዲህ ፡ ፈሶ ፡ አይቀርም ፡ በከንቱ ፤
«መሬት ፡ ላይ ፡ ወርጄ ፡ እኔ ፡ ባለቤቱ ፡
«እንዳንተው ፡ ሰው ፡ ሆኜ ፡ ሥጋኽን ፡ ለብሼ ፡
«ለጥፋትኽ ፡ ካሳ ፡ ደሜንም ፡ አፍስሼ ፡
«አደርግልኻለሁ ፡ ገነት ፡ እንድትገባ ።
ገንትን ፡ አስቦ ፡ ሆዱ ፡ ስለ ፡ ባባ ፡
አዳም ፡ ግን ፡ አሳቡ ፡ ምሕረትን ፡ አግኝቶ ፡
ወዲያው ፡ በዚያው ፡ ሰዓት ፡ ወደ ፡ ገነት ፡ ገብቶ ፡
ከሐዘን ፡ በቶሎ ፡ ነበረ ፡ ለመዳን ፤
እንደ ፡ ሕልም ፡ ሰማ ፡ ይህንን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡
የሚበጀው ፡ ነገር ፡ ለጊዜው ፡ የበቃ ፡
አላገኘምና ፡ በዚያች ፡ በደቂቃ ።
አራት ፡ ሺ ፡ ዓመታት ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡
የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ በውሉ ፡ ሊሞላ ፡
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የሰው ፡ ሥጋ ፡ ለብሶ ፡
ወንጌልን ፡ ሰበከ ፡ ኦሪትን ፡ አድሶ ፤
መጨረሻም ፡ ደሙን ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ አፍስሶ ፡
እንደ ፡ ነቢያት ፡ ቃል ፡ በመስቀል ፡ ላይ ፡ ሞተ ፤
እስከዚያ ፡ ድረስ ፡ ግን ፡ ስንቱ ፡ ተሳሳተ ።





ባራቱ ፡ ሺ ፡ ዓመታት ፡ ጠላታችን ፡ ሰይጣን ፡
ምንም ፡ አልቦዘነ ፡ ደከመ ፡ ሊያጠፋን ፡
ዩፒቴርና ፡ በዓል ፡ አጶሎን ፡ አቴና ፡
እነዚህ ፡ ጣዖቶች ፡ አልመጡም ፡ በደኅና ፤
እኛን ፡ ሊያጠፉን ፡ ነው ፤ ገነትን ፡ ሊያሳጡን ፡
ከዲያብሎስ ፡ ጋራ ፡ በሲኦል ፡ ሊያስቀጡን ፡
ያሰት ፡ አምላክ ፡ ትቶ ፡ ሁሉም ፡ አረመኔ ፡
ከዘላለም ፡ እሳት ፡ ከክፉ ፡ ኵነኔ ፡
በጥምቀት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ሊድን ፡ የሚችለው ፤
ከፈጣሪው ፡ ጋራ ፡ ዕርቅ ፡ የሚዠምረው ፡
የእግዚአብሔርን ፡ ምክር ፡ ሙሉውን ፡ ሐተታ ፡
ወዲያው ፡ ያገኘዋል ፡ በወንጌል ፡ ገበታ ።
ወንጌልም ፡ ይለናል ፡ የገነት ፡ ጐዳና ፡
እርስ ፡ በርስ ፡ መፋቀር ፡ ነው ፡ በሙሉ ፡ ልቡና ።
ዐዋጁም ፡ ይለናል ፡ ሲያዘን ፡ በጠቅላላ ፡
ላንተ ፡ እማትወደውን ፡ አትሥራ ፡ ለሌላ ።
በመንፈስ ፡ በሥጋ ፡ እንድትዘጋጁ ፡
እንሆ ፡ ይኸ ፡ ነው ፡ የጥምቀት ፡ ዐዋጁ ።

ተፈጸመ ።